አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ

መርሀ ግብር

በቅዱሳን ነገሥታትና በአንድ ጳጳስ ገድል ላይ የተደረገ ንጽጽራዊ ጥናት

ከተጋዳሊ ሚት ንድፈ ሐሳቦች አንጻር

በ

ማሎደ ዋስይሁን

CLEARED
FROM
ILS LIBRARY

ግንቦት 2005 ዓ. ም

አዲስ አበባ

በቅዱሳን ነገሥታትና በአንድ ጳጳስ ገድል ላይ የተደረገ ንጽጽራዊ ጥናት

ከተጋዳሊ ሚት ንድፈ ሐሳቦች አንጻር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ማለደ ዋስይሁን

አማካሪ

ሰላማዊት መካ

ግንቦት 2005 ዓ. ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

በቅዱሳን ነገሥታትና በአንድ ጳጳስ ገድል ላይ የተደረገ ንጽጽራዊ ጥናት ከተጋዳሊ ሚት ንድፈ ሐሳቦች አንጻር

በ

ማለደ ዋስይሁን

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም	ፊርማ
ወ/ሮ ታላማዊት መካ	.....
የፈታኝ ስም	ፊርማ
አየለ ጥቅሌ	.....
ሰርገሙ ገከሙ	.....

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቁ.ጥ.ቁ.
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

ሰው ሁሉ አንድን ነገር ለማድረግ በማቀድና በመፈጸም ሒደት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ እርሱ ካሰበው በላይ ስኬታማ እንዲሆን ግን የሌሎችን ድጋፍና ትብብር ማግኘት ያስፈልገዋል፡፡ እኔም ተምሬ ይህንን ጥናት በማከናውንበት ጊዜ ድጋፍና ትብብሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥር የሚገኘውን ማኅበረ ቅዱሳንን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገውን ወጪ በተወሰነ ደረጃ በመደገፉ ሳላመሰግን አላልፍም፡፡

ገድላት ለሃይማኖታዊ አገልግሎት፣ ለታሪክ ጥናት ከሚሰጡት ጥቅም ባለፈ እንደ ሥነጽሑፍ እሴት ሊጠኑም እንደሚችሉ ፍንጮችን በመስጠትና በማነሣሣት እገዛ ላደረገችልኝ አማካሪዬ ወይዘሮ ሰላማዊት መካ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አጠቃሎ

ይህ ጥናት በማኅበረሰቡ ዘንድ የመዓርግ ልዕልና ባላቸው ማለትም ነገሥታትና ጳጳስ ስም በተጻፉ ገድሎች ውስጥ የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ እንዴት እንደተገለጸና እነዚህን ገድላት ያበቀለ ማኅበረሰብ የራሱን የሚኖርበትን፣ ሊኖርበት የሚሻውን ርእዮተ ዓለም እንዴት እንደቀመረበትና እንዳሰረገበት ማጥናት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በተመረጡት ሦስት ገድላት ላይ ጆሴፍ ካምቤልና ዴቪድ ሌሚንግ ስለተጋዳሊ ሚት ካነሧቸው ጽንሰ ሐሳቦች አንጻር ትንታኔ አድርጓል፡፡ በዚያም መሠረት በዋናነት በገድላቱ ተመሳሳይና ተቀራራቢ የመባያ ጉዳዮች /motifs/ ያሉ ሲሆን እነዚህ መባያዎች ደግሞ ነገሥታትና ጳጳሳት ተጋዳልያነ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል፣ መቅደስ መሥራት፣ ወደኢየሩሳሌም የመጓዝ፣ በጽድቅና በትሩፋት የላቀ መሆን እና ሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች የተንጸባረቀባቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ የመባያ ጉዳዮችና ትእምርቶች ማኅበረሰቡ ራሱን በዓለም ላይ የተመረጠ፣ አሸናፊ፣ በሰማይም በምድርም የከበረ አድርጎ ያቀርባል፡፡ እነዚህ በረከቶች የተሰጡት በተጋዳሊው የመመረጥ፣ የተጋድሎና አንዳች በረከትን ይዞ ለተከታዮቹ በመገኘት ሒደት ውስጥ ነው፡፡ በመሆኑም ጆሴፍ ካምቤል ስለተጋዳሊ ሚት ባቀረበው ንድፈ ሐሳብ የተነተናቸው ተጋዳሊው ያልፍባቸዋል ካላቸው ምዕራፎች ጋር ተገናዝበው የተጨበጡ ግኝቶች ናቸው፡፡ የነገሥታቱና የጳጳሱም ገድሎች ተመሳሳይ መባያዎችና ትእምርቶች ያሏቸው በመሆኑ አንድ ዓይነት ርእዮተ ዓለምን ማኅበረሰቡ ለመትከል እንደተጠቀመባቸው፤ እንዲሁም ንጉሡና ጳጳሱ አንድም ሁለትም ሆነው የሚንዘቡበትን ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለማዊ መሠረት በንጽጽራዊ ዕይታም መረዳት ተችሏል፡፡

ማውጫ

ርእስት ገጽ

ምስጋና.....I

አጠቃሎ.....II

ማውጫ.....III

1 የመግቢያ ክፍል

1.1 መግቢያ.....1

1.2 የጥናቱ ዳራ.....2

1.3 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት.....7

1.4 የጥናቱ ዓላማ.....7

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ.....8

1.6 የጥናቱ ወሰን.....8

1.7 የጥናቱ ዘዴ.....8

2 ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.....11

2.2 የንድፈ ሐሳብ ትንታኔ.....18

3 ትንታኔ

3.1 ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ.....29

3.1.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል.....29

3.1.1.1 የዘር ሐረግ ቆጠራ.....30

3.1.1.2 የጽንስና የልደት ቀን.....32

3.1.1.3 ማኅጸነ ዮርዳኖስ አብራከ መንፈስ ቅዱስ.....34
3.1.1.4 የጌርጌሴኖን አጋንንት.....36
3.1.2 አንድ ሕልም.....38
3.1.3 በትረ ሙሴ.....40
3.1.4 የጽድቅ ትሩፋት.....43
3.1.5 ቤተመቅደሱ.....45
3.1.5.1 ከሰሎሞን መቅደስ የሚበልጥ መቅደስ.....46
3.1.5.2 ኢየሱስ ያከበረው መቅደስ.....47
3.1.6 ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም.....49
3.2 ገድለ ሳላማ ከሳቱ ብርሃን.....53
3.2.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል.....53
3.2.1.1 ዐውደ ልደት.....53
3.2.1.2 የክህነት ዘር ቆጠራ.....54
3.2.2 አንድ ሕልም.....58
3.2.3 መስበክና ማጥመቅ ለታላቁ ቤተመቅደስ.....59
3.2.4 የተባረኩ ምንጮች.....62
3.3 ገድለ ላሊበላ.....65
3.3.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል.....65
3.3.1.1 ዐውደ ልደት.....65
3.3.1.2 ንግሥና.....66
3.3.1.3 ሞትና ትንሣኤ.....67
3.3.2 ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም.....68
3.3.3 የጽድቅ ትሩፋት.....72
3.3.4 ቤተመቅደሱ.....75

3.4 ንጽጽራዊ ዕይታ.....75
ማጠቃለያ 81
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው.....88
መዘርዝር.....90

1 የመግቢያ ክፍል

1.1.መግቢያ

ይህ ጥናት ሦስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የጥናቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ የጥናቱ የመግቢያ ክፍል የሆኑትን የጥናቱን ዳራ፣ አነሣሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ጠቀሜታና ዘዴን ይዟል፡፡ ይህ የመግቢያ ክፍል በተለያዩ መስኮች የገድላት ጥናት ምን ያህል እንደተሔደበት ስለ ገድላትም የቀረቡ ጥናቶች ገድላትን በምን ዓይነትና ደረጃ እንደገለጿቸው ለማየት የሞከርኩበት ነው፡፡

በጥናቱ ሁለተኛ ምዕራፍ የመጀመሪያ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሁለት የኤም ኤ የጥናት ሥራዎችን ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ፡፡ በዚህ ክፍል በገድላት ላይ የተጠኑ ሌሎች ሥራዎች ቢኖሩም በኤም ኤ ደረጃ ያሉና ከእኔ ጥናት ጋር ቅርበት እንዳላቸው ያመንኩባቸውን ብቻ መርጬ ዘርዘር አድርጌ አሳያለሁ፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለትንታኔ ያግዙኛል የምላቸውንና የጥናቱን ወሰን የሚያመለክቱ የንድፈ ሐሳብ ትንታኔዎች አቅርቤያለሁ፡፡

በምዕራፍ ሦስት ደግሞ ለጥናት የመረጥኳቸውን ሦስት ገድላት ካቀረብኩት ንድፈ ሐሳብ፣ ዓላማና ዘዴ በመነሣት ለመተንተን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በቅድሚያ የአብርሃ አጽብሐን ገድል በመተንተን ከዚያም በታሪክ መሠረት ዘመንኛ ነው ያልኩትን የጳጳሱን የሰላማ ከሳቱ ብርሃንን ገድል ተንትኛለሁ፡፡ ይህም በታሪክ ዐውድ አክሱማውያን በሆኑት ታሪካዊዎቹ ነገሥታትና ጳጳስ ስም የተጻፉትን ገድላት ትረካ ለማነጻጸርና ለመተንተን አመቺ ነው ብዬ ስላመንኩ ያደረግሁት ነው፡፡ ከዚያም በታሪክ ዐውድ ለየት የሚለውን የላሊበላን ገድል አስከትዬ በትንታኔዬ አካትቻለሁ፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ሌላ ክፍል አድርጌ በትንታኔዬ የወሰድኩት እነዚህን ሦስት ገድላት ካሏቸው የጋራ የመባያ ጉዳዮችና በውስጣቸው ከሚያስተጋቧቸው ርእሶተ ዓለሞች አንጻር በንጽጽር ለማየት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በዚህም ክፍል የንጉሡን ገድል ከጳጳሱ፣ የንጉሡን ገድል ከሌላው ንጉሥ ገድል ጋር የተነጻጸረበት ነው፡፡ የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል የማጠቃለያ ሐሳብ ሲሆን በትንታኔው የተደረሰባቸውን ዋና ዋና ፍሬ ጉዳዮች የሚያስዳስስ ነው፡፡ ከዚያም ቀጥሎ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ቀርበዋል፡፡ ለጥናቱ ጥቅም የሰጡ መዘርዝሮችም ተካተው ቀርበዋል፡፡

1.2 የጥናቱ ዳራ

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ከሚደረግባቸው የጥናት መስኮች አንዱ በኢትዮጵያ የመካከለኛው የታሪክ ዘመን የሚገኘው የሀገሪቱ ሥነ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአመዛኙ ሃይማኖታዊ ተረኮች ላይ ስለሚያተኩር በዚህ ረገድ የግእዝ ሥነጽሑፍ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል፡፡

የክርስትና ሃይማኖት ከአራተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የሀገሪቱ መንግሥታዊ ሃይማኖት ሆኖ እስከ ሃያኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ ከመቆየቱ የተነሣ የዚህ ሃይማኖታዊ ሥነጽሑፍ አመንጪና ባለቤት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ንጉሥ ኢዛና ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ሃይማኖቱን የመንግሥቱ ሃይማኖት እንዲሆን በማድረጉ ቀጣዩ ዘመን ሙሉ በሙሉ የክርስትና ሃይማኖት የነገሠበት ሥነ ጽሑፍ ሆኖ ታይቷል፡፡ የሚጻፉትና የሚነሡት ነገረ ጉዳዮች ወይም ጭብጦች ክርስትናን የሚያንጸባረቁ ሆነዋል፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነጽሑፍ ስንል ለሃይማኖታዊ አገልግሎት ከዋሉ መጻሕፍት በዘለለ የምናገኘው ሌላ ዓይነት ጽሑፍ ትርጉም ባለው መጠን አለመኖሩ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ አምሳሉ አክሊሉ «*የክርስትና ሃይማኖት በሀገሪቱ ላይ ጠንካራ እድና ተጽዕኖ ስለነበረው ከሃይማኖት ውጪ የሆኑ መጻሕፍት እንዳይወጡ አድርጓል*» ሲሉ ገልጸዋል /አምሳሉ፣1976፣ ገጽ 32/፡፡

እነዚህ ጽሑፎች አብዛኞቹ ከሱርስት፣ ከግሪክ፣ ከአረብኛና ቅብጥ ቋንቋ የተተረጎሙ በመሆኑም የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነጽሑፍ የትርጉም ሥነጽሑፍ ነው አሰኝተውታል /ዝኒ ከማሁ፣ 32/፡፡ ይሁን እንጂ የሀገሪቱ የራሷ የሚባሉ የፈጠራ ድርሰቶች መኖራቸውን አምሳሉ አክሊሉ ሲያመለክቱ «*አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ ታሪክና እንደ ገድላ ገድል በመሳሰሉት በሀገር ውስጥ በተደረሱ መጻሕፍት ውስጥ ከትርጉም ይልቅ የፈጠራ ድርሰቶችም እናገኛለን*» ብለዋል /ዝኒ ከማሁ፣ 32/፡፡

ጌታቸው ኃይሌ ደግሞ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የግእዝ ሥነጽሑፍ ዓይነቶች በአራት ከፍሎ ያዩአቸዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ብሉያትና ሐዲሳትን የሚያካትተውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ሁለተኛ ዓይነት ደግሞ ዜና መዋዕሎች ናቸው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ሰባ ሊቃናት ተርጉመዋቸው እንደነበር የሚነገርላቸውና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተጨማሪ ሆነው የሚካተቱትን፣ የመጻሕፍቱንም ቁጥሩን ሰማንያ አንድ ያደረሰችበትን ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት/Deutro Canonical Books/[1] እና ሊቃውንት ተብለው

[1] እነዚህን መጻሕፍት ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ያመጣቸው የሰባው ሊቃናት ትርጉም የሆነው ጥንታዊው የግሪክ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ /Septuagint/ ነው፡፡ ይህ የሰባው ሊቃናት ትርጉም /septuagiant/ የግሪክ ተናጋሪ አይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍልስጥኤማውያን አይሁዶች ቀናኢ መጽሐፍ ቅዱስ

የሚታወቁትን ተጨማሪ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ይይዛል። በአራተኛ ደረጃ ዓይነት አድርገው ያቀረቡት ደግሞ የቅዱሳንን ሥራና ተአምራት የሚገልጹ መጻሕፍትን /Hagiography/ ሲሆን ገድላትና ተአምራትን የሚያመለክት ነው/Getatchew, 1988, 37/

እነዚህንም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአራት ወይም በአምስት ዘመናት ከፍሎ ሲያያቸው የመጀመሪያዎቹ የአክሱማውያን፣ ሁለተኛውን የሚጠት/Restoration period/፣ ሦስተኛውን ደግሞ በአንዳንዶች ወርቃማው የሥነጽሑፍ ዘመን የሚባለውን ከ1430 እስከ 1520 ድረስ ያለውን ጊዜ፣ አራተኛና አምስተኛውን ደግሞ ከግራኝ ወረራ በኋላ ያሉትን ጊዜያት እንደሚሸፍን ይገልጻሉ።/ዝኒ ከማሁ/

በኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነጽሑፍ ውስጥም አምሳሉና ጌታቸው ትኩረት የሰጡት ዐፄ ዘርአያዕቆብ የገዛበትን ከ1430 በኋላ ያለውን ከእርሱም በኋላ እስከ ግራኝ ወረራ 1520ዎቹ ድረስ ያለውን ዘመን ነው። ይጻፍበት የነበረው ዓላማ የጽሑፉ ዓይነትና መጠን ትኩረት እንዲሰጠው የጋበዘ ሆኖ አግኝተውታል። አምሳሉ አክሊሉ በዘርአያዕቆብ ዘመን ኢትዮጵያውያን ደራሲዎች ትርጉም ባለው ሁኔታ መጻፍ የጀመሩበት በመሆኑ ዘመኑ ለየት ያለ መሆኑን አመልክቷል። ንጉሡ ከእርሱ ዘመን በፊትና በእርሱም ዘመን ሠልጥኖ የነበረውን የጥንቆላና የአስማት ሥራ በመቃወም የዘመኑ ሊቃውንት እንዲቆሙ ያደረገው ግፊት ለግእዝ ሥነጽሑፍ ማደግ በር ከፍቷል። እነዚህን የጥንቆላ ተግባራት ለማጥፋትና ሃይማኖተኞችን ለመጠበቅ ለማጽናት በመንግሥታዊ ሥልጣኑ ከሚወስደው ቅጣት በተጨማሪ ራሱና በጊዜው የነበሩ ሊቃውንት መጻሕፍትን እንዲጽፉ ያበረታታ ነበር /አምሳሉ፣ 1976፣ ገጽ 32/። ከትርጉም ሥራዎችም ይልቅ ሀገርኛ ሥነ ጽሑፎች እንዲኖሩ ስላደረገው ጥረት ጌታቸው ኃይሌ ሲጠቅሱ

> *በንጉሡ ነገሥቱ ዓይን በዚያን ዘመን ቤተክርስቲያንን ያጋጠሟት ሁለት ችግሮች ነበሩ። ጥንቆላና የአስማት ሥራ ዘርአያዕቆብ ቀድሞ ወደ ግዕዝ የተተረጎሙትና በግዕዝም የተጻፉት መጻሕፍት ለታወቀና ለተለየ ዓላማ የተጻፉ ቢሆንም እርሱ በጊዜው ወሳኝ ናቸው ብሎ ከሚያስባቸው ችግሮች ጋር አብረው የሚሔዱለት አልነበሩም። ስለዚህም እርሱ ራሱ ተሰጥኦ እንዳለው እንደ አንድ ጸሐፊ በሕዝቡ መካከል የነበሩትን ኢክርስቲያናዊ ተግባራት የሚያወግዙ ከፍተኛ ብቃት የታየባቸውን በርካታ መጻሕፍትን ጻፈ። መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ባህርይ፣ ተአቅቦ ምስጢር ከጻፋቸው ጥቂቶቹ ናቸው። ዘርአያዕቆብ ለትርጉም ሥራዎች ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ ይመስላል። የራሳቸው ባህል ላላቸው ለኢትዮጵያውያን ሀገርኛ አድርጎ ማቅረብ የበለጠ ትርጉም የሚሰጥ /ጠቃሚ/ እንደሆነ ያስብ ነበር* /Getatchew, 1988, 39/

በኢትዮጵያውያን ደራሲያን ተጻፉ ከሚባሉትና የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሥነጽሑፍ ጥናት ትኩረት ከሚሰጥባቸው ዘውጎች አንዱ ገድል ነው። ገድል ማለት «ተጋደለ» ከሚለው የግእዝ

በመጠኑ ይለያል። ይህም በእስክንድርያ አይሁድ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው መጻሕፍት ቁጥር በትውፊትም ሆነ በጉባኤ እንዳልተወሰነ ያሳያል። በጣም ጥንታዊ በሆነው የግሪክ የብሉይ ኪዳን ቅጂ /Codex Vaticanus/ ሁሉንም ሁለተኛ ቀኖናት/ Deutro Canonical Books/ ይዟል። /ቸርነት፣ 2003/

ግሥ ,የተገኘ ሲሆን በቁሙ ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ፣ ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም፣ የሚሠሩት ሥራ፣ የሚቀበሉት መከራ፤... መንፈሳዊ ዜና ወግ ታሪክ የቅዱሳንን መከራና ጸጋ ተጋድሏቸውን የሚናገር መጽሐፍ ነው:: /ኪዳነ ወልድ፣ 1948፣ ገጽ 301/

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ201 ያላነሡ ገድላት እንዳሉ ክነፈርግብ ዘለቀ በጥናታቸው ያመለከቱ ሲሆን እነዚህም በዋናነት በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስቲያናዊ መንግሥት ከተመሠረተበት 4ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ተጽፈዋል /Kineferegeb, 1975/::

ታደሰ ታምራት ገድላት በአክሱም በዛጉዌ እና በሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት አገዛዝ ዘመን የነበሩ ቅዱሳንን ሁሉ የሚያነሡ መሆናቸውን ይገልጻሉ:: እነዚህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅድስና የሰጠቻቸው ሰዎች ወጥ ገድሎች መጻፍ የጀመሩት ከዘርአያዕቆብ ዘመንም በፊት ከዐሥራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ሲሆን ከዚያ በኋላ ግን የበለጠ እየተስፋፉ መሔዳቸው ይነገራል:: በጉልህ የሚታየው እጅግ ትኩረት የተሰጣቸው ግን በመካከለኛው የኢትዮጵያ የታሪክ ዘመን ውስጥ ከዐሥራ ሦስተኛው እስከ ዐሥራ ሰድስተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ለነበሩ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ነው::

እነዚህ ሦስት ምዕተ ዓመታት/ ከይኩኖ አምላክ እስከ ግራኝ ወረራ ድረስ/ ደግሞ የኢትዮጵያ ሰሎሞናዊ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ብቸኛ ኃያልና ገናና መንግሥት ሆኖ የታየበት በመሆኑ ሥነጽሑፍን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ በሆኑ መስኮች እመርታ ያሳየበት ጊዜ ነበር:: መንግሥቱ ጠንካራ ክርስቲያናዊ መንግሥት ስለነበርና የአገዛዙም ርዕዮት ከዚያ የሚቀዳ፣ ዓላማና ተግባሩም ያንን የሚረዳ ሆኗል:: ስለዚህም ሰፊ ሃይማኖታዊ፣ ሥነጽሑፋዊ ዕሴቶች የተገኙበትና ለተግባራቱ ማዕከል የነበሩት ገዳማትና ገዳማዊ ሕይወት የተስፋፉበት ዘመን ነበር /Taddesse, 1988, 3/

ገድላቱ የሚጻፉበትም ዓላማ በዋናነት ለሃይማኖታዊ ትምህርትና ተግባር ማስፋፊያ ታስቦ ነው:: የቅዱሱን ገዳማዊ ሕይወት ከፈጣሪም ጋር የነበራቸውን ግንኙነት መመስከር ቅዱሱም የኖረበትን ገዳም ወይም ሥፍራ /የተወለደበትን፣ ያደገበትን፣ ተአምራት የሠራበትን፣ ያስተማረበትን፣ የተጋደለበትን፣ የተቀበረበትን...ወዘተ/ ገናናና የተከበረ ለማድረግ ነው:: ስለዚህ አብዛኞቹ በታሪክ የታወቀ ሥፍራና ጊዜን መቼት አድርገው ተጽፈዋል::

ስለአጻጻፋቸው ፍንጭ የሚሰጠው የታደሰ ታምራት ጥናት የገድላቱን ጸሐፊዎች በምናብ የማርቀቅ፣ የማስፋት፣ የማግነን ሚና ሳይክድ የመረጃ አገኛኘቱን እና የተስፋፉበትን ጊዜና ሁኔታ እንደሚከተለው ያስቀምጣል፣

...የሚጻፈው ደግሞ ከዘመዶቹ እየተጠየቀ በተወሰደ መረጃ ሲሆን አስባስቦ አደራጀቶ የሚጽፈው ግን የገዳሙ አበምኔት ወይም በቅዱሱ ተከታዮች ይሆናል። አንዳንዶቹ ወዲያው ከቅዱሱ ዕረፍት በኋላ የተጻፉ ሲሆን ሌሎች ከተራዘመ ጊዜ በኋላ ተጽፈዋል። የአንዳንዶቹ ዋናው ቅጂ በግራኝ ዘመን የጠፉ ሲሆን በትውስታም የተጻፉ አሉ። አንዳንዶቹ የተጻፉበትን ዘመን የሚጠቁም ፍንጭ ሲኖራቸው ሌሎች ግን በአንዳንድ ክስተቶችና ስሞች አማካኝነት ለማወቅ ጥረት ካልተደረገ በቀር አይገኝም። /Taddesse , 1988, 5/

በእርግጥ ኢትዮጵያ የነበሩትም ገድሎች ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያውያን ደራሲያን የጻፏቸው ናቸው ማለት እንደማይቻል ሊቃውንት ይገልጻሉ። አምሳሉ አክሊሉ በሁለት ከፍለው የመጀመሪያው ዓይነት የትርጉም ገድል ነው፣ ሁለተኛው ወገን ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የጻፏቸው ወጥ ገድላት መሆናቸውን ያስረዳሉ /አምሳሉ ፣1976 55/። ይሁን እንጂ የገድላቱን ምንነት በተሻለ ለመረዳት ያሉባቸው ውስንነት አለ። ከእነዚህም ውስንነቶች መካከል የብዙዎቹ ገድላት ጸሐፊዎች ማንነት አለመታወቅ፤ የተጻፉበትም ቁርጥ ጊዜ በውል አለመለየቱ እና ጸሐፊዎቹም የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ምንጭ ተጠቅመው አለመጻፋቸው ተጠቃሾቹ ናቸው /Selamawit, 3/። እነዚህ ሀገርኛ ገድሎች ለታሪክና ለሥነጽሑፍ ጥናት ካላቸው ወሳኝ ድርሻ አንጻር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያን ጥንታዊና የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ሁሉ ለማጥናት ለሚነሣ ሁነኛ የመረጃ ምንጮች ከመሆን አያመልጡም። በተለይ ደግሞ ለሥነጽሑፍ ጥናት ተመራማሪዎች ስላላቸው ዋጋ አምሳሉ አክሊሉ ሲገልጹ

የገድሎችን ሥነጽሑፋዊ ዋጋ በምንገመግምበት ጊዜ የአንድ ጻድቅ ታሪክ ሲጻፍ ያ ጻድቅ በሕይወቱ የሠራቸውን ሥራዎች፣ ያደረጋቸውን ተጋድሎዎች ለመግለጽ ሥዕላዊ ወይንም ገላጭ በሆነ የድርሰት ዓይነት ሲገለጽ እናያለን። ቅዱሱ በሕይወቱ ያደረገውን ገድል ብቻ ሳይሆን ደራሲው ቅዱሱ እንዲያደርገው የሚመኘውን ጭምር በፈጠራ ጽሑፍ አስጊጦ ያቀርብለታል። ከዚህም የተነሣ የደራሲው ያስተሳሰብ አድማስ ከእውነተኛው ታሪክ መጥቶ ሔዶ ምናባዊ ችሎታውን ያንጸባርቃል። /አምሳሉ፣ 1976፣ ገጽ 56/

በሌሎችም ቤተእምነት ተከታዮች ዘንድ ተሻግሮ ተጽዕኖ ስለመፍጠሩ ወይም ስላለመፍጠሩ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም በተለይ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በገድላቱ ውስጥ የሚታየው የግእዙ ቋንቋ ውበት፣ የምናብ ምጥቀት እስከአሁን አንባቢና አድማጭ እንዳያጡ አድርጓል። ከዚያም አልፎ መጽሐፍ ቅዱስን የመሰሉ ሃይማኖታዊ ጽሑፎች ለአውሮፓውያን የሥነጽሑፍ ዕድገት በር መሠረት እንደነበሩ ሁሉ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ ሥራዎች ላይም ሃይማኖታዊ ገድላት ተጽዕኖ የፈጠሩና መሠረት ሆነው የሚታዩ ናቸው። በተለይ በታሪክ አወቃቀርና በቋንቋ አጠቃቀም በኩል የነበራቸው ድርሻ በሊቃውንቱ የተመሰከረ ነው።

በሀገራችን የታወቀ የተለመደ ከሙያ የዋለ የገድል አጻጻፍ ቴክኒክ አለ። ገድል የአንድ ሰማዕት ወይንም የአንድ ጻድቅ የሕይወት ታሪክ ነው። ገድል በጠቅላላ የሚያወጋው ወይም የሚተርከው የሰማዕቱን ወይም የጻድቁን ተጋድሎ ነው፤ ስለሰማያዊው ልዕልና ስለሰማያዊው ክብር መንፈሳዊ የሆነ ምድራዊ ተጋድሎ። አተራረኩ በመንፈሳዊ ዕውነት ላይ የተመሠረተ ነው። ትልምና ባህርያት፣ የአተራረክ ስልትም አለው፤ የአተራረክ ፈሊጥም አለው፤ ብሎም ገድለ ተክለሃይማኖትን መጥቀስ ይበቃል። አንቱ የሚባል ወይም ለመባል የሚሻ ደራሲ የገድልን አጻጻፍ አጥርቶ ማወቅ ግዴታው ነው። ብዙ ነገር ይማራል። አያሌ ጥበብ ይቀስማል። በቴክኒክም ይበለጽጋል። /ዮሐንስ አድማሱ፣1961/

ስለዚህ በገድላት ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ሁሉ በአጠቃላይ የሀገራችን የሥነጽሑፍ ታሪክን፣ የሥነጽሑፍ ዓይነትና ደረጃን ለመረዳት ለሚደረገው ግስጋሴ መንደርደሪያ ናቸው። ማለት ይቻላል። ገድላት በሌላው ዓለም ሚታዊና አፈታሪካዊ ሌሎችም የተረክ ዓይነቶች የሚገኙባቸው የጥንታዊው ሥነጽሑፍ ወሳኝ ክፍሎች መሆናቸውን በማመን በዓይነትና በደረጃ እየተለዩ በሊቃውንት ሲጠኑ ቆይተዋል።

በገድላት ጥናት ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ተመራማሪዎች በተለያዩ የምርምር መስክ ዓይነቶች አሉ። ከእነዚህም፣ ኤንሪኮ ቼሩሊ፣ ኮንቲ ሮሲኒ፣ ጌታቸው ኃይሌ፣ ታደሰ ታምራት ታውሎ ማራሲኒ፣ ስቴቨን ካፕላን፣ ክነፈ ርግብ ዘለቀ፣ ማሪሎር ዴራት፣ ዴኒስ ኖስኒስቲን፣ ተስፋዬ ገብረማርያምና ሰላማዊት መካ ይገኛሉ። አብዛኞቹ ከታሪክና ከሥነ ድርሳናት ጥናት አንጻር የተጻፉ ሲሆን በሥነጽሑፍ መስክ ሰላማዊት መካ በገድላት ላይ ያደረገችው ጥናትም ተጠቃሽ ነው። ይህ የሚያመለክተው በገድላት ላይ የበለጠ ጥልቅ ጥናት እያደረጉ ለመሔድ የሚያስችል በቂ መሠረት መኖሩን ነው።

በተለይ በሥነጽሑፍ ረገድ የተወሰኑ አጥኚዎች በገድላት ቅርጽና ቴክኒክ ላይ በማተኮር ሲሠሩ ሌሎች ደግሞ ገድላት ከሃይማኖታዊ ጽሑፍነታቸው ባለፈ ያላቸው ሌላ ትርጉም ላይ በማተኮር ለመመርመር ጥረዋል። በተለይ ሰላማዊት መካ ያነሣችው በገድላት ውስጥ የሚንጸባርቀውን የጾታ ፖለቲካ በተለይም የሴቶች ገድላት ይዞታና የጸሐፊ ገድላቱ የገለጻ አንድምታ የተመረመረበት ነው። በተያያዥ የአራጌ ይመር በአራት ገድሎች ላይ የተደረገ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ ሰላማዊት ያነሣችውን የጾታ ጉዳይ ጨምሮ ተጋዳሊዎቹ ሊላበሱት ስለሚፈልጉት የእስራኤላዊነት መለዮ ተንትኗል። በእነዚህ ጥናቶች በዋናነት እየተነጻጸሩ የቀረቡት የሴቶችና የወንዶች ገድላት በመሆናቸው በገድላቱ ውስጥ የተንጸባረቀውን የእነዚህን ማኅበራዊ መደቦች ቡድኖች /social group/ በገድላቱ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ለማሳየት ረድቷል።

በኤም ኤ ደረጃ በሥነጽሑፍ ዘርፍ የአንተነህ አወቀ በግዕዝ ቋንቋ በተጻፉ ተረኮች በመጀመሪያዎቹ የአማርኛ ዝርው ልቦለዶች ውስጥ ያለውን የተራኪውን ሚና ያሳየበትን ጥናት አድርጓል። ኤፍሬም እሸቴ ደግሞ በታመረጡ አራት ገድሎች ውስጥ ያለውን የአጻጻፍ ቴክኒክ አጥንቷል።

በገድላት ላይ በኤም ኤ ደረጃ ጥናት ከመከናወኑ በፊት በቢኤ ደረጃ የተሠሩ ጥናቶችም ነበሩ፡፡ ስባሔ ካሳው በ1981 ዓ.ም ሥነጽሑፋዊ ፋይዳ እንዳለው አምንበታለሁ ብሎ የመረጠውን የገድለ ተክለሃይማኖትን የአጻጻፍ ባህርይና ሥነጽሑፋዊ ዕሴት ላይ ዲግሪን አዘጋጅቷል፡፡ በ1983 ደግሞ ሠርጸ ገብረመድኅን በገድለ ጊዮርጊስ የአጻጻፍ ባህርይና ሥነጽሑፋዊ ዕሴት ላይ ዲግሪን አዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በገድላት ላይ በቢኤ ደረጃ በሥነጽሑፍ ጥናት ውስጥ የታዩ ጥረቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ጥናቶቹ የእኔ ጥናት በሚያተኩርበት ገጽታ ማለትም የገድላቱን ቅርጽና ቴክኒክ በግርድፉ ለማየት የተደረጉ ጥረቶች ናቸው፡፡

1.3 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ገድላትን የማውቃቸው በሚሰጡት ሃይማኖታዊ አገልግሎት ከዚያም ሲያልፍ ለታሪክ ጥናት የመረጃ ምንጭ በሚሆኑበት ደረጃ ነበር፡፡ በኤም ኤ ደረጃ የሥነጽሑፍ ትምህርትን ለመከታተል በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ስገባ ግን በጥንታዊ የሥነ ጽሑፎች ላይ በተሰጠው ትምህርት ገድላት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥነጽሑፍ ዋነኛ ተጠቃሽ ክፍሎች መሆናቸውን ለመረዳት ቻልኩ፡፡ ይህንኑ መነሻ አድርጌ የተጠኑ ጥናቶችን አይቻለሁ፡፡ ከዚያም በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ሥር ያቀርብኳቸውን ጥናቶች ማየቴ የበለጠ የኤም ኤ የጥናት ርእሰ ጉዳዬ ከዚህ መውጣት እንደሌለበት ወሰንኩ፡፡ ይህን እንድወስን ደግሞ የበለጠ ድፍረትን ያላበሰችኝ አማካሪዬ ወይዘሮ ሰላማዊት መካ ነች፡፡ በተለይም የነገሥታትና የጳጳሳት ገድላት ላይ ለይቶ በወገን በወገኑ መሥራት በዚህ ዘውግ ለሚካሔደው ሥነጽሑፋዊ ጥናት መሠረት የሚሆኑ ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤዎችን ለማምጣት አስተዋጽኦ በማድረግ እንደሚጠቅም ያደረግነው ውይይት መነሻዬ ነበር፡፡

1.4 የጥናቱ ዓላማ

አጠቃላይ ዓላማ

የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ በቅዱሳን ነገሥታትና በጳጳሳት ገድላት ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ ወሳኝ መባያዎችን በመተንተን ማሳየት ነው፡፡

ዝርዝር ዓላማ

- የተጋዳሊዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስን የመምሰል አካሔድ ትርጉምና አንድምታ ምን እንደሆነ ማሳየት፣
- በተደጋጋሚ በገድላቱ የሚዘወተሩት መቅደስን የመሥራት ዝንባሌ ትርጉምና አንድምታ መተንተን፡
- ተጋዳልያኑ ወደ ምድራዊትና ሰማያዊት ኢየሩሳሌም የሚያደርጉትን ገዘፍ ፋይዳ ማሳየት፡

- በተጋዳልያኑ የተጋድሎ ምዕራፎች ውስጥ ሁሉ የሚታዩ የጽድቅ ትሩፋትና የኃይል እሳቤዎች መነሻና መድረሻ ትርጓሜዎችን መመርመር፣
- በነገሥታቱና በጳጳሱ ገድላት ያሉ የመባያ ጉዳዮችን እያነጻጸሩ ልዩነትና አንድነቱን በንጽጽር ማሳየት፤

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

- የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብን መነሻ አድርገው የተሠሩ ጥናቶችን በበቂ ሁኔታ የተሟላ ገጽታቸውን ለመረዳት ይጠቅማል። ይልቁንም በነገሥታትና በጳጳሳት ገድላት ውስጥ ይኸው ጽንሰ ሐሳብ በምን ዓይነትና ደረጃ እንደተንጸባረቀ ለመረዳት ይጠቅማል።
- ትምሕርት ክፍሉ በጥንታዊ ሥነጽሑፍ ትምህርትና ጥናት ላይ ለሚኖረው ድርሻ የገድላት ጥናት እስከምን ደረጃ መጠናት እንዳለባቸው በማመላከት በኩል ድርሻ ይኖረዋል።
- ገድላት እንደ ሥነጽሑፋዊ ሀብት ከአንድ ወይም ከብዙ ማኅበረሰብ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ርእዮተ ዓለማዊ ጉዳዮችን በያዟቸው መባያዎች /motifs/፣ ትእምርቶች /symbols/፣ በገድላቱ ትረካዎች፣ በሁነቶች፣ በድርጊትና በንግግሮች አማካኝነት እንደሚያስተጋቡ ለመረዳት ይጠቅማል።

1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በተመረጡ ሦስት ገድላት ማለትም በገድለ ላሊበላ፣ በገድለ አብርሃ ወአጽብሐ እና በገድለ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ላይ ብቻ ይካሔዳል። ለዚህም በሚት ጥናት ረገድ አንቱ ከተባሉ ንድፈ ሐሳባውያን በተለይም በጆሴፍ ካምቤልና በዴቪድ ሌሚንግ በሚያነሧቸው የተጋዳሊ ሚት ጽንሰ ሐሳቦች መሠረት ገድላቱ የሚገለጹበትን ደረጃና ማኅበረሰቡ በእነዚህ ሃይማኖታዊ ተረኮች ውስጥ ራሱን የተመረጠ ለሚያደርግበት ርእዮተ ዓለማዊ አካሔድ እንዴት መሣሪያ ሆነው እንደሚያገለግሉ በውስጣቸው ያሉ ትእምርቶችንና መባያዎችን መተንተን ላይ ያተኩራል።

1.7 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የሚከናወነው በጽሑፍ አሐድ /text/ ላይ በመሆኑ የጥናት ሂደቱ የመስክ ሥራ ሳይኖረው በዋናነት የሚካሔደው በቤተመጻሕፍት በሚከናወኑ ንባቦች ነው። የሚጠኑትንና ለማጥናት የሚጠቅሙ የንድፈ ሐሳብ መጻሕፍትን መምረጥ የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ጥናቱ በገድላት ላይ የሚከናወን በመሆኑ ተፈላጊ ገድሎችን መለየት አስፈላጊ ነበር።

ገድላት በጾታ ደረጃ ለሴትና ለወንድ ቅዱሳንና ቅዱሳት ተጽፈዋል፡፡ በማኅበራዊ መደብ ለካህናቱና ለነገሥታቱ ተጽፈዋል፡፡ በአገልግሎት መዓርግ ለሊቀጳጳስ፣ ለቆሞሳትም ተጽፈዋል፡፡ በጋብቻ ሁኔታ ላላገቡ መነኮሳት፣ ላገቡ መዓስባን፡ በዕውቀት ደረጃም ለተማሩ ሊቃውንት ላልተማሩ መሐይምናን ተጽፏል፡፡ በአኗኗርም በአንድነት ለሚኖሩ አበው መነኮሳት፣ ተለይተው ለሚኖሩ ባሕታውያን ተጽፈዋል፡፡

ስለዚህ በገድላት መረጣ እንዲጠኑ እኔ የመረጥኳቸው በዋናነት የቅዱሳን ነገሥታትን ገድል ነው፡፡ ቢያንስ በሁለቱ የኢትዮጵያ ሥርወ መንግሥታት የታሪክ ዘመናት ውስጥ ካሉና ቅድስና መዓርግ አግኝተው ገድል ከተጻፈላቸው ነገሥታት የሁለቱን ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ ብዙ ጊዜዬን እነርሱን በመምረጥና በመፈለግ ወስጄአለሁ፡፡ የነገሥታቱንንና የጳጳሱን ገድላት ማጥናት የመረጥኩትም ጸሐፌ ገድሉና እርሱን ያበቀለው ማኅበረሰብ ለነገሥታትና ጳጳሳት ከሚሰጠው የከበሬታ ሥፍራ አንጻር ትርጉም ያለው ጥናት ይሆናል በሚል እምነት ነው፡፡

ከዚያም ተከትሎ ለእነርሱ ተነጻጻሪ የሚሆኑትን በተመሳሳይ የታሪክ ዐውድ የሚገኙ የጳጳሳት ገድል ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑና ጥናቱን ለመሥራት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው ከሌሎች ገድላት ጋር በማነጻጸር ቢቀርብ በመሆኑ በታሪክ ዘመን ተመሳሳይ ዐውድ ላይ ያሉ፣ በሚና ግን የተለዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት የወሰድኩባቸውን ተነጻጻሪ ገድላትም መምረጥ ያንንም መፈለግ ሌላው ጊዜ የወሰደ ሥራ ነው፡፡ ጥናቱ እንዲጠና የተፈለገው በዚህ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ መደቦች ላይ የተመሠረተ ንጽጽራዊ ዕይታም እንዲኖር በመሆኑ ያንን በማድረግ ጊዜ መውሰድ አግባብ ነበር፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት መዓርገ ቅድስናን ገንዘብ ያደረጉ ሁለት የነገሥታት ገድልና ለእነዚህም ሁለት የነገሥታት ገድላት ተነጻጻሪ የሆኑ ሌሎች ገድላት ስመርጥ በዓላማ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ባላቸው ሁለት ሥርወ መንግሥታት ውስጥ የነበሩ የሁለት ነገሥታትን ገድል መርጫለሁ፡፡ በተነጻጻሪ ያሉትንም ገድላት በዚሁ የታሪክ ዓውድ ውስጥ ጠብቀው እንዲሔዱ ለማድረግ ብጥርም ከአንዱ፣ በአክሱም ሥርወ መንግሥት ከሚገኘው አንድ የጳጳስ ገድል በስተቀር ሌላ ለጳጳሳት የተጻፈ ገድል ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዋናነት ትኩረት የማደርግባቸውን የነገሥታት ገድል ብቸኛ ሆኖ በስሙ ገድል ከተጻፈለት ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ገድል ጋር በማቆራኘት ማጥናት እንደሚቻል በማመን ጥናቴን አከናውኛለሁ፡፡ ከገድላቱ ሁለቱ ማለትም የሰላማ ከሳቴ ብርሃንና የላሊበላ ገድሎች ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው የታተሙ ናቸው፡፡ የአብርሃ ወአጽብሐ ገድል ግን ያልታተመና ያልተተረጎመ በመሆኑ ከግእዙ ቅጂ ወስዶ ማጥናት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በርእሱም እንደተጠቀሰው የትንታኔ አካሔዱ እያንዳንዱን ገድል ለማየት ገለጻዊ መንገድን የሚጠቀም ሲሆን የነገሥታቱን ገድል ከሌሎች ለማነጻጸር ግን በትንታኔው ንጽጽራዊ ዘዴን ይከተላል። ለዚህም በተመረጡት እያንዳንዳቸው ገድላት ያሉና በአብዛኛው የጋራቸው የሆኑ በገድላቱም ትኩረት ከተሰጣቸው መባያ ጉዳዮችን ለይቶ ይተነትናል። በእያንዳንዱ ገድል ያሉትን የመባያ ጉዳዮች ከተተነተኑ በኋላ ሦስቱን ገድላት በይዘታና በአተራረክ ያላቸውን ልዩነትና አንድነት በማነጻጸር ለማቅረብ ጥረት አድርጌያለሁ።

2. ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ደግሞ የገድላትን ሥነጽሑፋዊ ፋይዳ ለማጥናት ጥረት ካደረጉትና ከላይ አስቀድሜ ከጠቀስኳቸው በተለያየ ደረጃ ከተከናወኑ ጥናቶች መካከል በዚህ በእኔ ጥናት ውስጥ ቢከለሱ ይጠቅማሉ ያልኳቸውን ሁለት ጥናቶችን ብቻ እመለከታለሁ:: በመጨረሻም ከእኔ ጋር ያላቸውን ዝምድናና ልዩነት አስቀምጣለሁ::

ጸሐፊው ኤፍሬም እሸቴ፣ ርዕሱ Narrative Techniques of Three Selected Ethiopian Hgiographies፣ ቲሲሱ የተጻፈለት ትምህርት ክፍል፣ የውጭ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ሲሆን የተዘጋጀው ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ነው:: አጥኚው ያጠናቸውን ገድሎች የመረጠበትን መንገድ ሲገለጽ በኢትዮጵያ ካሉ ከ200 ያላነሱ ገድላት ውስጥ ባለታሪክ የሆኑት ቅዱሳን ከወጠ ብት የተለያዩ ማኅበረሰቦች /ከነገሥታት ቤተሰብ፣ ከሴት መናንያን፣ ከአበምኔቶች፣ ባህታውያን፣ ወዘተ. /አንጻር ወካይ የሆኑ የቅዱሳንን ገድል መምረጡን ይገልጻል:: የተከተለው የጥናት ዘዴም ለአተራረክ መዋቅር በዋናነት የቭላድሚር ፕሮፕን እይታ /Vladmir Propp's point of view ነው:: ለገጸባህርያት ድርጊትና ሚና ጥናቱ የጁሊያን ግሬሚያስ ሞዴልን /Julien Algirdas Gremias's Model የአተራረክ ጊዜን ለማጥናት ደግሞ የጀነቴ/Gennete እና የሬሞን ኬነን /Rimmon Kenan ንድፈ ሐሳብ ተከትሎ ማጥናቱን ጠቁሟል::

አጥኚው ትኩረት ሰጥቶ ለማየት የሞከራቸው ዕንሰ ሐሳቦች አራት ናቸው:: የአተራረክ መዋቅር ጊዜና የገጸባህርያቱ ተግባር፣ ምንነትና ይዞታ ናቸው:: ተረክ በውስጡ የሚይዛቸውን ዘሮች የተለያዩ ሊቃውንት ካቀረቧቸው ማብራሪያዎች አንጻር ልዩነትና አንድነታቸውን ያሳያል:: በተረኮች የሚካተቱትን ዘሮች አንዱን ካንዱ የሚለዩበት መሥፈርቶችን ያሳያል:: ለዚህም የባርተዝ/Barthes፣ የሚካኤል ቶለን /Michael Toolan፣ የስኮልስ /Scholes እና ኬሎግ/ Kellog እንዲሁም የቶዶሮቭ / Todorov ጽንሰ ሐሳቦች እየተነጻጸሩ ቀርበዋል::

የአተራረክ መዋቅርን በተመለከተም ምንነቱ ከቅርጽ/form/ ጋር ያለውን ልዩነት ለማሳየት የተጠቀመባቸውን የሊቃውንት ሐሳቦች በትንታኔ አቅርቧል:: በተለይም ገድላቱን ከዚሁ አንጻር ለመተንተን የመረጠውን የቭላድሚር ፕሮፕን እይታ እና የሮናልድ ባርስ እና የሲይምነር ቻትማን/Seymnor Chatman የሚከተሉትን Story Paraphrase እና Event Leveling የተባሉትን የጥናት ዘዴዎች/approches/ የተወሰኑ አመላካች ነጥቦች አቅርቧል:: ስለ ገጸባህርያት/characterization/ ባቀረበው የጽንሰ ሐሳብ ዳሰሳም ለገድላት ጥናት ቅርበትና ምቹነት አለው የሚለውን የጁሊያን ግሬሚያስ ሞዴልን በትኩረት አይቷል:: ይህ ዘዴ

ከገጸባህርያቱ ሰብእና ይልቅ ከድርጊትና ባህሪ ተዛምዶ አንጻር/action-character relation angle /ያያል። በተጨማሪም በገድላትም የሚታየው የገጸባህርያቱ ተግባር በመሆኑ የጄሊያን ግሬሚያስ ሞዴል ለዚህ ተመርጧል።

ስለአተራረክ ጊዜ ባቀረበበት ክፍል ደግሞ ስለጊዜ ሰዎች ያላቸውን ግንዛቤ ያስረዳል። ጊዜ በአተራረክ የመባያ ጉዳይ በመሆኑ ስለ ስለሚነገረው ነገር ጊዜ /Story-Time/ እና የአተራረክ ጊዜ /Text-Time / ምንነትምና ልዩነት ያስረዳል። ለዚህም የChristian Metz ሐሳብ ተብራርቷል። እነዚያን መነሻ አድርጎ የጸሐፍተ ገድላቱ ለአንድ ጉዳይ የሚሰጡት ጊዜ ከሌላው መለየቱ የራሱ ምክንያት አለው ይላል። ከዚያም የጀነቴ እና የሬሞን ኬነን ንድፈ ሐሳብን መነሻ አድርጎ ጊዜን የሚያጠናበት አንጻር የአቀማመጥ ሥርዓት/Order/ የቆይታ ጊዜ/Duration/ የድግግሞሽ መጠ ን/Frequency/ መሆኑን ያስቀምጣል። የእነርሱንም ምንነት በስፋት ያቀርባል።

ዋና ዋና ይዘቶች

የጥናቱ ዋና ዋና ይዘቶች ሲታዩም ጥናቱን የሠራው ከአተራረክ ቴክኒኮች አንጻር ሲሆን በተመረጡ ሦስት ገድሎች /ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ገድለ ገብረ ክርስቶስ፣ ገድለ ክርስቶስ ሰምራ/ ላይ ነው። ባነሣው የአተራረክ ቴክኒክ/Narrative Techniques/ ጥናትም በገድላቱ ያለውን የአተራረክ መዋቅር /Narrative Structure/፣ የአተራረክ ጊዜ /Narrative Time/፣ የገጸባህርያት ተግባርና ሚና/Characterization/ ላይ አተኩሮ ነው። ይህንንም በእያንዳንዱ ገድል ውስጥ በዝርዝር ለማየት የቻለ ሲሆን፤ የአተራረክ መዋቅርን ለማየት በየገድላቱ ያነሣቸው ዋናዎቹ የመባያ ጉዳዮች ትጋት /ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደትን/፤ ምልጃ /ለኃጥአንና በርግማን ላሉ ምሕረትን ለመለመን መቆም/፤ ተልእኮን መቀበል /ያላመኑትን ለማሳመን፣ ጠ ላቶችን ለማጥፋት/፤ መከራ መቀበል /በሰይጣን ጸር መፈተን/፤ ተአምራት /ከሕፃንነት ወራት አንሥቶ እስከ ፍጻሜ የተደረጉ ድንቅ ነገሮች፣ ከአራዊት ጋር መኖር፣ ፈውስ ወዘተ. / እና ቃልኪዳን /ያለውን፣ የሚመጣውንም ትውልድ ለማስማር የሚያስችል ጸጋ/ ናቸው።

የገጸ ባህርያትን ሚናና ተግባር በተመለከተም ጽንሰ ሐሳቦችን ባብራራበት የጥናቱ ክፍል የተጠ ቀሰውን የግሬሚያስ ሞዴልን መነሻ አድርጎ የታሪኩን ባለቤት/Subject/፣ ተራዳኢ/Helper/፣ ተገዳዳሪ/Opponent/ ልዕለ ተራዳኢ/Superhelper/፣ ለመያዝ ለማግኘት ዓላማ የተደረገው ነገር/Object/ ተቀባይ ወይም ተጠቃሚ /Receiver or Beneficiery/ ማን ወይም ምን እንደሆነ በየገድላቱ ተንትኗል።

የአተራረክ ጊዜን በተመለከተም ጽንሰ ሐሳቦችን ባብራራበት የጥናቱ ክፍል የጠቀሰውን የጀነቴ/Gennete እና የሬሞን ኬነን ያቀረቡትን የአተራረክ ጊዜ የሚጠናበትን አንጻር ማለትም

የአቀማመጥ ሥርዓት፣ የቆይታ ጊዜ፣ የድግግሞሽ መጠንን መነሻ አድርጎ እያንዳንዱን ገድል በዝርዝር አይቷል። በእነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች ያሉ ነጥቦችን እያነሣ በገድላቱ እንዴት እንደተገለጹ ያብራራል። በንድፈ ሐሳብ ትንተናው ያነሣቸውን ሐሳቦች ሁሉ በትንታኔው ሂደት ውስጥ በቀጥታ ሲጠቀምባቸው ይታያል።

ያስቀመጠው መደምደሚያም ሲታይ አጥኚው በሦስት ምዕራፎች የሠራቸውን የሦስት ገድላት የአተራረክ ቴክኒክ ሲያይ በዋናነት በአተራረክ መዋቅሩ፣ በገጸባህርያቱ ሚናና ተግባር፣ በአተራረክ ጊዜው ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ በአተራረክ መዋቅር ረገድ ሁነቶችና ድርጊቶች በገድላቱ የቀረቡበትን የአቀማመጥ ሥርዓት አይቷል። በአንዱ ገድል /ገብረመንፈስ ቅዱስ/ በክፍልና ምዕራፍ የቀረበ መሆኑን፣ በቀሪዎቹ ሁለቱ ግን በወራት ተከፍለው መቅረባቸውን አመልክቷል። በወራት ከተከፈሉት ገድሎች መካከል ደግሞ አንዱ /ገብረ ክርስቶስ/ ታሪኮቹ እንደተከሰቱበት የጊዜ ቅደም ተከተል በወራት የተቀመጡ መሆኑን፣ በገድለ ክርስቶስ ሰምራ ግን ታሪኮቹ ቅደም ተከተላቸውን ሳይጠብቁ ለየወራቱ ተበታትነው መቅረባቸውን አመልክቷል።

ሦስቱ ገድላት ባሏቸው የመባያ ጉዳዮች በተደጋጋሚ በሚታዩ ሁነቶችና ድርጊቶች የጋራ ባህርያት አሏቸው። በእነዚህ ሁነቶችና ድርጊቶች መጠን ግን አንዱ ገድል ከሌላው ቢለይም በሁሉም ገድል መኖራቸው ግን አያጠያይቅም። በእነዚህ ሦስት ገድላት የአተራረክ መዋቅር በዋናነትና በጋራ የሚከተሉትን አላባውያን/elements/ በሚከተለው አደራደር/arrangement/ ይዘዋል። ታሪኮቹ የተፈጸሙበትን ቦታና ጊዜ፣ ዘርአ ሙላድ፣ ምናኔ፣ ተጋድሎ፣ ቃልኪዳን፣ ዕረፍት /የነፍስ ከሥጋ መለየት/ ናቸው።

ገጸባህርያቱን/Characterization/ በተመለከተም የሁሉም የገድላቱ ታሪክ ባለቤቶች ቅዱሳኑ ናቸው። የእነርሱም ዋነኛ ተራዳኢዎች መላእክት ናቸው። ተገዳዳሪው ደግሞ ሰይጣን መሆኑ ተመልክቷል። ተጠቃሹ ልዕለ ተራዳኢ እግዚአብሔር ሲሆን፣ ክርስቶስ ወይም ቅድስት ሥላሴ እየተባለም በተለዋዋጭ መጠራቱን ጠቁሟል። የቅዱሳኑ ተጋድሎ የሚያጠነጥንበት ነገር ወይም ዓላማ/Object/ መንግሥተ ሰማይን መውረስና ለሰዎች ድኅነትን ማግኘት ናቸው። የቅዱሳኑ ተጋድሎ ተጠቃሚዎች ደግሞ ኃጥአን፣ አካላዊ ተግዳሮት የደረሰባቸው አካላት/the physically challenged/፣ ለቃልኪዳኑ መፈጸም የተቀመጠውን መመዘኛ ያሟላ ትውልድ፣ ቅዱሳኑም የሚሏምኑላቸው ሁሉ ናቸው።

የአተራረክ ጊዜን በተመለከተ ደግሞ ጸሐፍተ ገድላቱ ሁነቶችና ድርጊቶችን ያስቀመጡበት ሥርዓት የተለያየ ነው። በገድለ ገብረመንፈስ ቅዱስና ገብረ ክርስቶስ ታሪኮቹ የተፈጸሙበትን ጊዜ ቅደም ተከተል ጠብቀው የቀረቡ ሲሆን በክርስቶስ ሰምራ ግን ይህንን አይከተልም። የጊዜ

ቆይታን ስንመለከትም በክለሳ /summary/ የሚቀረቡ ታሪኮች እንዳሉ ሁሉ ሳይጠቀሱ የሚታለፉ ይኖራሉ፡፡ ቅዱሳኑ ለቤተሰብ ያላቸው ፍቅር፣ የልጅና የወላጅ ግንኙነት፣ የሚወዷቸውና የሚጠሏቸው ነገሮች በታ አልተሰጣቸውም፡፡ በገድላቱ ተደጋግመው የሚጠቀሱ የመባያ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ድርጊቶችና ሁነቶች ናቸው፡፡ እነሱም አንድ ዓይነት መነሻ/motivation/፣ ቅርጽ/form/ና ዓለማ ያላቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ገድላት ጠ ቃሚና ትርጉም ያላቸው የአተራረክ ቴክኒኮች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የተደረጉባቸው በመሆኑ የጸሐፍተ ገድላቱን የአተራረክ ብቃት ያሳያል ብሏል፡፡

ሌላው አጥኚ አራጌ ይመር ሲሆን የጥናት ርዕሱ ‹‹በአራት ገድሎች ላይ የተደረገ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ» የሚል ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ላይ ነው፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከኬኔዲ ፣ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ ከቋንቋዎች ጥናት ተቋም አብያተ መጻሕፍት ነው፡፡ መረጃዎቹ በገድል፣ በአፈታሪክና በሚት ላይ የተሰሩ የንድፈ ሐሳብ መጻሕፍት፣ የጥናትና የምርምር ስራዎች፣ ጆርናሎች እና ለሴሚናር የቀረቡ መጣጥፎች ናቸው፡፡ የትንተና አካሄዱም ንፅፅራዊ ዘዴን (Comparative method) የተከተለ ነው፡፡ አራቱን ዐውደ ንባቦች በማወዳደርና በማነፃፀርም ተንትኗል፡፡

አጥኚው ያብራራቸው ፅንሰ ሐሳቦች ሚት፣ አፈታሪክ እና ገድል ናቸው፡፡ እነዚህን ሦስት ፅንሰ ሐሳቦች አብራርቷል፡፡ በተጨማሪም «ገድልና የባህል ዓለም» በሚል ርዕስ ሐራ ድንግል፣ እስትንፋሰ ክርስቶስ፣ ወለተጴጥሮስ እና ፍቅርተ ክርስቶስ በክርስትናው የባህል ዓለም ውስጥ ሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ታሪክ የሚተረክባቸው ተጋዳሊያን መሆናቸውን ጠቅሶ የክርስትና ሃይማኖት ድኅነትን ማዕከል ያደረገ ሲሆን ከኦሪት ይልቅ ወደ ሐዲስ ኪዳኑ እንደሚያይል በመጥቀስ አስረድቷል፡፡ «የተጋድሎ ሂደቶች» በተባለው ርዕሱም የካምቤል የተጋድሎ ሂደቶችን የገለጸበትን ሐሳብ ወስዶ፣ እያንዳንዳቸውን እንደቅደም ተከተላቸው ጎርየት፣ ምናኔ፣ ትንሣኤ በሚል የአማርኛ ትርጓሜ ሰጥቶ ለእያንዳንዱ ፅንሰ ሐሳብ ማብራሪያ አቅርቧል፡፡

ዋና ዋና ይዘቶች

ዋና ዋና ይዘቶቹ ሲታዩም ጥናቱን የሠራው በአቡነ ሐራ ድንግል፣ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ፣ ወለተ ጴጥሮስና ፍቅርተ ክርስቶስ ገድላት ላይ ነው፡፡ አጥኚው «ሃይማኖት ለአንድ የተለየ ነገር መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላልን?» የሚለውን የተሲቺን አባባል ቃል በቃል ወስዶ ነው ወደ ዋና ተግባሩ የተንደረደረው፡፡

አራት ቁም ነገሮችን ዴርሱልጣን፣ ባዕዶቹ፣ ወተቱ እንዳይጎድል ጥጃውም እንዳይሞትና ሴት እኮ ናት የተባሉ አንኳር ጉዳዮችን በመያዝ የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ በኢትዮጵያ ዐውድ እንዴት እንደሚገለፅ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡

1. ዴርሡልጣን፡- ዴርሱልጣን የአማርኛ ትርጓሜው በንጉሥ የተሰጠ ቦታ ማለት እንደሆነ ተመራማሪው በመግለጽ ንጉሥ ሰለሞን ለንግሥተ ሳባ በምድረ እስራኤል ውስጥ የሰጣት ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያዊያን ዴርሡልጣንን በቦታነት ብቻ ሳይሆን የሚያዩት «ርስቱ የሰጠውን የባለቤትነት ስልጣን ነው፡፡» በማለት አመጣጡን ጭምር ተንትኗል፡፡

እንደ ተመራማሪው ጥናት ዴርሡልጣን የነፍስና የሥጋ ጉዳይ ነው፡፡ ሥልጣናቸው ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው ማስረገጫ፣ ኢትዮጵያውያን የተመረጡ ሕዝቦች ለመሆናቸው ምስክር፣ መሬታቸውም የእግዚአብሔር አገር፣ ሃይማኖታቸውም እግዚአብሔር የመረጠው ሃይማኖት መሆኑን ማሳያ ጭምር ነው፡፡ ገድላቱም ተጋዳሊያኑ እስራኤላዊ የመሆን ፍላጎት እንዳላቸው እና ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን እስራኤል ጭምር መሆኗን፣ ሕዝቦቿም ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆኑ እስራኤላውያን እንደሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍቱ ማረጋገጣቸውንና ለዚህ ወራሽነታቸውም ማሳያ ዴርሱልጣን መሆኑን ተንትኗል፡፡

2. ባዕዶቹ፡- በዚህ ክፍል የተመራማሪው ትኩረት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከስቶ የነበረውን የሃይማኖት ጦርነት እና የጦርነቱ ሰበብ ሱስንዮስ ቀዳሚቷን የእስክንድርያ ሃይማኖት አስወግዶ የረከሰች ያሏትን የካቶሊክ ሃይማኖት ማቋቋሙ መሆኑን ገልጿል፡፡ ባዕድ የተባሉትም ነባሩን የእስክንድርያ ሃይማኖት ያሳደደው የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮቹ (ሮማዎች) ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት ተጋዳሊያኑ ስለክርስቶስ ፍቅር ደማቸውን ማፍሰስ ስለሚፈልጉ ከንጉሡ የሚደርስባቸው ማስፈራራት ሃይማኖታቸውን ለማስቀየር ሳይሆን ለሰማዕትነት እንደሚገፋፋቸውና ሰማዕት እንደሚሆኑ አብራርቷል፡፡ በተጨማሪም ተጋዳሊያኑ ባዕዶቹን እኛ ትክክል ነን እናንተ ተሳስታችኋል፣ እኛ የክርስቶስ ቤተሰቦች ስንሆን እናንተ የሰይጣን ቤተሰቦች ናችሁ በማለት አባባሉን ለፓለቲካ ቅስቀሳ በመጠቀም አትምጡብን ብቻችንን እናስተዳድር በማለት በራቸውን መዝጋት ይፈልጉ እንደነበር ተንትኗል፡፡

3. ወተቱ እንዳይጎድል ጥጃውም እንዳይሞት፡- በዚህ ክፍል አጥኚው የሀዲስ አለማየሁን አባባል ላነሣው ጉዳይ መጠሪያ በማድረግ ተገልግሎበታል፡፡ ለሴቶቹ ተጋዳሊያን ገድል ተጽፎላቸዋል፡፡ ነገር ግን ተመራማሪው ከወንዶቹ ገድል ጋር አነፃፅሮ ሲያጠናው እዚህ ግባ የማይባል ሲሆንበት የተጠቀመው አባባል ይመስላል፡፡ የሴቶች ተጋዳሊያንን ገድል የሚጽፉ ሰዎች የሴቶቹን ገድላት ሲጽፉ ከሴቷ አንፃር አይተው አደረገች ከማለት ይልቅ ተደረገላት ማለት ያበዛሉ፡፡ «ገድሉ»

የበቀለበት እና የሃይማኖቱ ባለቤት በሆነው ማኅበረሰብ ባህል ተፅዕኖ ሥር በመሆኑ፣ ባህሉ ስለ ሚፈቅድላቸውና ስለሚነፍጋቸው ጉዳዩች በገድሎቹ ላይ መንፀባረቁ የግድ መሆኑን እና ሴት ተጋድሊያን እንደ ተጋዳሊነታቸው ይተገብሯቸዋል ተብሎ የሚጠበቀውን ጉዳይ በሙሉ ተግብረዋል ብሎ ለመተረክ የባህሉ ፈቃድ ወሳኝ በመሆኑ፣ ባህሉ የነፈጋትን ተግባር አላብሶ መስጠት በጉድሉ ላይም እንዳልተቻለና ሴቶች ቅዱሳን ላይ የሚቀርቡ አንዳንድ አምንታዊ ጥቅሶች ያለተግባር ለይሰሙላ እንደሚቀርቡ አጥኚው በምሳሌ እያስደገፈ አብራርቷል። ተመራማሪው የሴቶቹንና የወንዶቹን ገድል ንፅፅር በሠንጠረዥ አሳይቷል። በክፍሉ ርዕስ የተነሣበትን ዓላማ አጠንክሮ የሚያስረዳ ሠንጠረዥ አቅርቧል። በሴቶቹ ገድላት ላይ በማጀት ውስጥ የሚያተኩር ገድልና ተአምር ሲሆን፣ በወንዶቹ ገድላት ላይ በሽተኛን ከመፈወስ እና ሙታንን ከማስነሣት ጋር የተያያዙ ገድላት እና ተአምራት በብዛት እንደሚታዩ ገልጿል።

4. ሴት እኮ ናት፡- አጥኚው ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን የበላይነት ያሳዩልኛል ያላቸውን ምሳሌዎች በማንሳት በአስረጂነት አቅርቧል። ሴትነት ለራሱ ብያኔ እንዲሰጥ በማድረግ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን ትልቅነት በራሳቸው በሴቶች እንዲቀነቀን የሴቶች ያልሆነ ንግግር በማስነገር ሥልጣናቸውን እንዳረጋገጡ ተንትኗል። ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖቱ ባህሉ የኮነነውን የሚኮንን፣ ያወገዘውን የሚያወግዝ፣ ባህሉ ለወንድና ለሴት የደነገገውን ሥራና ተግባር የሚያፀና፣ ለባህሉ ታማኝ በመሆኑ ሴቶች በባህሉ የተነፈጉትን ነገር በሙሉ ሃይማኖቱም ነፍጓቸዋል ብሏል።

አጥኚው አራት ቁምነገሮችን በማንሣት ትንታኔ እንደሰጠ ሁሉ መደምደሚያውም እነዚህን የጥናቱን ዋና ዋና ጉዳዩች መሠረት ያደረገ ነው።

ተጋዳሊያኑ እንደ አይሁድ የዘር ሐረግ ይቆጥራሉ። ኃያላኑ ከእስራኤላውያን ወገን እንደሆኑም ያምናሉ። የእስራኤላዊነት መለዮ ፍለጋው ሃይማኖታዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ስልት ነው። የሰለሞንና ሳባን አፈታሪክ በመጠቀም የገድሎቹ ተራኪዎች ይህን ሀገራዊ ተረክ ሃይማኖት አስመስለው ፖለቲካውን የሃይማኖት ጉዳይ በማድረግ መልሰው ለፖለቲካ ማጠየቂያነት አውለውታል። የአፈታሪኩ መፈጠር ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያውያንን የእስራኤላውያን ወገኖች በማድረግ የእስራኤላውያንን ማንነት የራሳቸው ማድረግ ነው በማለት ድምዳሜውን ሰጥቷል።

በንጉሥ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በሮማ ካቶሊክ እና በእስክንድርያ ተዋሕዶ ሃይማኖት መካከል የርዕዮተ ዓለም ክርክር ተነሥቶ ነበር። ክርክሩ ከሮ ወደ ጦርነት ገብተው ነበር። ተጋዳሊያኑ በዚህ ወቅት የተጠቀሙት ስልት ፖለቲካውን የሃይማኖት ጉዳይ በማድረግ ትክክለኛ

ዋ ሃይማኖት የእኛ ናት በማለት አትምጡብን፣ ብቻችን እንገዛ፣ እናስተዳድር የሚል የመከላከል ስልት ይጠቀማሉ ብሏል፡፡

ገድሎቹ ለተጠሩበት ማኅበረሰብ ባህል ተገዢ ናቸው፡፡ በሰበካው ሲታዩ ዐውደ ንባቦቹ የሃይማኖት ናቸው፣ በመንግስት እና በሃይማኖት ርዕዮተ ዓለም ሲታዩ በፖለቲካ የተሞሉ ናቸው በሚል ድምዳሜውን አሰረግጧል፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ጥናቶች በዚህ ክለሳ ድርሳን ቢቀርቡ የነበሩና ያሉ በገድላት ላይ የተሠሩ ጥናቶችን በተሻለ ወክለው መታየት የሚችሉና ከእኔ ጥናት አንጻርም ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ ከሦስቱ ጥናቶች መካከል ደግሞ የኤፍሬም ጥናት በዋናነት ቅርጽና መዋቅር ላይ ያተኮረ ቢሆንም ገድላት ላይ የተሠራ ሥነጽሑፋዊ ጥናት በመሆኑ በአንጻራዊ መልኩ ከእኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ቴክኒክ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ መሥራቱ አተራረክ ላይ ማለትም በትረካ በተራኪ በአተኩሮት በተረኮቹ ቅደም ተከተላዊ አደራደርና አደራደሮቹ ባላቸው ፋይዳ እንዲሁም የገጸባህርያቱ የተሳሉበት ሁኔታ ከሚያተኩረው ከእኔ ጥናት የተለየ ነው፡፡

የአራጌ ይመር ጥናት ግን ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ በመሆኑ በአጠቃላይ ከቅርጽ ውጪ በገድላቱ የተንጸባረቀውን ርእዮተዓለማዊ ማኅበራዊና ባህላዊ ተጽዕኖዎችን መተንተን ነው፡፡ ከእኔም ጥናት ጋር ዝምድና አለው፡፡ የእኔ ጥናት በማኅበረሰቡ ዘንድ በመዓርግ ከፍ ያለ ሥፍራ ያላቸውን ንጉሥና ጳጳስ ገድላት ላይ የተሠራ በመሆኑና በዚሁ አራጌ በሠራበት የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ ላይ ተመርኩዞ ቢሠራ የላቀ ትርጉም ሊኖረው ይችላል በሚል መሠራቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የእኔ ጥናት ከአራጌ ጥናት ጋር ተዳምሮ ቢታይ ገድላት በተጋዳልያኑ በኩል የማኅበረሰብን ርእዮተ ዓለማዊ ፍላጎት የሚያንጸባርቁበትን ደረጃ በጥልቅ መረዳት ይቻላል እላለሁ፡፡

2.2 የንድፈ ሐሳብ መሠረት

ገድላት ሃይማኖታዊ ተረኮች እንደመሆናቸው መጠን ሥነ ተረክ /Narratology/ ሊያጠናቸው ከሚገቡ ዘውጎች እንደ አንዱ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ተረክ በዝርው ወይም በግጥም ሊነገር የሚችል ገጸባህርያቱን፣ ገጸባህርያቱ የሚናገሩትንና የሚሠሩትን ሁሉ የያዘ ታሪክ ነው /Abrams,173/፡፡ በገድላትም ተጋዳልያን የተጋዳሊያኑ ግብርና ንግግር ገለጻዎችና ሁነቶች ይኖራሉ፡፡ ተረኮች የጽሑፍ ሥራዎች ብቻ አለመሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ሥዕል፣ ንግግር ወዘተ ተረክ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሬሞን ኬናን ሰትገልጽ እንዲህ ብላለች፡፡ «ጋዜጣ፣ ሪፖርቶች፣ የታሪክ መጻሕፍት፣ ረጅም ልቦለዶች፣ ፊልሞች፣ አስቂኝ ምስሎች፣ ድምፅ አልባ ተውኔት፣ የጭፈራ ክዋኔዎች፣ ሹክሹክታዎች፣ ሥነልቦናዊ ጨዋታዎች *በአኗኗራችን ውስጥ ከሠለጠኑ ተረኮች ጥቂቶቹ ናቸው*» (Rimmon-Kenan, 1983,1)[1]

ተረኮች በዋናነት እውነተኛና ልቦለዳዊ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በጎብረ ቀለማት/spectrum/ ውስጥ ቀለማት አንዳቸው ካንዳቸው ባላቸው ግንኙነት ተነጻጽረው ሊታዩ እንደሚችሉት ተረኮችንም ደግሞ በልዩነትና በተመሳስሎ በየንዑስ ክፍሎች ሊመደቡ ወይም ዘውግ ሊበጅላቸው ይችላሉ /The New Encyclopedia Britanica, 1991, 710/፡፡ ስለዚህ ተረኮች የተለያየ ገጽታ ያላቸው በመሆናቸው የተረኮች ጥናትም ተቋማዊ መልክ እየያዘ የተለያዩ ብያኔዎች እየሰጡ የሚያጠኑ አብያተ ኀልዮት/School of thought/ እንዲኖሩ አድርጓል፡፡

እኔ ለጥናቴ የመረጥኋቸው ገድላት ሃይማኖታዊ የተቀደሱ /sacred/ ተረኮች ናቸው፡፡ እንዲህ ያሉ ተረኮች ደግሞ በሚታዊ ተረኮች ውስጥ የሚፈረጁ ናቸው፡፡ ሚት ሲባልም በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ሲታይ እውነት ያልሆነ ወይም አስገራሚ የሆነ እምነት ወይም ግንዛቤ ነው፡፡ ባህሎችና ሃይማኖቶች የራሳቸው የሆነ የተቀደሰ ተረክ ይኖራቸዋል፡፡ ተረኮቹ ግን ከዚያ ማኅበረሰብ ባሻገር እንደ ሚት የሚታሰቡ /የሚቆጠሩ/ ይሆናሉ፡፡ ዴቪድ ሊሚንግ ይህንን ብቻ ሳይሆን ሚርሴ ኤልያድን /Eliade/ ጠቅሶ ሲናገር ሚት የሚባለው ነገር ለአማኞቹ እንደ "እውነተኛ ታሪክ" እንደሚታሰብ ይነግረናል፡፡ ለሌሎች ግን ሚት ነው፡፡ የነገረ ሚት ሊቃውንት የሚባሉት ካርል ዮንግ፣ ሚርሴ ኤልያዴ እና ጆሴፍ ካምቤል በበኩላቸው የተቀደሱ ተረኮች የምናብ ውጤቶች መሆናቸውን ያስረዳሉ /David Leeming, 2002, 9/፡፡

ሚት የአንድን ማኅበረሰብ ማንነት የምንረዳበት፣ የአንድን ወገን ወይም ባህል ሥነ-ልቦናዊ መሠረት የምናውቅበት ነው፡፡ ሚት ከህልም ጋር ተነጻጽሮ ይታያል፡፡ ሕልሞች ስለራሳችን ማንነት መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ይህም ጥሬና በንቁ አእምሮ የመከላከል ስልት ያልተበረዘ እውነተኛ ማንነታችንን የሚያሳይ ነው፡፡ ሚትም ለባህሎች ይህንኑ የሚያደርግ ነው፡፡ ካምቤልና

ዩንግን ጠቅሶ የሚነግረን ዴቪድ ሌሚንግ ይህንኑ ሲያብረራ ሚቶች በተለይም የራሳችን የሆኑትና ያለፈውን ባህል ይዞታና መነሻ ያለቀቁ ሲሆኑ የራሳችንን ዕውቀትና ማንነት የምንረዳባቸው ይሆናሉ፡፡ እነዚህም ያልተነካኩ ስሞቻችንን፣ ቅድመ ትውልዳችንን እና አካባቢያዊ ገጽታዎቻችንን ለትውልዳችን ያሸጋገሩልን ናቸው ይላል /ዝኒ ከማሁ፣ 10/፡፡

ሁሉን አቀፍ ምልከታ ያላቸው /Universalists/ም ሆኑ ንጽጽራዊ ምልከታ ያላቸው/Comparatists/ ሚትን የእውነታ ማጓጓዣ ሠረገላ አድርገው ያዩታል፡፡ ስለዚህ የሚትን ሁሉን አቀፋዊ ቋንቋ እና አርኬታይፕ /ጥንተ መልክእ/ ለመረዳት ከተፈለገ የአንድን ሰው ሕልም ለመፍታት የግለሰቡን ልምድና ዕውቀት መረዳት እንደሚያስፈልገው ሁሉ የዚያን ሚት ባለቤት የባህል ልምድና ዕውቀት ይጠይቃል /ዝኒ ከማሁ፣14/፡፡

በሁሉም ቦታ፣ በሁሉም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሚት ሊመነጭ ይችላል፡፡ ከሰብአዊ ፍጡር የአእምሮና የአካል ተግባር መንጭቶ የሚገለጽም ነው፡፡ ከዚያም በማኅበረሰብ ባህል ውስጥ የሚገለጽ ነው፡፡ ስለዚህ ሃይማኖትን ጨምሮ ፍልስፍና፣ ሥነ ጥበብ፣ በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የነበሩ ማኅበራዊ ቅርጾች፣ ቅድምና ያላቸው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ከዚሁ ከሚት መሠረት የሚፈልቁ ናቸው /Campbell,1948, 3/፡፡

በዓለም ላይ በተለያዩ ቦታዎች ያሉ ሚቶች በአንድ ጊዜ ተመሳሳይ ጭብጦች ይዘው ሊገኙም ይችላሉ፡፡ በንጽጽር የሚጠናው የአርኬታይፓዊ ሁኔታ እንደሚያሳየው የሥነ ፍጥረት፣ ነገረ ዓለመ ሙታን፣ የነገረ መለኮት እሳቤ፣ የተጋዳሊነት ጥያቄ እንደ አንድ ጭብጥ የሚመነጨት ከሁሉን አቀፍ ሥነ አእምሮአዊ ዝንባሌ /Universal Psychic Tendency/ ነው፡፡ ሚቶሎጂዎች ሁሉ ሰብአዊ ሕልሞችና ዩንግ የጋርዮሽ ደመ ነፍሳዊ ሐሳብ "Collective Unconcious" ብሎ የሚጠራው ነገር ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ አርኬታይፓዊ ገጽታዎች /images/ የአጠቃላዩ ዓለም ትእምርታዊ ቋንቋ ሆነዋል፡፡ በእነዚህም የሕይወትን ውስጣዊ ትርጉም፣ ራሱን እውነታንም ወደ መረዳት የሚያቀርብ ነው /David Leeming, 2002, 11/፡፡ ለምሳሌ ስለ ትንሣኤ ያለውን እውነት ስለ ኢየሱስ በሚነገሩ ተረኮች ውስጥ እንደምናገኝ ሁሉ የኦስሪስን /Osiris/ ወይም ፐርሴፎን /Persephone/ ተረክ ውስጥም እናገኛለን፡፡ ይህንን በእምነት ዘውግ ወይም በአካባቢ ሁኔታ ሳይገደብ በንጽጽር ቢታይ ለዚህ ማሳያ የሚያርፈው ትንሣኤ በሚለው ሐሳብ ላይ እንጂ የሚነሣው አካል ማንነት ላይ አይደለም፡፡ ትንሣኤ በድንግልና መውለድ የመሳሰሉ ጉዳዮች እንደ ትእምርት የሚታዩ ናቸው፡፡ ትእምርቶች ደግሞ በራሳቸው እውነታ/Truth/ ባይሆኑም ጎሊናን ወደ እውነታ ይወስዳሉ፡፡

የተቀደሱ ሃይማኖታዊ ተረኮችም በዚህ የተሞሉ ናቸው፡፡ እኔም የማጠናቸው ገድላትም በውስጣቸው ባሉ በጉልህ በሚታዩ ትእምርቶች ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ባህላዊ እውነታዎችን ያንጸባርቃሉ፡፡ ይህንን እውነታ ለመረዳት በየገድላቱ ያለውን ይዘት በጥልቅ መርምሮ በንጽጽር አንዱን ከአንዱ በማስተያየት ከሃይማኖታዊ ሐሳቦቻቸው ባሻገር ምን እያሉን እንደሆነ ለመረዳት ይቻለናል፡፡

ሃይማኖተኞች የእነዚህን የእምነት ተረኮች ታሪካዊና ነጠላ /Literal/ ይዞታ ላይ በማተኮር ይሰብኳቸዋል፡፡ ሥነ ሚት ደግሞ የሚቶቹ ትእምርታዊ እውነት ላይ በማተኮር ተጠየቃዊ ጥናት ያደርጋል፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው መንታ ሐሳብ /Dilemma/ በዓለም ያለውን የዕለት ዕለት ልምድን መሠረት አድርጐ በሚያየው በሳይንሳዊና ተጠየቃዊ ቅኝትና ሚታዊና ሥነ አምልኳዊ /Ritualistic/ ማዕከል ባደረገው ሃይማኖታዊ ትውፊት መካከል ያደገ ነው /ዝኒ ከማሁ፣ 12/፡፡

ሃይማኖታዊው መልክ በአብያተ መቅደስ በሥነ አምልኮ ውስጥ በአካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ሥፍራ /Space/ ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ቅዱስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም ፍፁም በዓለም ካለው ነባራዊ እውነታ የተለየ ነው፡፡ ነገር ግን በዚሁ ሃይማኖታዊ ነገር ውስጥ ከሕይወት በስተጀርባ ስላለ ምስጢር እናስባለን፤ የምናስበውንና የምንናገረውንም እንዘምራለን፤ ሚታዊ የሆኑ ቅድመ ትውልዶቻችንን ለመምሰል እንጥራለን፣ አልባሳት ለብሰን የአመክንዮ ሕግ ቅሚቀበለው ውጪ በሆነ በአንዳች ሁነት ውስጥ እናከብረዋለን፡፡ ዋናው ነጥብ ግን ሁሉም ባህሎች በልዩነቶቻቸው ውስጥ አንድ የሚያደርጋቸው ያልታወቀውን ነገር በመመርመር ሂደት ውስጥ በሃይማኖታቸው እና በሚቶሎጂያዊ ሂደቶች /Mythological process/ ውስጥ ይገናኛሉ /ዝኒ ከማሁ፣15/፡፡

የሚቶሎጂ ጥናት ደግሞ የሚት መባያዎች የሚጠኑበት፣ ባህላዊ ወይም የጋርዮሽ /Collective/ ሚቶችን የሚበየኑበት /የሚተረጎሙበት/፣ ስለ ራስ ማንነትና ስለ ውስጣዊ ስሜታችን ያለንን ሰብአዊ ጥያቄን ለመመለስ ጥቅም ላይ የዋሉ ሚቶችን ይዞታ ያንንም ለመግለጽ /"ታሪክ ለመንገር"/ ሰዎች የተጠቀሙባቸውን የነበሩ /የተሠሩ/ ዘይቤያዊ መገለጫዎች /Methaphor/ የሚጠኑበት ነው፡፡

የእኔ ሐሳብ እኔም በማጠናቸው ገድላት ያሉ መባያዎች ሲመረመሩ ገድላቱን ያበቀለውን ማኅበረሰብ ስለራሱ ማንነት ያለውን እሳቤ ለራሱ የሰጠውን ዋጋና ቦታ ጥልቅ ስሜትና

ፍላጎቶቹን ያንጸባርቃሉ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ያንን የሚነግርበት ዘይቤ በእነዚህ ሚታዊና አፈታሪካዊ ተረኮች ውስጥ አሉት የሚል ነው፡፡

ሚቶች በጋርዮሽ ምናብ የሚፈጠሩና ነገሮች በሕይወት ውስጥ ያሉበትን /የሆነበትን/ መንገድ ለመግለጽ እንደ ዘይቤ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህም እውነታን የምናውቅበት ልምድ፣ ያንን ልምድ በሚያስመስሉ /mimetic/ ታሪኮችና ግንዛቤዎች ለማልበስ ካለን ከእኛ ተፈጥሯዊ ፍላጐት የተነሣ የሚመጡ ናቸው፡፡ ልምዶቻችን የባህላችን አንድ ዘር ወደ መሆን ይለወጣሉ፡፡ ካሉን ከነበሩን ቁሳዊ /ነባራዊ/ አኗኗር እንወጣና እንዳሉ እንደነበሩ ሆነው ከአጠቃላይ የህላዋ /existence/ ገጽታ ጋር እየተዛመዱ ጥንታዊ ሚቶች እና ተዛማጅ የአምልኮ ሥርዓቶች ወደ መሆን ያድጋሉ፤ አዳዲሶችም ይወለዳሉ፡፡

የእነዚህ የተቀደሱ ተረኮች ተርጓሚ ሃይማኖት በመሆኑ እነዚህን ሚቶች ለመግለጽ፣ ለማስተዋወቅ ለማጽናት ለማስረግም አሁንም ሃይማኖት የአምልኮ ሥርዓቶች ያዘጋጃል፡፡ ከዚያም ተሻግሮ ተቋማዊ መሠረት ይይዛል፡፡

ይህንን ተቋማዊነቱን ተጠቅሞ ደግሞ ከሃይማኖት ዓለም ውጪ የሆኑ ፖለቲካን ለመሰሉ ጉዳዮች አገልግሎት ሊ ሰጥ ይች ላል፡፡ ዴ ቪድ ሌሚን ግ ስለዚ ህ ሲ ጽፍ እንዲህ ብሏ ል፡፡ ‹‹ሃይማኖት ተቋማዊ እንደመሆኑና ከዓለማዊው የፖለቲካ ሰልፍ ጋር እንደማበሩ እነዚህ የጋርዮሽ የተቀደሱ ዘይቤዎች /ሜታፊሮች/ እና ራሱ ሃይማኖትም ለራሱ ጥቅምና ለፖለቲካ ዓላማ ይቆነጻጸላሉ›› /David Leeming, 2002, 19/ [11]

ስለዚህ ሃይማኖት በራሱ ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ በተቃራኒ ኃይላት መካከል ትግል መኖሩን የሚያንጸባርቅ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሃይማኖታዊ ተረኮች ከፖለቲካም ሌላ ለጾታዊ ክርክር፣ ለዘር ልዕልና ክርክር፣ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ሁሉ ሊውል ይችላል፡፡ ሃይማኖት ያሉትን ሚቶች ለመቀሰጥ /Perversion/ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ሌሎች መገለጦችን /revelation/ ለመጨቆን ሊጠቅም ይችላል፡፡ የያዘውን ሊያጸና ዛሬ የሚወለዱትን ሊጨቁን ይነሣል፡፡ ሚት ደግሞ በየጊዜው የምናብ ውጤት ሆኖ በተጸነሰ ጊዜ ሁሉ ተቋማዊ የሆነው ሃይማኖት ካስወረደው /abort/ የግለሰቦችን አእምሯዊ፣ የባህሎችን ልማት፣ የዕውቀት አድማስን ማስፋት ይቃወማልና ከሚት ጋር ተቃርኖ ውስጥ ይወድቃል /ዝኒ ከማሁ፣ 20/፡፡

እነዚህ ሚታዊ ሃይማኖታዊ ተረኮች ለየትኛውም ዓይነት የማኅበረሰብ ዓላማ ቢውሉም በሚያነሡት ሃይማኖታዊ ጉዳይ በዓይነት በዓይነት ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ዛሬ በምናስብና በምንናገረው በምናደርገውም ነገር ሁሉ ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸውን የቀጠሉ በሰብአዊ

ማኅበረሰቡ ውስጥ ማዕከል ሆነው ያሉ ሦስት ዓይነት ዋና ዋና የሚት ዓይነቶች መኖራቸውን ዴቪድ ሌሚንግ ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያው የሥነ ፍጥረት /ዘርያ/ ሚት ሲሆን ከየት መጣን፣ ነገሮች እንዴት ጀመሩ /ተጀመሩ/ የሚለውን የሚነግረን ነው፡፡ ሁለተኛው የአማልክት ሚት፡ ደግሞ ከሥነ ፍጥረት ሚት ጋር ተዛማጅ ሆኖ ለእኛ ብቸኛ አስገኚዎች /Ultimate Progenitors/ ያለንን ዘይቤያዊ መገለጫ ወይም ያለንን ህልም የሚነግር ነው፡፡ ነገረ ተጋዳሊ /Hero myth/ ደግሞ በአብዛኛው ሰብአዊ ሆኖ በገናናውም ሥነ ልቦናዊ ቅርጽ ያለው ሦስተኛው ዓይነት ሚት ነው፡፡ የነገረ ተጋዳሊ ተረኮች ለእኛ በሕይወትና በታሪክ ውስጥ ለነበረን ግላዊና የጋርዮሽ ዕድገት እንደ ዘይቤያዊ መገለጫ ሆነው የሚነገሩ ናቸው፡፡

የእኔም ጥናት በዚሁ በነገረ ተጋዳሊ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከሦስቱ ዋና ዋና የሚት ዓይነቶች የተጋዳሊ ሚትን መሠረታዊ አሳቤዎች ላንሣ፡፡ ካምቤል እና ሌሚንግ በተባሉት ሁለት የሚቶሎጂ ሊቃውንት መጻሕፍት ላይ ተመሥርቶ መጣጥፎቹን እንዳዘጋጀ የሚነግረን ቴዎድሮስ ገብሬ ስለሚት፣ ተጋዳሊና ተጋድሎ ባቀረበው ገለጻ "ሁሉም ባህል የግል ማንነቱን የሚገልጽባቸው፣ የጋራ ራእዩን የሚቀምርባቸው፣ ልዕለ ተፈጥሯዊና ልዕለ ሰብአዊ ሁነቶችን የሚያትትባቸው ሃይማኖታዊና ዓለማዊ አለበለዚያም ያሁለቱም ድብልቅ ተጋዳሊያን አሉት›› ይለናል /ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 43/ በማለት ያትታል፡፡ እነዚህ ተጋዳሊያን በአንድ በኩል ሥግዋን አማልእክት ሊሆኑ ሲችሉ በሌላ አንጻር ደግሞ በአማልእክት የተቀቡ /የተሾሙ/ ሃይማኖታዊ ተልእኮ ያላቸው ተጋዳሊያን ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ ግን ሃይማኖታዊ ያልሆነ ሌላ ዓለማዊ የሆኑ ተአምራዊ ተግባራትን የሚፈጽሙ ተጋዳሊያን አሉ፡፡ ሁሉም ግን ተጋዳሊ አድርገ የቆጠራቸውን ማኅበረሰብ ፍላጎት የመፈጸም፣ የማስፈጸም ድርሻ ይዘው ይታያሉ፡፡ አንዳንዶቹ የእስራኤል ታዳጊ እንደነበረው እንደ ሙሴ የአንድ የተወሰነ ወገን አካባቢ ወይም ነገድ ጎሳ ተጋዳሊ፣ ሌሎች ደግሞ መድኃኔዓለም እንደተባለው እንደ ኢየሱስ ሁሉን አቀፍ ተጋዳሊ ሆነው ይታያሉ፡፡ ከምንም በላይ ማኅበረሰቡ ያሉበትን አንዳች ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ሌሎች ቀውሶች በነገሡበት ሁኔታ ውስጥ ተወልዶ አድጎ፣ ከአቋመ ማኅበሩ ተጋጭቶም ቢሆን ፈውስን፣ ዕረፍትን፣ ክብርን፣ ድኅነትን ወዘተ. የሚከስት ሆኖ ይገልጣል፡፡ ወደዚያ ለመድረስ ወይም ማኅበረሰቡን ለማድረስ ግን ከቅርብ ወይም ከሩቅ ተቃዋሚ በተጋዳሊው ላይ ይነሣል፡፡

ስለዚህም ሄሮድስ በኢየሱስ ላይ፣ ፈርኦን በሙሴ ላይ የደቀኑት ተግዳሮት ማሳያ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ከዚህ መአት ሲሰውራቸው፣ የሚያሸንፉበትን ኃይል

ሲያድላቸው፣ ከማሸነፍ አልፈው ጠላትን ሲቀስፉ መታየታቸው በዚያን ጊዜና ከዚያም በኋላ በቀሪው ዘመን ስለሚመጣው የተጋዳሊነት ዕጣ ፈንታቸው ጠቋሚ ይሆናል /ዝኒ ከማሁ፣ 44/፡፡

በእነዚህ ዓይነት ሚታዊ ተረኮች የየባህሉ ተጋዳሊዎችም ጊዜያቸው ደርሶ ለገድል ሲሰማሩ የሚያልፉባቸው ተደጋጋሚና ቋሚ ፈለጎች እንዳሉና አንድ ወጥ የሆነ ሚቶሎጂያዊ ሥርዓት /Monomyth/ እንደሚከተሉ ጆሴፍ ካምቤል ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ፈለጎችና ሚቶሎጂያዊ ሥርዓቶች አማካኝነት የተጋዲሊዎቹ ዕጣ ዞሮ ገጠም የሕይወት ዑደትን ተከትሎ እንደሚጓዝ ይነግረናል፡፡ ከወገን የመለየት፣ ወደ ሚጠበቅና የሚከለከል ሥፍራ የመዝለቅ በኋላም አንዳች በረከትን ይዞ የመመለስ /Separation, initiation, return/ ነገር ነው፡፡ ‹‹ተጋዳሊው ከሰርካዊው ዓለም ተለይቶ ወደፊት በመራመድ ወደ ልዕለ ተፈጥሮ ክልል ይዘልቃል፤ በዚያ ያሉ አንዳች ለዚህ ዓለም እንግዳ የሆኑ ኃይሎችም ይገዳደሩታል፤ ወሳኝ ድልም ይቀዳጃል፤ ተጋዳሊው ተመልሶ ከዚህ ምስጢራዊ ወይም ድንቅ ጉዞ ተከታዩን ሰው /ወገኑን/ በበረከት ከሚያትረፈርፍ ኃይል ጋር ይመለሳል፡፡›› /Campbell,1948, 30/[III]

እንደ ካምቤል ገለጻ ከምስራቃውያን እና ከጥንታውያን የግሪክ ተረኮች ጀምሮ እስከ መጽሐፍ ቅዱስ ተአምራዊና አፈታሪካዊ ተረኮች ድረስ ከላይ የተጠቀሰውን ፈለግ ተከትለው እንደሚቀርቡ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ ተረኮችም ከዚህ ቅንብብ ውጪ ሊወጡ እንደማይችሉ አስባለሁ፡፡ ተጋዳሊው ከአይሁድም ይሁን ከአሕዛብ፣ ግሪክም ይሁን ባርቤሪያን፣ ታላቅም ይሁን ታናሽ በመሠረታዊው የሚት ጉዞ ፈለግ ያለው ልዩነት እጅግ ጥቂት ነው፡፡ ሕዝባውያን ተረቶች የተጋዳሊውን እንቅስቃሴ አካላዊ አድርገው ቢስሉም ታላላቅ ሃይማኖቶች ደግሞ ተግባሩን ሞራላዊ ቢያደርጉትም በተጋድሎው ጉዞ ቅርጽ፣ በገጸባህርያቱ ሚና፣ በሚያገኙት ድሎች የሚኖረው ልዩነት በአብዛኛው ምንም ነው፡፡

ተረኮቹ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም ግላዊ ፍላጎት ወይም ዓላማ ቢኖራቸው በዚህ ፈለግ ውስጥ በሚያልፉ ተጋዳልያን አማካኝነት ሐሳባቸውን የሚያንጸባርቁ ይሆናል፡፡ እኔም በማጠናቸው ገድላት ያበቀላቸው ማኅበረሰብ ዓላማ ሃይማኖትም ይሁን ፖለቲካ በዚሁ ሂደት ወስጥ የሚያልፉ ተጋዳልያን አሏቸው፡፡

በጥሪ የተለየው ተጋዳሊ ለዓለሙና ለተከታዮቹ ዳግም ልደትን፣ ታላቅነትን፣ ታላቅ ኃይልን ያመጣ ዘንድ ስለዓለሙ ይሞታል ወይ መከራን ይቀበላል፡፡ ዘወትር የምናየውን ዘወትርም የሚገለጠውን ነገር ዳግም ለማየት በዚህ ፈለግ ውስጥ የሚያልፉ ብዙ ተጋዳልያን ይኖሩናል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ እነዚህን ገጽታዎች አሁን ላለ ዘመንኛ ሕይወት ያላቸውን ትርጉም

እንድናውቅ የሚረዳን ብቻ ሳይሆን የሰዎች የፍላጎት፣ የኃይልና ጥበብ መንፈስ እንድነትን እንድንገነዘብም እንደሚያግዝ ካምቤል ያብራራል /ዝኒ ከማሁ፣ 36-38/፡፡

በተለይ ከወገን መለየት በተባለው ደረጃ ተጋዳሊው ለገድሉ የሚለይበትን፣ የሚዘጋጅበት በሕልም፣ በራዕይ፣ በሆነ ትእምርት፣ ወይም በሌሎች በተመረጡ አካላት የሚመጣ ጥሪ ነው፡፡ ጥሪ ሲባል ተጋዳሊው ምናልባትም በትክክል በሚገባ አስቀድሞ ከማያውቃቸው ኃይሎች ጋር መገናኘት የሚጀምርበት ነው፡፡ ጥሪው በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ተጋዳሊውን ሊያሳምን የሚችል ሆኖ ልዕለ ተፈጥሮ ያሰመረውን መስመር ተከትሎ ተጋዳሊው ለገድሉ እንዲሰይ የሚያደርግ ነው፡፡ ተጋዳሊውን የበቀለበት ማኅበረሰብ ከሠራበት ውስጣዊ ማንነት ፈንቅሎ ወደሌላ ወደማያውቀው መንፈሳዊ አዲስ የስበት ኃይል ወዳለበት አቅጣጫ የሚያሸጋግረው ነው፡፡

የሚጠራበትም ሁኔታ በምድረበዳ፣ በጫካ፣ ከሰማያት በላይ ካለ ወይም ከምድር በታች በጥልቅ ካለ ግዛት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም እጅግ ከገዘፈ ተራራ ጫፍ ወይም ከምስጢራዊ ደሴት ወይም ያንን መሰረት ባደረገ ሕልም ውስጥ ይሆናል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን በጥሪው ሰዓት እንግዳ የሆኑ ክስተቶች ይታያሉ፡፡ ከዚያ ጥሪ በኋላ ተጋዳሊው ሰርካዊውን ዓለም የሚያይበት ዓይን ተለውጦ፣ ከራሱና፣ የዘወትራዊው ዓለም ተዋናይና ጠበቃ ከሆኑት ጋር ታግሎ አሸንፎ የሚታይበት የተጋድሎው መውጫ በር ነው /ዝኒ ከማሁ፣ 58/፡፡

የገድል ጥሪው ለተለያየ ዓላማ የሚፈጸም ሲሆን በተለይ በሃይማኖታዊ ተረኮች ለዚያው ለሃይማኖታዊ ተጋድሎ የሚደርሱ ጥሪዎች ናቸው፡፡ አስቀድሞ እንደተገለጸው ጥሪዎቹ ልብን የማሸፈት ኃይል ባላቸው ድባቦች ውስጥ በመከሰታቸው ወይም በመደጋገማቸው ወይም ተጋዳሊው ዕጣ ፈንታዬ ነው ብሎ በውል በመገንዘቡ ምክንያት ለጥሪው ጆሮ መንፈግ አይቻለውም፡፡ ከዚያ በኋላ "በልዕለ ተፈጥሮ ኃይሎች ጫና ገድሉን ለመፈጸም ወደ አንድ የማይታወቅ የሚፈራና የሚጠላ "ጨለማ ዓለም" ይዘልቃል" /ቴዎድሮስ፣2001፣ 13/፡፡

ብዙ ጊዜ የሚቶሎጂ ሊቃውንት የሚጠቅሱት በአይሁድ፣ በክርስትናና፣ በእስልምና ሃይማኖት ትርጉም ያለው ስለሙሴ ታሪክ የሚቀርቡ ተረኮች እነዚህን ሚቴሎጂያዊ ሥርዓቶች /ፈለጎች/ ለማሳየት አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ሙሴ ከሕፃንነት ዘመን የተመረጠ ሆኖ ከትልቁ የኤርትራ ባሕር ቢጣልም የባሕር ማዕበሉ፣ የማዕበሉም ውሽንፍር ደፍቆ ሳያጠፋው ኃይሉ ከባሕሩ ኃይል አይሎ መትረፉ፤ ወደ ባሕር እንዲጣል ምክንያት ባደረጉት ኃያላን ቤት ማደጉ አመላካች ሆኖ ቆይቷል፡፡ በሰና ሐመልማል ከነበልባል ሆኖ በተከሰተበት ራእዩ ከማያውቀው ኃይል ጋር

ግንኙነት ጀመረ፡፡ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ነጻ ለሚያወጣቸው ወገኖቹ ሁሉ ከማይታወቅ ኃይል የቀረበ ጥሪ በመሆኑ "የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁም ጊዜ ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?" /ዘጸ 3፡13/ ሲል የሙሴ ቃል ይደመጣል፡፡

ልዕለ ተፈጥሮ ግን በተጋዳሊው ፊት የሚከሰተው በነገር ሁሉ ጥሪውን ለመቀበል እንዳያቅማማ አድርጐ በመሆኑ በሙሴ እጅ ያለችው እባብም የምትሆነው በትር፣ ለምጽ የሚያለብስ ከለምጽም የሚነጻ ብብቱ፣ ከወንዝ የቀዳው ወደ መሬትም ያፈሰሰው ውሃ፣ ወደ ደም ያደረገው ውሳጤ ሁሉ ሙሴን ጥሪውን ለመቀበል አሻፈረኝ እንዲል ዕድል አይሰጡም፡፡ እስራኤልን ነጻ ለማውጣት፣ ከነዓንን ለመውረስ ተጋዳሊ አድርጐ ሲጠራው የተጠራበት ድባብ ሙሴን ያንን የገድል ጥሪ እምቢ ለማለት የሚያሰኘው አልነበረም፡፡ ያ ድባብ ሙሴን በእሽታ ገድሉን እንዲቀበል ከማድረግ አልፎ "ፈርዖን ሕዝቤን ልቀቅ" ብሎ የሚጠራበትን ቀዳሚ ትጽር ለመዝለቅ ጉልበትም ሆኖታል፡፡ ከጥሪው በኋላ የሚባለውን በፈርዖንና /ግብጻውያን/ የበላይነት በእስራኤል የበታችነት የተቋረጠውን ሠርካዊውን ዓለም የሚያይበት መነጽር ተለውጧል፡፡

በእርግጥ በተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ ተጋዳሊው ጥሪን ባለመቀበል /እምቢኝታ/ ጸንቶ የማይቀር ቢሆንም በትሕትና ምክንያት አልያም "ባይሆንልኝስ ባይሳካልኝስ" በሚል ፍርሃት ቀድሞ ያለመቀበል ድምፅ ሊያሰማ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አስቀድሜ በጠቀሰኳቸው ምክንያቶች እሺታው አይዘገይም፤ ካልሆነ ግን መቀሰፍ፣ መረገም፣ መኮነን አይቀሬ ይሆናል፡፡ ካምቤል ለዚህ ማሳያ አድርጎ ከመጽሐፈ ምሳሌ ያስቀመጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ላቅርብ፡፡

> ‹‹በጠራሁ ጊዜ አልሰማችሁኝምና እጄን ዘረጋሁ፤ ስለዚህ እኔ በጥፋታችሁ እስቃለሁ፤ ጥፋትም በመጣባችሁ ጊዜ ደስ ይለኛል፤ ጭቅጭቅ ድንገት በመጣባችሁ ጊዜ እንደዚሁም ጥፋታችሁ እንደ አውሎ ነፋስ በመጣባችሁ ጊዜ ችግርና ምርኮ በደረሰባችሁ ጊዜ እኔ ከዚያ አለሁ፤ አላዋቂዎችን አለመመለሳቸው ትገድላቸዋለችና ሰነፎችንም ምርመራቸው ትገድላቸዋለችና›› /Campbell, 1948, 59/[IV]

ስለዚህ ለሌሎች ማስተማርያ ሆኖ ለዘላለም ይቀሰፋል፤ ካልሆነ ደግሞ ከተወሰነ ቅጣት በኋላ ምሕረት አግኝቶ ይሰማራል፡፡

የእስራኤል ተጋዳሊ ሙሴ "ወደ ፈርዖን የምሔድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማነኝ?" እያለ በትሕትና እምቢኝታውን ቢያሰማም፤ በኋላም በእምቢተኝታው ሊጸና ቢታገልም የልዕለ ተፈጥሮ ተግሣጽ ሲከተለውም እናያለን "የእግዚአብሔርም ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ" ተብሏል /ዘጸ 4፡13/፡፡

በተጋዳሊ ሚት ውስጥ ጥሪ ከማቅረብ ጀምሮ ጥሪውን እንዲቀበል ተዕዕኖ እስከማሳደር ከዚያም ቀጣዩን የተጋዳሊውን ዕጣ ፈንታ እስከ መወሰን ሚና ያለው የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤትም ሌላው ወሳኝ ነጥብ ነው። ልዕለ ተፈጥሮ ተጋዳሊውን ከሚመጣ፣ ከታሰበና ካልታሰበ ፈተና ሁሉ የሚጠብቅና አላፊ አሸናፊ አድርጐ የሚያወጣ ዐቃቤ ኃይል ነው። ልዕለ ተፈጥሮ የምንለው መላእክት፣ ቅዱሳን፣ አምላክ፣ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ ብዙዎቹ በወንድ ወይም እንደ ጥቂቶቹ በሴት አንቀጽ የሚጠራ ሊሆን ይችላል። ተጋዳሊውን የሚጠብቀው የሚመራው የሚያስተምረው የሚንከባከበው ኃይል ነው /Campbell, 1948, 73/።

ሁሉም ሚቶች የዚህ ባሕርይ ተጋሪ ናቸው። ሃይማኖታዊ ተረኮች ደግሞ ተጋዳሊውን የጠራው ኃይል የዚህም ኃይል መልእክተኛ፣ የሃይማኖቱ ልዑል ሆኖ የሚታመነው ነገር በዚህ ረገድ ሚና ያለው ይህን ኃይል አምኖ መውጣቱም ለተጋዳሊው ኃይል ብርታት ሆኖ በየተራ የሚመጡበትን ተገዳዳሪዎች ድል ሲነሣለት የሚታይ ይሆናል።

ግዙፍም ረቂቅም ከሆነው ጋሬጣ ማለፍ ብቻ ሳይሆን ሊደርስበት ካለመው በመድረስ አንዳች በረከትን አግኝቶ እስኪመለስ አብሮት የሚጓዝ ነው። ተጋዳሊውን ተጋዳሊ የሚያሰኙትን ያሰበውን አንዳች በረከ ት እስኪይዙ የሚገጥ ሙት ውጣ ውረዶ ች በመሆናቸው ከእነዚ ህ ከሚነፍሱ የመከራ ነፋሳት፣ ከሚጐርፍ የመከራ ጐርፍ እንዲድን ቢያውኩትም እንዲጸና የሚያደርገው በመሆኑ ከተጋዳሊው ርምኧዎች ሁሉ ጋር ቁርኝት አለው። የተረኩን የፍሰት አቅጣጫ ከወዲያ ወዲህ የሚያደርጉ መከሰቻዎችም ከዚሁ ከልዕለ ተፈጥሮ ባሕርይና ሙያ ይመነጫል። ልዕለ ተፈጥሮ ተጋዳሊውን ከእናቱ ማኅጸን ከመምረጥ ጀምሮ ከመቃብሩም በኋላ ያለውን ዕጣና ዕጣው የሚጓዝበትን ፈለግ የሚወስን ነው /ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 16/።

ተጋዳሊውን ሙሴን ልዕለ ተፈጥሮ ከመጥራት ጀምሮ በተጋድሎ ጉዞው ሁሉ ኃይልን እስከማስታጠቅ የፈርዖንን ቤተመንግሥት እንዲደፍር የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠርቶ በቤተመንግሥቱ ደጃፍ እንዲያሳምጽ፣ ፈርዖንና ግብጻውያን ገዢዎቻቸውን በተለያየ መቅሰፍት እንዲመታ ማዘዙንና ማስቻሉን በመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን። ሙሴ በእነዚህ ሁሉ ረድኤቶች ቀጣዩን የተጋድሎ ቅጽር ደረጀ በደረጃ ይዘልቃል።

በተጋዳሊ ሚት ውስጥ ተጋዳሊው ገድሉን ወደ ሚፈጽምበት በመጀመሪያ ደረጃ ወደሚቀርብበት የተለየና የማይታወቅ የተጋድሎ ሥፍራ ይጓዛል። ይህ የማይታወቅ ሥፍራ ምድረበዳ፣ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ፣ጥልቅ ባህር እንግዳ ወይም አዲስ ምድር፣... ወዘተ ሊሆን ይችላል። ጉዞው አካላዊ ወይም ኅሊናዊ ሊሆን ይችላል። አስፈሪ፣ አስደንጋጭ የማይደፈሩ ቅጽርና የቅጽር

ጠባቂዎች ያሉበት ሥፍራ ነው፤ ይህ የተጋድሎ ቀጠና። ይህንን ቅጽር ማለፍ ግን ለተጋዳሊው የማይቻለው አይሆንም። አይሆንም የተባለው ይሆናል፤ ሊታሰብ የማይችለው ይታሰባል። የዘወትራዊው ዓለም ሐሳብና ጫና ሳይበግረው ሊቋረጥ የማይችለውን ቅጽር ይረግጣል፤ ያልፈዋልም።

በዚህ የጨለማ ቅጽር ውስጥ በቅርጽና መጠናቸው አስፈሪ በግብራቸውም ሞት አምጪ ከሆኑ ፍጡራን ጋር ይታገላል። እነዚህ ፍጡራን ወይ በማማለል ወይም በማዋለል ወደ ሚፈለገው ሥፍራ እንዳይደርስ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ያውካሉ በተጋዳሊውም ይታወካሉ። በዚያ የተጋድሎ ቅጽር ወስጥ በየደረጃው ፍልሚያ ይሆናል። ካምቤል ስለዚህ ሲያብራራ

> የተጋድሎ ጉዞው ለዘወትርና ከሚታወቀው ማለፊያ ሥፍራ ባሻገር ወደማይታወቀው ሥፍራ ሁሉ ነው። በጠረፉ የሚታዩት ኃይሎች ሁሉ አደገኞች ናቸው። ከእነርሱ ጋር መገናኘት አደጋ ያስከትላል። ነገር ግን ብቁ ለሆነ በወኔ ላለ ለማንም አደጋው ይከስማል ይላል። /ዝኒ ከማሁ፣ 82/ [V]

ተጋዳሊው በትግል ፍፃሜውም ያወኩትን አውኮ ያደረሱበትን መከራ ሁሉ ተቋቁሞ አሸናፊ ይሆናል።

ይህ ተጋዳሊው የመጀመሪያውን ቅጽር በመዝለቅ ያገኘው አሸናፊነት ነው። ሙሴ የእስራኤልን ነጻነት በእጅ ሲጨብጥ /እውን ሲያደርግ/ እስራኤል ከግብፅ /ከራምሴ/ ወደ ከነዓን ገሰገሱ። በዚያም እርሱ ሊያልፈው መከራ በተቀበለበት ቅጽር ላይ ይነግሣል። ተከታዮቹ፣ ያመጣ ዘንድ ያለውን በረከት ተስፋ አድርገው ሲጠብቁ የነበሩ ወገኖቹ ሁሉ አሁን ቅጽሩን በሰላም ያልፋሉ። እነዚያ ተገዳዳሪ ኃይሎች ይሻራሉ፤ ይረገጣሉ። በዚያ ቅጽር ነጻነት ይሰፍናል።

በሃይማኖታዊ ተረኮች እንደሚዘወተረው መንፈሳዊውን ፈተና አልፎ የመንፈስ በረከት ነጻነት፣ ዕረፍት፣ የነፍስ ክብር ለተጋዳሊውና ለሚከተሉት ሁሉ ይሆናል። ተጋዳሊው ነጻነቱን /በረከቱን/ ያስገኘው ሕይወቱን ለማኖር ብቻ ሳይሆን በሞቱም ሊሆን ይችላል። የእርሱ ሞት ግን ለሌሎች ሕይወት ሆኖ ይታያል፤ ይተረካል። ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ታላቁን ተጋድሎ ይፈጽማል፤ ታላቁንም በረከት ለእርሱና እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት ሁሉ ያመጣል። ከዚህ አሸናፊነት በኋላ ግን ሌላም አሸናፊነት ይላበሳል። መሥዋዕት ሆኖ በመቃብር አይቀርም ትንሣኤ /ዳግም ልደት/ አለውና።

ይሁን እንጂ የታላቁ በረከት መገኛ የመጨረሻውን /ወሳኙን/ ቅጽር መዝለቅ አሁንም ተጋዳሊነቱን ለማጉላት የሚጠብቀው ምዕራፍ ነው። ስለዚህ ስለመጨረሻው ቅጽር ሁኔታ ቴዎድሮስ ገብሬ ያብራራበትን ገለጻ ስናይ የበለጠ እንረዳዋለን።

"ይህ ሥፍራ ሁለት ቋሚ ገጽታዎች አሉት፤ አንድም ለተጋዳሊው መጠራት ለጉዞው ለተጋድሎው ምክንያት የሆነው "ታላቅ በረከት" /The ultimate boon/ መገኛ ነው። እዚህ ሥፍራ ላይ ተአምራት ይገለጣሉ። ምስጢራት ይፈታሉ። አንድም ሥፍራው የታላቁ በረከት መገኛ በመሆኑ ከየትኞቹም ሥፍራዎች በላቀ ከፍ ያለ ስቃይ የሚያስከትሉ ለታላቅ ሕማም የሚያበቁ ለሞት ጭምር የሚዳርጉ ኃያላን ዘቦች ይቆመበታል። ጠንካራ ፈተናዎች ይቀርቡበታል። ስለዚህ ሥፍራው ታላቅ በረከት ከታላቅ ጻዕር ተጐራብተው የተቀመጡበት ዕውድም ነው። /ቴዎድሮስ፤ 2001፤ 35/

በተጋዳሊው ሙሴ እርምጃ ውስጥ ይሻው የነበረውን በረከት /የእስራኤልን ክብር /ነጻነት/ ለማግኘት የሚሻገረው የመጨረሻ ቅጽር የፈርዖንን ልብ ነበር። ሙሴ ይሻው የነበረውን በረከት ያየው የያዘው ቢመስለውም አሁንም ጭራው በፈርዖን ልብ ተሰንቅሮ ቀርቷል። ስለዚህ ይህንን ወሳኝ የመጨረሻ ቅጽር መሻገር አለበት። ፍፁም ክብር /ነጻነት/ ያለው በዚያ ነው። ስለዚህ የፈርዖን ሠረገሎች ጋለቡ፤ ተጋዳሊው የሚሻውን እንዳያገኝ በእጁም እንዳያስገባ የፍጻሜው ጦርነት ሆነ፤ የፍፃሜ ተጋድሎም ሆነ። የፈርዖን ምሽግ ልብ የሚሰበረው /የሚሞተው/ ባሕረ ኤርትራ ነው። በዚህ ኤርትራ በጋዳሊው እጅ ባለ በትር የሚከፈት የሚዘጋ ይሆናል። ለተጋዳሊው የሚከፈት ለፈርዖን የሚዘጋ በትረ ሥልጣን፤ ኃይል፤ ጥበብ ነው። በዚያ የፈርዖን ምሽግ ልብ ይፈታል። ከነሠራዊቱ ይሰጥማል። ተጋዳሊው የሚሻውን በረከት /የእስራኤልን ክብር/ በድል ያልፋል። "በክብርህም ብዛት የተነሡብህን አጠፋህ፤ ቁጣህን ሰደድህ እንደገለባም በላቸው።" /ዘጸ 15፡7/

እኔ ለጥናቱ የመረጥኳቸው ገድላትም ከዚሁ አንጻር ሲመረመሩ ተጋዳሊው ከላይ አስቀድመው በተጠቀሱት ምዕራፎች ማለፉን ማሳየት የሚያስችሉ ናቸው። በተጨማሪም ገድላቱ በረጅሙ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ታሪክ ወስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሃይማኖታዊ ተረኮች እንደመሆናቸው እኔም ሥነጽሑፍ ሊያተኩርባቸው ይገባሉ ያልኳቸውን በውስጣቸው ያሉ መባያዎችን እና ትእምርቶችን በቀጣዩ ምዕራፍ ለመተንተን ጥረት አድርጌያለሁ። እነዚሁ ሃይማኖታዊ ተረኮች በነጠላው ለሃይማኖታዊ አገልግሎት ካላቸው ትርጉም በላይ ማኅበረሰቡ ሊያንጸባርቃቸው የሚፈልጉ አንዳች ርዕዮታለማዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች እንዳሉም ለማመላከት ሞክሬያለሁ።

3. ትንታኔ

3.1 ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ

የአብርሃ ወአጽብሐ ገድል በዓይነቱ ልዩ ሚሆነው የሁለት ወንድማማች ነገሥታትን ተጋድሎ እንደ አንድ ተጋዳሊ ተድርጎ የሚተረክላቸው በመሆኑ ነው፡፡ አብርሃ ወአጽብሐ በገድል ውስጥ አንድ ሲሆኑ ሁለት፣ ሁለት ሲሆኑ አንድ ተደርገው[2] የተሣሉ ተጋዳሊ /ተጋዳልያን/ ናቸው፡፡ የተጋዳሊነትን ጽንሰ ሐሳብ ለመመርመር ስነሣ ለማጥናት ወሳኝ ሚና አላቸው ብዬ ያመንኩባቸውን በገድሉ ተደጋግመው የሚነሡ አምስት የመባያ ጉዳዮችን በመምረጥ ነው፡፡ እነዚህም ጸሐፌ ገድሉ በተረኩ ወስጥ ሊላቸው የፈለጋቸውን መሠረታዊ ሐሳቦች ለማስተጋባት በተደጋጋሚ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዋናነት ደግሞ በጆሴፍ ካምቤል በተነሡት የተጋዳሊነት ሂደቶች ውስጥ በገድላቱ ወስጥ ያሉ ተጋዳልያን እንዴት እንደሚያልፉ ማሳየት የሚያስችሉ መባያ ጉዳዮችን መርጫለሁ፡፡ ከእነዚህ ወስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል፣ ገዛ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ የጽድቅ ትሩፋት፣ አንድ ሕልም፣ መቅደሱ እና በትረ ሙሴ የተባሉትን መርጬ ለመተንተን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ እነዚህ የመባያ ጉዳዮች በዚህ ገድል ብቻ ሳይሆን በተከታታይ በጥናቴ የምተነትናቸው ገድሎችም ላይ ያሉ በመሆኑ በትንታኔው ለምደርስበት መደምደሚያ አመቺ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

3.1.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል

በአብርሃ አጽብሐ ገድል ጸሐፌ ገድሉ ማስተላለፍ የፈለጋቸውን ርእዮተዓለማዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ለማስተጋባት አንድ ወጥ ከሆነው የሚቶሎጂ ሥርዓት /Mono Myth/ ውስጥ ማለፉ አይቀርም፡፡ ካምቤል ከወገን የመለየት፣ ወደ ሚጠበቅና የሚከለከል ሥፍራ የመዝለቅ በኋላም አንዳች በረከትን ይዞ የመመለስ ነገር ብሎ ያስቀመጣቸው ነጥቦችን ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ባልነው የመባያ ጉዳይ ውስጥ በጉልህ ይታያል፡፡ በተለይ ከወገን በመለየት ሂደት ውስጥ የተጋዳልያኑ ጥሪና መመረጥ በዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስን አስመስሎ በማቅረብ ስልት ውስጥ ጎልቶ ይገለጻል፡፡ አስቀድሞ የሚወለድበትን የዘር ዘውግ ከኢየሱስ የዘር ሐረግ በማድረግ የገድሉ ገለጻ መጀመሩ፣ የኢየሱስን ጽንሰትና የልደት ቀን ቁጥር ለተጋዳልያኑ በመስጠት የተመረጡበትን ልዕልና ለማጉላት መዋሉ፣ ከማኅጸነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ

---

[2] የአብርሃ አጽብሐ ገድል ጸሐፊ በነገሥታት አብርሃና አጽብሐን የሣላቸው ሲያስቡ ሲናገሩና ሲያደርጉ ተጋዳልያኑን እንደ አንድ ገጸ ባሕርይ አድርጎ ነው፡፡ በገድሉ ፍፃሜ መቃረቢያ ግን ከተጋዳልያኑ የአንዱን መሞት ለመንገር ሲሻ ለየራሳቸው የተለየ ማንነት ሰጥቶ ሲተርክላቸው እናገኛለን፡፡ ከዚያ አስቀድሞ በባሕርይና ግብር አዋሕዶ እንደ አንድ የሣለበት ክፍል አክትሞ ሁለትም ሲሆኑ ደግሞ ያሳያል፡፡

ቅዱስ በመወለድ አዲስ ኃይልን ተላብሶ ወደ ተጋድሎ ሥፍራ እንዲዘልቁ የሚደረጉበት መንገድና በተጋድሎም ሥፍራ ማሸነፍ የሚገባቸውን ጠላት /የጌርጌሴኖን አጋንንትን/ ረትተው የሚፈለገው በረከት ወደሚመጣበት መካነ በረከት ያደረጉት ግስጋሴ ተጋዳልያኑ ኢየሱስን መስለው ተጠርተው፤ ተጋድሎ ፈጽመው በድል እንዲመለሱ መደረጉን በዚህ የመባያ ጉዳይ ውስጥ በጥልቅ ለማየት ይቻላል፡፡

3.1.1.1 የዘር ሐረግ ቆጠራ

አብርሃ አጽብሐ ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው መሣል የሚጀምሩት አስቀድሞ በገድሉ የተጋዳልያኑን የዘር ሐረግ በመቁጠር መተረክ በመጀመሩ ነው፡፡ የዘር ሐረጉ እንደ ለኢየሱስ እንደተቆጠረው የፍጥረት አስገኝ ከሆነው ከእግዚአብሔር እስከ ተጋዳልያኑ አብርሃ ወአጽብሐ ድረስ ይወርዳል፡፡ ‹‹በስድስተኛውም ቀን እግዚአብሔር አባታችን አዳምን ከአራቱ ባህርያት /ጠባያት/ በአርያውና በአምሳሉ ፈጠረው›› ብሎ ይጀምርና "ታዜር በዘመናቸው ክርስትናን ያመጡ አብርሃ እና አጽብሐን ወለደ..." ብሎ የሚፈጽም ቆጠራ ነው፡፡ /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 6/ ስለዚህ ተጋዳሊው የኢየሱስን የዘር ሐረግ ተዋርሶ ወገኑን ወገን፤ ክብሩን ክብር አድርጐ ይጀምራል፡፡[3]

ጸሐፊ ገድሉ ኢየሱስን አስመስሎ የራሱን ተጋዳሊ መሣልን ከሥር መሠረቱ ይሻዋል፡፡ የታከሉው /የተጨመረው/ ለሰሎሞናዊው መንግሥት አንዱ ወራሽ የሆነው ቀዳማዊ ምኒልክ የወለዳቸውን የልጅ ልጅ ሁሉ በማስከተል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ቀጥታ ሳይሆን ትይዩ ሆኖ የዘር ሐረጉ መውረዱ ነው፡፡[4] ተጋዳልያኑ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የደም ትስስር እንዲኖራቸው ይፈለጋል፡፡[5] በደም አዋሳኙ የታላቁ መቅደስ ሠሪና ጠቢብ ንጉሥ ሰሎሞን ይሆናል፡፡ ከዚያ

---

[3] ዘር ቆጠራ በታላላቅ የክህነትና የንግሥና የዘር ግንድ አላቸው ለሚባሉት ቅዱሳን በገድላቸው ይዘወተራል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በኢትዮጵያ የክህነት ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ቦታ ባላቸው በአቡነ ተክለሃይማት ገድል ውስጥ ዘር ቆጠራ ይደረጋል፡፡ በዚህም በሥጋና በመንፈስ የእስራኤል ወገን ሆነው ይቀርባሉ፡፡ /ኢኦተቤ፤ 1989፤ ገጽ 19/

[4] ቀጥታ ያልሆነ ነገር ግን ትይዩ ነው ያልኩበት ምክንያት አዋሳኙ ንጉሥ ሰሎሞን ሆኖ የአብርሃ እና የአጽብሐ የዘር ሐረግ ከንግሥተ ሳባ በሚወለደው ቀዳማዊ ምኒልክ በኩል ሲቆጠር የክርስቶስ ግን ከዚያው ከሰሎሞን በሚወለደው በሮብአም በኩል የሚወርድ የዘር ሐረግ ይሆናል፡፡ የዘሩ ግንድ ግን ከይሁዳ ወገን የሆነው ያው ሰሎሞን ነው፡፡

[5] ይህ ‘ኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ዘንድ ለረጅም ዘመን የኖረ ትውፊት ነው፡፡ በተለይ የገገርው መደብ አባላት ነገዳቸው ከይሁዳ ወገናቸው ከሰሎሞን እንደሆነ ያምናሉ፤ ያሳምናሉ፡፡ ኢየሱስ በስደቱ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ በሚነግሩ የሃይማኖቱ ተረኮች ውስጥ ማርያም ልጇ ኢየሱስና አረጋዊው ዮሴፍ ወደ ጣና ደሴት በደረሱ ጊዜ ስለተቀበላቸው አገረ ገዢ ሲነገር እንደሚከተለው ተብሏል ‹‹ትውልዱ ወይም ነገዱ ከገሊላ ከይሁዳ ነገሥታት ወገን በመሆኑ ከኢየሩሳሌም ወደኛ አገር የሚመጡትን ሁሉ ይወዳቸዋል፡፡›› በዚህ ገለጻ ገሊላዊ የሆነው ኢየሱስን የይሁዳ አንበሳ የተባለውን ኢየሱስን ዘመዱ እንዳደረገው ልናስተውል እንችላለን፡፡ /ኢኦተቤ፤ 1985፤ ገጽ 40፡፡/

በኋላ ኢየሱስም ‹‹መቅደሱን አፍርሱት እኔ በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ›› /ዮሐ 2፡20/ ይላል፡፡ አብርሃ አጽብሐም "የጽዮን ልጆች"[6] ሆነው ታላቁን መቅደስ በአክሱም ሊያቆሙ ይነሣሉ፡፡

ሁለቱም የመቅደሱን ሥራ ፍፃሜ ለማየት ተስፋ አድርገው የሚጠብቃቸው ወገን አለ፡፡ በጆሴፍ ካምቤል ሐሳብ መሠረት ተጋዳልያኑ የሚያመጡት በረከት አለ፡፡ ያም ነገረ መቅደሱ ነው፡፡ ተጋድሎውም ያንን ታላቅ በረከት ማምጣት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለመቅደሱ ሥራ በኩር ከነበረው ሰሎሞን ጋር ይወግናሉ፡፡ ተጋዳልያኑ የሚሠሩበትን ኃይል፣ የሚያገኙትን ክብር የሚላበሱት ተለይቶ በመጠራት፣ ተለይቶም በመባረክ ብቻ ሳይሆን ከተባረከው ዘር በመገኘትም በመወገንም እንዲሆን ይደረጋል፡፡ "ቃል ኪዳኔን በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዚያም ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፡፡" /ዘፍ 17፡7/ በዚህ ጊዜ ተጋድሎው ይሰምራል፡፡

አስቀድመን በንድፈ ሐሳብ ትንተናው የዴቪድ ሌሚንግን ሐሳብ እንዳየነው ሃይማኖታዊ የተቀደሱ ተረኮች ለሃይማኖት ዓላማ ብቻ የሚውሉ ሳይሆን ለፖለቲካና ከፖለቲካም ሌላ ለጾታዊ ክርክር፣ ለዘር ልዕልና ክርክር፣ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ሁሉ ሊውል እንደሚችል አንሥተናል፡፡ በዚህም ገድል አብርሃ አጽብሐን ኢየሱስን አስመስሎ በመሣል የኢየሱስ የሆነውን የይሁዳውን ገዢ የሰሎሞንን ምርጥ /የተባረከ/ ዘር የተጋራ መሆኑን ማሳየት ጸሐፊ ገድሉ የበቀለበት ማኅበረሰብ ጽኑ ፍላጎት መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚያውም የተጋዳሊውን ዕጣ ፈንታ፣ ጽዋ ተርታ አመላካች ነው፡፡ የአቸናፊዎች ዘር አቸናፊ መሆኑን ማመላከቻ ነው፡፡ ኢየሱስ ‹‹ሞዐ አንበሳ›› የተባለው ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አሸናፊ ነው፡፡ "ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር .... ድል ነሥቷል" /ራዕ 5፡5/ ከተባለለት ዘውግ ጋር አንድ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ የጸሐፊ ገድሉ ጽኑ ፍላጎት ነው፡፡ ይህ የጸሐፊ ገድሉ ብቻ ሳይሆን እርሱን ያበቀለው ማኅበረሰብም እንዲመጣለት የሚሻውን ‹‹ሰሎሞናዊ›› የመሆን እሴት የመትከል ኃይል አለው፡፡ ተጋዳሊው ከኢየሱስ ጋር በተፈጠረለት ዝምድናም ላይ ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ራሱን ምርጥ አድርጎ እንዲያስብ፤ በተመረጠ፣ በተቀደሰ ማንነቱም የሚመሠርተው

---

[6] አብርሃ አጽብሐ በገድሉ በተደጋጋሚ ‹‹ደቂቀ ጽዮን›› ተብለውም ተጠርተዋል፡፡ ‹‹ጽዮን›› የሚለው ስም የሙሴ ጽላት በአክሱም ተቀምጣለች ብሎ የሚያምነው የኢትዮጵያ ክርስቲያን ማኅበረሰብ አክሱም ላለችው ቤተክርስቲያንም ይህንኑ ስም በመስጠት ‹‹አክሱም ጽዮን›› ይላል፡፡ ነገሥታቱ ከእስራኤል ቤተመንግሥት ጋር መዛመዳቸውን መሠረት አደርጎ ክብር ያላቸውን የእስራኤል የተቀደሱ ስፍራዎች ሁሉ ስያሜ ወስደ በዚህ በኢትዮጵያም የተቀደሱ ሥፍራዎችን ለይቶ ስሙን ማውረስ የተለመደ ነው፡፡ ጽዮንም ከመሠረቱ እያሩሳሌም ከተሠራችባቸው ተራራዎች አንዱ ነው፡፡ የእስራኤሉ ንጉሥ ዳዊት የሰፈረበት ቦታ ነበር፡፡ በኋላም ታቦተ ጽዮንን በዚያ አኑሯል፡፡ በኋላ ግን ጽዮን ቤተመቅደስ ለተሠራበት ሞሪያ ለተባለው ተራራ መጠሪያ ሆነ፡፡ በኋላም ለመላዋ እያሩሳሌም መጠሪያ ሆነ፡፡ በጠቅላላውም የአይሁድ ሕዝብ በቦታው ስም ጽዮን እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ /የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤1972፡፡/

መንግሥትና ሃይማኖት ሁሉ ከኢየሱስ የተነሣ መለኮታዊ ቡራኬ ያለው ለዓለሙም የሚተርፍ መሆኑን መግለጽ ይሻል፡፡[7]

ስለዚህ "አብርሃም ይስሃቅን ወለደ..." ብሎ የተባረከውን ዘር ምንጭ መነሻ ማድረግና ለፍፃሜው ተጋዳሊውን ማምጣትና አሸናፊ መሆኑን መንገር የብዙ አፈታሪኮች /ሚቶች/ ልማድ ነው፡፡ በዘመናዊውም ዓለም ቢሆን ‹‹እናቸንፋለን›› ለማለት የ‹‹እገሌ ምርጥ ዘር፣ ወገን ነን›› ማለት ወሳኝ የሚት ተረኮች መባያ ነው፡፡[8]

3.1.1.2 የጽንስና የልደት ቀን

በብዙ ባሕሎች ውስጥ ቀናት፣ ሳምንታት ወራት /የቀናት ቁጥር/ ተለይተው ወይም ተቀድሰው እንዲከብሩ ይሆናል፡፡ እነዚህ ቀናት /ወራት/ የሚለዩት በልዕለ ተፈጥሮ ትእዛዝ ነው፤ አልያም በተጋዳልያን የተደረጉ ወይም የተደረገባቸውን ነገሮች ከግምት አስገብተው የሚለዩ ናቸው፡፡ "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንም ምድርን ባሕርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፏልና.... የሰንበትን ቀን ባርኮታል፤ ቀድሶታልም /ዘዳ 20፡11/ ይላል፡፡ የእስራኤል ሰዎች የነጻነታቸውን ቀን /ፋሲካን/፣ የመከሩን ጊዜ መታሰቢያ /በዓለ ሠዊት/ ወዘተ እያሉ ያከብራሉ፡፡

ከበዓሉ ባለቤት ረድኤት በረከት ለማግኘት፣ ወይም የበዓሉ ባለቤት ያደረገውን ለማስታወስ ያደርጉታል፡፡ /ብርሃኑ አድማስ፣ ገጽ 136/ ለሚያከብረውም ማኅበረሰብ አንድነትን፣ ጽናትን፣ ደስታን ወዘተ ያመጣልና ይዘወተራል፡፡ ለእነዚያ ቀናት ከሰው ሕይወት ዑደት ጋር የተያያዙ መወለድ፣ መሠረግ፣ ሞት ወዘተ ጋር የገጠመ እንደሆነም አንዳች ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡ ለምሳሌ በበዓለ ፋሲካ የተወለደው ከስሙ ጀምሮ ደስታ፣ ፋሲካ እየተባለ ስም ይሰጠዋል፡፡

በነገረ ተጋዳሊ ውስጥ ግን ከዚያም በላይ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ በአብርሃ አጽብሐ ገድል የምናየው አንዱ ገጽታ ይኸው ነው፡፡ ጸሐፊ ገድሉ የአብርሃ አጽብሐ ጽንሰትና ልደት ቀን

---

[7] ለዚህ ማኅበረሰብ መሻት ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የኅቡረዕድ ኤርሚያስ ከበደ ገለጻ ነው፤ ‹‹ኢትዮጵያ በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለሆነች ማንም መሪ ያለእርሱ ፈቃድ ሥልጣን ሊይዝ አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ወስጥ ባለፉት ዘመናት በቤተክርስቲያን ተቀብተው በሕጋዊ ሥርዓት ዘውድ በመጫን ሆነ በዓመፅ በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ዘርፍ የአመራሩን ሥልጣን የያዙት ሁሉ በእርሱ ዳኝነትና ትእዛዝ የእርሱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መሣሪያዎች ሆነው እንዲያገለግሉት የተመደቡ ነበሩ፤ የዛሬዎቹም ናቸው፡፡ የወደፊቶቹም ለዚሁ የሚጠሩ ይሆናሉ፡፡ የዚህች መለኮታዊት መንግሥት ምስጥና በየትኛውም ህልውና ዘልቆ በመግባት መላውን ፍጥረተ ዓለም የሚያጠቃልል በመሆኑ፤ ይህ ሥርዓት ጸንቶ የሚሠራው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ባለ በእያንዳንዱ አገር ጭምር መሆኑን ኢትዮጵያውያን ያምናሉ፡፡›› /ኤርሚያስ ከበደ፣ ገጽ 109፣ 1993፡/

[8] አዶልፍ ሂትለር በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ዓለምን ለመግዛት ወደ ምዕራብና ምስራቅ አውሮፓ ሲዘምት ለዘመቻው ስምረት የአርያን ምርጥ ዘር ውላጆች ነን ማለትን የዘማቾቹን ሥነልቦና ለማጠንከር፣ በተለይም ጸረ ሴማዊነትን በጀርመን ለመትከል እርሱና ግብር አበሮቹ የተጠቀሙበት ስልት እንደሆነ ይነገራል፡፡

መጋቢት 29 እና ታኅሣሥ 29 መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ ይህ የጽንሰትና ልደት ቀን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ትውፊት መሠረት ለኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰጠው የጽንሰትና የልደት ቀን ጋር ይገጥማል፡፡[9] ስለዚህ ከላይ በዘር ሐረግ ቆጠራው ተጋዳልያኑን ከክርስቶስ ያዛመደበት ዓላማ እዚህም ላይ ተከትሎት መምጣቱ ያለጥቅም የተደረገ አለመሆኑን እንድንመረምር ያስገድዳል፡፡

ከኢየሱስ የመፀነስና የመወለድ ሒደቶች ጋር ተመሳሳይና ተቀራራቢ የሆኑ ሁነቶችም በገድሉ ተቀምጠዋል፡፡ የኢየሱስ እናት ድንግል ናት፤ የአብርሃ አጽብሐ እናት ሶፊያ መካን ሆና የኖረች ናት፡፡ የኢየሱስ እናት በመላእክት ራእይ ተበሰረች፤ ሶፊያም በመላእክት ራእይ ተበሰረች፤ የኢየሱስን እናት ገብርኤል ያበስራል፤ የአብርሃ አጽብሐን እናት ሚካኤል ያበስራል፡፡ የሁለቱም ጽንሰት ቀን መጋቢት 29 ይሆናል፡፡ የማርያም የጽንሷን ነገር ዐውቆ በኤልሳቤጥ ማኅፀን ያለ ልጇ ዮሐንስ ይሰግዳል፤ የሶፊያን የጽንሷን ነገር አውቀው የሀገሩ ሠራዊት ይሰግዳሉ፡፡ ኢየሱስ በመጸነሱ የማርያም ዘመዶችና ኤልሣቤጥ ደስ ተሰኙ፤ ሶፊያም ንጉሥ ጸንሳለችና ዘመዶቿ ተደሰቱ፡፡ ሁለቱም በተመሳሳይ ቀን ታኅሣሥ 29 ቀን እንደተወለዱ ይነገረናል፡፡

አብርሃ አጽብሐ ከኢየሱስ እንዲወርሱ የሚደረገው ከዘሩ የሚገኘውን ኃይልና መንፈስ ብቻ አይደለም፡፡ የጽንስና የልደት ጊዜው ካለበሰው ኃይልና መንፈስም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ነገር ተጋዳሊው ያለበት ማኅበረሰብ የሚሻውን በረከት ለማምጣት የሚያስችል አቅም እንደያዘ ማሳያ አድርጎ ጸሐፊው ተጠቅሞበታል፡፡

በብዙ ሚቶች እንደሚታዩት ተጋዳልያን፤ የእነዚህም ተጋዳልያን ተአምራዊ ሕይወት እንዲጀምር የሚደረገው በማኅፀንና በሕፃንነት ወራታቸው ነው፡፡ ለተሰጣቸው ተልዕኮ የተገቡ ለመሆናቸው ጠቃሽ መሆኑ ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐ መንታ ሆነው ይወለዳሉ፡፡ ገና በእናታቸው እቅፍ እያሉ ጡት ሳይሻሙ አንዱ ለአንዱ በትሕትና ጡት የሚተባበሉ ይሆናሉ፡፡ ይህ የተባዩ የመንትዮቹን አንድም ሁለትም ሆነው የሚገዙበት የተጋዳሊነት ዕጣ ፈንታ ጠራጊ አድርጎ ጸሐፊው እየተለመ መነሣቱን ልናስብ እንችላለን፡፡ ከዚህ በኋላ አንዲት መንበረ ሥልጣን ላይ ተቀምጠው ሳይቀናኑ፤ ሳይሻሙ፤ በፍርድ በፍትሕ ሐሳብ ሳይለያዩ እንደ አንድ ልብ መካሪ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ይራመዳሉ፡፡ የትኛውንም ትጽር ለማለፍ የበቁ ተጋዳልያን አድርጎ ጸሐፊው ማቅረቡን ያስረዳል፡፡

---

[9] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የበዓላትን ቀን ቆጥራ፤ ሰፍራ በየዕለቱ የመደበችበት ቀመር አለ፡፡ በዚህ ቀመር መሠረት የኢየሱስ ልደት ታኅሳስ 29 በየአራት ዓመቱ ደግሞ ታኅሳስ 28 እንዲከብር ይታዘዛል፡፡ የኢየሱስ ጽንሰት ቀን ደግሞ መጋቢት 29 እንደሚውል ይህንኑ የበዓላት ቀናት የሚጠቁመው መጽሐፍ ያመለክታል /ኢኦተቤ፤1991፣ ገጽ 20/፡፡

3.1.1.3 ማኅፀነ ዮርዳኖስ አብራከ መንፈስ ቅዱስ

አብርሃ አጽብሐን ከሥግው አምላክ ኢየሱስ ጋር የማመሳሰሉ ነገር በልደት ቀን ብቻ አያበቃም፡፡ ዳግም ልደት ባገኙበትም ሁኔታ ዳግመኛ እንዲመሳሰሉ ይደረጋሉ፡፡ "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም" /ዮሐ 3፡5/ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ወርዶ በመታየቱ ተከታዮቹ ዳግም ለሚወለዱበት ጥምቀት አርአያ ሆኖ ታየ፡፡ ጥምቀትንም የፈጸመው በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ነው፡፡ የዮርዳኖስ ውሃና መንፈስ ቅዱስ፣ እንዲሁም ዮሐንስ መጥምቅ ለአብርሃ አጽብሐም በዚያው መልክ ይህንን እንዲፈጽሙ ለማድረግ ጸሐፊው ወደኋላ አይልም፡፡

> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቅዱስ ሚካኤልን የዮርዳኖስን ውሃ አምጣ አለው፡፡ ፈጥኖም አመጣ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጥምቁ ዮሐንስም በዚህ ውሃ እነዚህን ወዳጆቼን አጥምቅ አለው፡፡ ዮሐንስም ለጌታችን ጻጻስ እያለ እኔ አጠምቅ ዘንድ ይገባኛልን አለው፡፡ ጌታም ለወዳጆቼ ያለኝ ፍቅር ይታወቅ ዘንድ ነው አለው፡፡ ዮሐንስም በቅዱስ ሚካኤል እጅ ወዳለው ውሃ ተመለሰ፡፡ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አለ፡፡ አብርሃ አጽብሐ ብሎም ስምን ሰጣቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስም በእነርሱ ላይ ወረደ... /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 31/[VI]

መጠመቅ ከኃጢአት መንጻት ነው፡፡ ዳግም መወለድ ነው፡፡ ስለዚህ አብርሃ አጽብሐ እንደ ተጋዳሊ የበቀሉበት ማኅበረሰብ የተሰማውን ከአሮጌ ሕይወት የመላቀቅ፣ አዲሱን የመሻት፣ መሠረትን አጽንቶ እንደ አዲስ ለመራመድ የተዘጋጀ ትውልድ የመሆኑ አምሳያ ይሆናል፡፡ አብርሃ አጽብሐ ብሎ ስም መስጠትም ያንን አብሳሪ እንዲሆን ነው፤ የጨለማውን መገፈፍ፣ የሌሊቱን መንጋት ይነግራል፡፡

ኢየሱስን አስመስሎ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ እጅ እንዲወለዱ ማድረግ፤ ጸሐፊው የሣላቸው የእርሱ ተጋዳልያን እንደ እርሱ /እንደ ኢየሱስ/ ባለ ኃይል፣ እንደ እርሱ ባለ የዕውቀት ብርሃን ተልዕኮን ለመፈጸም የመቻላቸው ትእምርት አድርጎ ያሳየበት ነው፡፡ በዚህ ኃይልና ዕውቀት ነው-ታላቁ መቅደስ የሚሠራው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ዮርዳኖስ ከነጓዙ ካለበት ሥፍራ ወደ ኢትዮጵያ፣ ዮሐንስ መጥምቅም ከነትሕትናው ወደ አክሱም ሊመጡ አይችሉም፡፡ ከኢየሱስ በዳግም ልደት ሳያመሳስሉ ሳያዛምዱ[10] "ሞዐ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ"[11] ሆነው መቅደሱን ሠሩ፣ የማይጠፋ ዘመናትን የሚሻገር ምልክና /ገጠነትን/ መትከል ቻሉ ብሎ ለመንገር ያስችግራል፡፡ [12]

---

[10] መወለድ ከወላጅ ዝምድና ማግኛ፣ ከወላጅም ብቻ ሳይሆን በዚሁ መንገድ ከወላጁ ጋር ዝምድና ካለው ከሌላውም ጋር ለመዛመድ የሚያበቃ ነው፡፡ መወለድ ግን በተለያዩ ሚቶች ውስጥ የግድ በአንድ መንገድ ብቻ የሚሆን

ስለዚህ ጸሐፊው በሥጋ የአዳም ዘር ከሆነው አብርሃም፤ ከአብርሃም የልጅ ልጅ ከያዕቆብ ከሚወለደው ይሁዳ ዘርን አቋጥሮ ምልክናውን በተጋዳልያኑ እጅ እንዳስገባ ሁሉ በዳግም ልደትም "የይሁዳ አንበሳ" ከሆነው ከኢየሱስ መንፈሳዊ ምልክና አጋርቶ፤ በአዲስ ምርጥ የሥጋና የመንፈስ ዘር ላይ አቁሞ ያለፈውን አሮጌ የበታችነት፤ የድንቁርና፤ የጨለማ ዘመን አሽቀንሮ ይጥላል። ጸሐፊው ብቻም ሳይሆን እርሱ የበቀለበት ማኅበረሰብ ይህንን የተቀደሰ ዘለዓለማዊ ህላዌ በጥብቅ ይሻዋል።

ከዚያም ተጋዳሊው ‹‹ሰሎሞናዊ›› ሆኖ መቅደስን ለማቆም ሲታገል ሊያሳየን ይጀምራል። ዘር ሳይቆጥሩ ተጋዳልያኑን ይሁዳ ጋር ማድረስ አይቻልም። ስለዚህ ዘርን በማቋጠር ተጋዳሊው ኢየሱስን እንዲመስል ተደረገ። በቆጠራ ከይሁዳ ጋር ሳያደርሱ የዳዊት ልጅ ሰሎሞናዊ ማድረግ አይቻልም። ከዚያ ሰሎሞናዊ አድርጎ መቅደስ መሥራት ቻለ ማለት ቀላል ይሆናል።

ዳግመኛም የዳዊት ልጅ ክርስቶስን በማኅፀነ ዮርዳኖስ በማዛመድ ተጋዳሊው አብርሃ አጽብሃ የሚሠሩት መቅደስ ከመቅደሶች ሁሉ ይልቃል። ከሰሎሞን የሚበልጥ አድርጎ ማሳየት የሚቻለው ከኢየሱስ ጋር በማዛመድ ነው። በንግሥተ ሳባና በሰሎሞን አፈታሪካዊ የፍቅር ግንኙነት ላይ መሥርቶ የኢትዮጵያን ገናናነት ከኢየሱስም ታላቅነትና ክብር ጋር አስተሳስሮ ማቅረብ የዚህ ማኅበረሰብ ልማድ ነው።[13]

አይደለም። ለምሳሌ በክርስትና ሃይማኖት ያለው መወለድ ወይም ልደት በመንፈስ የሚሆንና ይህም ከውስጣና ከመንፈስ በመወለድ የሚፈጸም ነው። ከክርስቶስ ጋር ዝምድና መፍጠር የሚቻለው በሥጋ በመዋለድ ብቻ አይደለም። ስለዚህ አብርሃና አጽብሐም ከክርስቶስ ጋር የሚዘመዱበት አንድ መንገድ ጥምቀት ነው። የእነርሱ ሳቅ የሚለው እንዲላበሱት የሚፈለገውን የአዳኝነት ሚና ለተከታዮቻቸው ለሚያመጡት በረከት የበቁ መሆናቸውን ማሳየት ጸሐፊው ይሻልና መጠመቂያቸውን የሚያደርገው በዮርዳኖስ ነው፤ አጥማቂውም መጥምቁ ዮሐንስ ይሆናል።

[11] ይህ ስያሜ ‹‹ሰሎሞናዊ›› በሚባለው የኢትዮጵያውያን ሥርወ መንግሥት ውስጥ ነገሥታቱ ለመንግሥታቸው የሰጡት ስያሜ ነው›› መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሆኖ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ከተሰጠው ቡራኬ የተነሣ ገዥነት የእርሱ ዕድል ሆኖ መሰጠቱ በመጽሐፍ ቅዱስም የተጠቀሰ ነው /ዘፍ፡ 49፡10/። በኋላም ኢየሱስ ክርስቶስ ላለው ዘላለማዊ ንግሥና ስያሜ ሆኖ ተሰጥቷል። የኢትዮጵያ ነገሥታት ደግሞ በክብረ ነገሥቱ እንደተቀመጠው በቀዳማዊ ምኒልክ በኩል የሰሎሞን ልጆች ሆነው የዚሁ የይሁዳ የገዥነት ቡራኬ ደርሶናል ይላሉ። ስለዚህም የመንግሥታቸው ምልክት ይኸው ‹‹ሞዐ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ›› ሆኖ ከመካከለኛው የኢትዮጵያ የታሪክ ዘመን እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል።

[12] ይህ እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ዘንድ ተስፋ እየተደረገ እየታመነም የሚኬድበት መሆኑን በአንዳንድ ምንጮች ማየት ይቻላል። የእስራኤል መንግሥት አሁን በኢትዮጵያውያን እጅ መሆኑን እና በፍፃሜው ዘመን ተረካቢው ኢየሱስ መሆኑን ከመጽሐፈ አብርሃት ጥቂት ወስዶ ማሳየት ይቻላል፤ ‹‹ምንም እኛ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤል በፊት የአምልኮተ እግዚአብሔርን ሥርዐት የሚፈጽም ክህነት ቢኖረንም እንዲሁ ሕገ መንግሥቱን የሚያካሒዱና ሕዝቡን የሚመሩ ነገሥታት ነበሩን፤ ስለዚህ ከእስራኤል ልጆች ጋር አንድ እግዚአብሔርን በአንድነት ከማምለካችን የተነሣ የዳዊት መንግሥትና የኢትዮጲስ መንግሥት በሰሎሞንና በእዜብ ንግሥት ኢትያ ዘመነ መንግሥት ተቀላቅሏል። ተዋሕዷል። ... ይህ የዳዊት የልጅ ልጅ የሰሎሞን ልጅ የምን ይልክ ዙፋን ሲሆን ፍፃሜው ግን ለክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ›› /መራራስ አማን በላይ፤ 2004፤ ገጽ VIII — IX/

[13] ይህ ነገር በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ባህልና ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት በሚሰብኩ ተረኮች ሁሉ እንደሚዘወተር ለማየት የዮናስ አድማሱን የጥናት ሐሳብ መጥቀስ ይቻላል። ‹‹Two interconnectd themes proper to our

የይሁዳ አንበሳነት ትእምርተ ኃይል ነው፡፡ አሸናፊነት ነው፡፡ ማዛመዱ ምርጥ ዘር ማስያዣ ነውና ትእምርተ ቅድስናም /ቡራኬ/ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በተረኩ ወስጥ ለሰሎሞንም ለኢየሱስም የተቻለው ሁሉ ለአብርሃ አጽብሐ ሲቻላቸው እናያለን፡፡

3.1.1.4 የጌርጌሴኖን[14] አጋንንት

- መንፈስ ቅዱስን የለበሱ አብርሃ አጽብሐም ያንን ሰይጣን የሰዎችን ልብ ለማሳት በዚህች ሀገር ምን ያህል ዘመን ኖርክ አሉት፡ ፡ ሰይጣ ኑም አስቀድ ሜ በሀገረ ጌርጌሴኖን ነበርኩ፡፡ ከዚያም እናን ተ የምታመልኩት ክርስቶስ የምትሉት ኢየሱስ ወንጌል በሚያስተምርበት ዘመን ከዚያ አሳደደን፡፡ ዳግመኛም መንገድ ወደ መራን እንድንሔድ አሰናበተን፡፡ ያንንም ሀገር ተውን፡፡ በአካባቢዎችም ሁሉ ዞርን፡፡ ወደዚህም ደረስን እስከ አሁንም በዚህች ሀገር አማልእክት ሆነን እንኖራለን /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 39/ [VII]

አብርሃ አጽብሐ በጸሐፊ ገድሉ ተዘርተው እንዲበቅሉ የተደረጉበት ምርጥ ዘር፣ እንዲያገኙ የተደረጉት ዳግም ልደት ያለበሳቸው ኃይል በኢየሱስ የተረታውን ጠላት ሁሉ ለመርታት ያበቃቸዋል፡፡ ይህም ጠላት የጌርጌሴኖን አጋንንት ነው፡፡

በዚህ ገድልም አብርሃ አጽብሐም ይህንን ለማድረግ እንዳይሳናቸው ሆነው ይቀርባሉ፡፡ የግዛታቸው ክፍል በሆኑት በሐማሴን፣ በሥርዓዊ፣ በናግራን በጣና ሐይቅ አካባቢ ሠፍሮ የነበረ መንፈስ ይዘው አስረዋል፡፡ በዚህ ሁነት ጸሐፊ ገድሉ ተጋዳልያኑን ከኢየሱስ ጋር የማመሳሰል የጸና መሻቱ ን አሁንም ደግሞ የምንረዳው የአጋንንቱ ማንነት ሲገለጥ ነው፡፡ መንፈሱ ይለፈልፋል፤ አስቀድሞ በሀገረ ጌርጌሴኖን በኢየሱስ የተረታውና የተሰደደው መንፈስ በአብርሃ አጽብሐ ግዛት መመሸጉን እንረዳለን፡፡

ይህ እንግዲህ አብርሃ አጽብሐ እንደተጋዳለ በሚጓዙበት ሂደት ወስጥ ለተጋድሎ ተለይቶ የተሰጣቸው ሥፍራ ነው፡፡ በካምቤል ሐሳብ ገድሉን የሚፈጽሙበት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርብላቸው የተለየና የማይታወቅ የተጋድሎ ሥፍራ ነው፡፡ አስፈሪ፣ አስደንጋጭ

topic emerge out of this story of romance; the first theme somewhat obvious has to do with the long lineage of the Ethiopian kings with the ancientness of Ethiopia as a necessary correlate. While the second theme is the chasennes of the Ethiopian kings and the country as a whole." /Yonas,1995, 68/

[14] ጌርጌሴኖን በደጂ ሰው እንዳያልፍ የሚተናኮሉ ሰዎች ላይ ያደሩ ክፉ መናፍስት የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ መናፍስት "እጅግ ክፉዎች" ነበሩ፡፡ ሥግው አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሲያስጨንቃቸው ሲያሳድዳቸው እናነባለን፡፡ እነዚያን ክፉ መናፍስት ከሰዎች ላይ አሳዶ በእርያዎች ላይ ያሳድራል፡፡ /ሉቃስ 8፡26/

የማይደፈሩ ቅጽርና የቅጽር ጠባቂዎች ያሉበት ሥፍራ ነውና፤ የአብርሃ አጽብሐ የተጋድሎ ቀጠና ነው፡፡ ይህንን ቅጽር ማለፍ ግን ለእነዚህ ተጋዳልያን የማይቻላቸው አይሆንም፡፡

ወደሚፈለገው ሥፍራ እንዳይደርሱ አብርሃ አጽብሐን የሚያሰናክሉ ሆነው የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ ያውካሉ በተጋዳሊውም ይታወካሉ፡፡

ይህንን መንፈስ ለመርታት የተመረጠውን ለዚያ ብቁ ሆኖ የተገኘውን የይሁዳ አንበሳን ኃይል መላበስ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ አብርሃ አጽብሐ የዚህ እጥረት እንዳይኖርባቸው ሆነው ተሥልዋልና ኢየሱስ የጌርጌሴኖን ክፉ መናፍስት /አጋንንት/ በእርያዎች ላይ እንዳሳደረ እንዳሳደዳቸውም አብርሃ አጽብሐ በዕዕዋት ላይ ያሳድራሉ፤ ያስሩታል፤ ያሳድዱታልም፡፡

ይህ የጌርጌሴኖን አጋንንት ትእምርት ነው፡፡ በሰዎች ላይ አድረው ሰዎችን የሚያጎሳቁሉ በመቃብር ሥፍራ የሚያኖሩ ናቸው፡፡ እነርሱ ያደሩባቸው ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ሁሉ ሰዎች ለማለፍ ሚቸገሩበት አካባቢ ነው፡፡ እንግዲህ የሞት፣ የጉስቁልና፣ የዐመፅ፣ ያለመገዛት፣ ሥርዓት አልበኝነት የሰፈነበት ማኅበረሰብ አምሳያ ናቸው ልንል እንችላለን፡፡ አዲስን ሥርዓት፣ ሕግ፣ ዕውቀት፣ ንጉሥ፣ ብልፅግና ሕይወትን ሁሉ ያለመቀበል ተምሳሌት ነው፡፡ የጌርጌሴኖን አጋንንት ጨምድደው ይዘው ይገዟት ከነበረች ኢየሩሳሌም በ‹‹ይሁዳ አንበሳ›› በኢየሱስ ተሸንፈው ከወጡ በኋላ ለዘመናት ደግሞ በኢትዮጵያ ከትመው እንደነበር ‹‹ወዮልን ከእነዚህ ነገሥት ፊት እንዴት እንሸሽ አስቀድሞ ዐሥራ ሁለቱ ሰዎች በኢየሩሳሌምና በሀገራችም ሁሉ ተነሡብን፤ ተውንላቸውም፡፡ አሁን ደግሞ እንደ አራዊት በምድረ በዳ ሳለን እነዚህ ዕኑዐን ነገሥታት ከዚህ ያሳድዱን ዘንድ ተነሡ፤ እንግዲህ ወዴት እንሒድ አብርሃ እና አጽብሐ ተስፋ ያደረግናትን ኢትዮጵያን አስለቀቁን" /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ ገጽ 40/[VIII] እያሉ ይነግሩናል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ከዚህ ነጻ የምትወጣው ጸሐፊው ቀድሞ በትልሙ የይሁዳ አንበሳን መንፈስና ኃይል ጥበብ ባላበሳቸው ተጋዳልያን አብርሃ አጽብሐ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ኢየሩሳሌም የሰሎሞን መቅደስ ያለበት ሀገር /ግዛት/ ናት፡፡ ስለዚህ የጌርጌሴኖን አጋንንት አይሠለጥኑባትም፡፡ ኢትዮጵያም የሰሎሞናውያን ተጋዳልያን ቤተመቅደስ ያለባት /የሚኖርባት/ ሀገር /ግዛት/ ተደርጋ በጸሐፊው ትገለጻለችና አስቀድሞ የጌርጌሴኖን አጋንንት ሊሰደዱ ሊታሰሩ ይገባል፡፡ የመቅደሱ ማኅደር ጸሐፌ ገድሉ የበቀሉበት ማኅበረሰብ ነው፡፡ ስለዚህ አዲሱን ሰሎሞናዊ ምልክና ሊቀበል ይሻልና የጌርጌሴኖንን አጋንንት ላይ ሐሳብን፣ ዐመፅን፣ የበታችነትን ሊጥል ይነሣል፡፡

በሌላም በኩል የጌርጌሴኖን አጋንንት ለኢትዮጵያ ባዕዳን ናቸው፡፡ እርሷ አጋንንት የማታበቅል ንጽህት ድንግል ትሆንና ሊደፍሯት የመጡትንም ውጊያን ከኢየሱስ ጋር የለመዱ ክፉ መናፍስትን በፍፃሜውም ጦርነት ረትታ የፍፃሜውንም መቅደስና ታቦተ ጽዮንን ለራሷ ብቻ ታስቀራለች፡፡[15] አንድም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ የሚጸረረው የሚጐረብጠው የጠላት ሐሳብ፣ አካል፣ ነገር ራሱ ምንጩ ከባሕር ማዶ እንደሆነ ያስባል ተብሎም ሊፈከር ይችላል፡፡

3.1.2 አንድ ሕልም

በገድላት ውስጥ ህልምን መጪውን የተጋዳሊያኑን ዕጣ ፈንታ ጽዋ ተርታ ለማመላከት ጥቅም ላይ የሚያውሉት ቴክኒክ መሆኑን በተለያዩ ገድላት ላይ በቀረቡት ተመሳሳይ አካሔዶች እንረዳለን፡፡ የአብርሃ አጽብሃ ገድል ጸሐፊም ይህን እንዳይጠቀም የሚከለክለው አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ የአብርሃ አጽብሐ ገድል መነበብ ከሚጀምርበት የመጀመሪያው ወር የገድል ክፍል ውስጥ ከሚገኙ ወሳኝ ነጥቦች አንዱ ከእስራኤላዊው ከካህኑ ከሌዊ ወገን እንደ ተወለደች በገድሉ የተነገረላት የአብርሃ አጽብሐ እናት ሶፊያ ያየችው ሕልም ነው፡፡ /ገድለ አብርሃ አጽብሃ፣ ገጽ 9/

ሶፊያ ያየችው ሕልም ለገድሉ እንደ ንግር ሆኖ የሚያገለግል የተጋዳልያኑን ቀጣይ ተጋድሎና ዕጣ ፈንታ ጠቋሚ ሆኗል፡፡ ሶፊያ ግን የምታየው ሕልም የልጆቿን ብቻ ሳይሆን ልጆቿን በክህነቱ የሚያከብረውን የጳጳሱን የሰላማን ተጋድሎና ዕጣ ፋንታ የሚያሳይ ንግር እንዲሆንም ይፈለጋል፡፡ ሶፊያ ልጆቿን በሁለት የብርሃን መሰላል፣ ሰላማ ከሣቱ ብርሃንን ደግሞ ብርሃን ለብሶ በትረ ወርቅ በጨበጠ ሰው ተመስለው አይታለች፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች በኋላም ገድሉ ራሱ ይተረጉማቸዋል፡፡ ሁለቱ የብርሃን መሰላሎች ሁለቱ ነገሥታት፣ በትረ ወርቅ የያዘው ብርሃን የለበሰው ሰው ደግሞ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ሆነው ይተረጎማሉ፡፡

ሶፊያ ከጅምሩ ገድላቸው ሊነገርላቸው የሚገቡ የልጆቿን ዕጣ ፈንታ ብቻ ልታይ ሲገባ ከዚያ ተሻግራ ካህኑን ወይም ጳጳሱን ሰላማን የምትፈልግበት ህልም በዋዛ የገባ አይደለም፡፡ ከጅምሩም

---

[15] የኢትዮጵያ ንጽሕና ቅድስና ክብር ልዕልና በኢትዮጵያ ባሉ ክብረ ነገሥትን በመሰሉ ተረኮች ውስጥ የሚነሳበት አንዳች ምክንያት እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡ የሀገራቱ ቅድስና ከእስራኤልም ሁሉ የላቀ ሆኖ መሣሉ ለፖለቲካውና ለማኅበራዊ ግንኙነቱም ጭምር ፋይዳው ታላቅ እንደሚሆን አይጠረጠርም፡፡ በዚህ ጉዳይ የዮናስን የጥናት ቃል ማቅረብ ይቻላል፡፡ ‹‹the notion of 'wisdom' and the 'Ark' are used as informing codes to justify the claim as well as give the story its moral and poltical significance. Both are necessary for the founding of a kingdom for more glorious than that of Israel in which are echoed the portentous words and behold a greater than Solomon is here!" / Yonas, 1995, 68/

ሶፊያ ከካህኑ ከሌዊ ወገን እንደሆነች ጸሐፊ ገድሉ ገልጾ ሕልሙን ወደ መተረክ መግባቱ ቤተክህነቱ በጥብቅ የሚፈለግበት ምስጢር እንዳለ አመላካች ነው፡፡

አብርሃ አጽብሐ ከጅምሩ በአባታቸው በኩል የተቆጠረው የዘር ሐረግ ከነገሥታቱ ከይሁዳ ወገን መሆናቸው ሲሆን በአንድ በኩል በእናታቸው በኩል ደግሞ በካህኑ በሌዊ በኩል ከካህናት ወገን መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ በዚህ በኩል በገድሉ ስለተጋዳልያኑ ሊነግረን የሚፈልገው ዋነኛ ነጥብ ከሁለቱም ማለትም ከቤተመንግሥቱም ከቤተክህነቱም ወገን እንደሚወለዱ ነው፡፡ መወለድ ወራሽ መሆንን ለዚያ የተገቡ መሆንን መመረጥን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው ምስፍናን ከክህነት አጣምረው በመያዝ በቤተመንግሥቱም ሆነ በቤተክህነቱ ‹‹ይደልዎ›› /ይገባል/ የተባለላቸው ተጋዳልያን እንደሆኑ አደርጎ ማቅረቡን ይመርጣል፡፡ ይህም ተጋዳልያኑ የተጠሩበትንና የተለዩበትን ግርማ አመላካች መሆኑ ነው፡፡ መለየት ወስጥ በአንድም በኩል ማኅበረሰቡ ባበቀለው ጸሐፊ ገድል በኩል እንዲህ በሥጋም በነፍስም አገልጋይ የሚሆን፣ ከሰማይም ከምድሩም በረከት የሚያገኝ ንጉሥ ተጋዳሊ እሻለሁ እያለን ነው፡፡

ከዚያ አልፎ የመጣው የብርሃን ልብስ የለበሰው፣ በትረ ወረቅ የያዘው፣ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን በንጉሡ ገድል በዚህ አንድ ሕልም ወስጥ እንዲታይ መደረጉ በሶፊያ የተመሰለች ኢትዮጵያ ለነገሥታት ልጆቿ ብርሃን/ዕውቀት/ ወርቅ /ሀብት፣ በረከት/ የሚሆነውን ቤተ ክህነቱን መሻቷን የሚያሳይ ይመስላል፡፡ እነዚህ ሁለት አካላት/ቤተክህነቱና ቤተ መንግሥቱ/ በአንድ ገድል የተገለጹበት አግባብ በአንድ ክንፍ የሚበሩ፣ በአንድ ርእዮት የሚራመዱ፣ አንዱ በአንዱ ውስጥ ባለድርሻ የሚሆኑ ናቸው፡፡

ቤተመንግሥቱ ያለቤተክህነቱ ተቀባይነት /legitimacy/ ለማግኘት እንደሚቸገርም ያሳያል፡፡ ስለዚህ ንጉሡ የሠራውን ሁሉ ጳጳሱ ይባርካል፡፡ ንጉሡ ተጋዳሊ ለተከታዮቹ የሚያመጣውን በረከት ሁሉ ጳጳሱ ተጋዳሊ ‹‹ይለፍ›› ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለዚያም ተጋድሎ የበቃ የሚያደርገውን የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት የሚጨብጠው በጳጳሱ በኩል ይሆናል፡፡

አብርሃ አጽብሃ በዘመቱበት ሁሉ አባ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ያጠምቃል፡፡ አብርሃ አጽብሃ በሠሩት መቅደስ የሚቀድሰው ሰላማ ነው፡፡ ያለ አባ ሰላማ መቅደሱ መቅደስ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ተጋዳሊያኑ የሚያመጡትን ታላቁን በረከት ከማኅበረሰቡ ጋር የሚያጋራው ጳጳሱ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ የንጉሡ ተጋዳሊነት፣ በተጋዳሊነትም የሚገኘው በረከት ያለጳጳሱ ቡራኬ የሚጸና አይሆንም፡፡ ስለዚህ ጳጳሱ ንጉሡን፣ ንጉሡም ጳጳሱን ይፈልገዋል፡፡

3.1.3 በትረ ሙሴ

"ይህችን ተአምራት የምታደርግበትን በትር በእጅህ ይዘሃት ሂድ" /ዘጸ 4.17/

"ይህቺ በትር ከእናንተ ጋር ትሁን፣ አትለያችሁ ክፉው መንፈስ እንዳይቀርባችሁ›› /ገድለ አብርሃ አጽብሐ፣ ገጽ 21/[IX]

የሙሴ በትር በተጋድሎው ሂደት ሁሉ የማይለየው የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ማሳያ ነው፡፡ ሙሴ በበትሩ ያልተሻገረው ቅጽር ያላሸነፈውም ተገዳዳሪ የለም፡፡ በበትሩ የፈርዖንን ደጃፍ ይደፍራል፤ የፈርዖንና የሠራዊቱን ጉልበት ያርዳል፤ ፈርዖን ሙሴን በትር ላስታጠቀው ልዕለ ተፈጥሮ ይታዘዛል፤ እስራኤል ከእስራት ይፈታሉ፤ በነጻነት ጉዞ ሁሉ የሚገጥማቸውን ቅጽር የሚጥሉት በሙሴ በትር ነው፡፡ ባህሩ የሚከፈለው እስራኤል የሚሻገሩት፣ ባህሩ የሚዘጋው ፈርዖን የሚሰጥመው በዚሁ በትር ነው፡፡ ይህ በትር እያለ እስራኤል አይራቡም፤ አይጠሙም፡፡ ዐለቱ የሚመታው፣ ውኃው የሚፈልቀውም በዚሁ በሙሴ በትር ነውና፡፡

ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእምርት የአብርሃ አጽብሐ ገድል ጸሐፊ በውል ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ በዚያ ታሪክ አንጻር ለእርሱ ተጋዳልያንም የኃይልና ሥልጣን ትእምርት አድርጎ ይህን በትረ ሙሴ ያስታጥቃቸዋል፡፡

በትሩ የተጋዳልያን ሥልጣንና ኃይል ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐም የተጋድሏቸው ሥልጣንና ኃይል ምንጭ የሆነውን በትረ ሙሴ ልዕለ ተፈጥሮ ያስታጥቃቸዋል፡፡

በትር፤ አብርሃ አጽብሐን ለይቶ መርጦ ተጋዳሊ ያደረጋቸው ልዕለ ተፈጥሮ የሚሰጠው ረድኤት ምልክት ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐ ከሚመጣ፣ ከታሰበና ካልታሰበ አደጋ ሁሉ የሚጠብቅና አሸናፊ አድርጎ የሚያወጣቸው ኃይል ማሳያ ነው፡፡ አስቀድመን በንድፈ ሐሳብ እንደተጠቀሰው ልዕለ ተፈጥሮ የምንለው መላእክት፣ ቅዱሳን፣ አምላክ፣ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አብርሃ አጽብሐንም በትረ ሙሴን የሰጣቸው መልአክ ነው፡፡

የሙሴን በትር ያስታጠቀው መልአክ ሚካኤል[16] ለአብርሃ አጽብሐም ያንኑ የሙሴን በትር እንዲያስታጥቅ ይደረጋል፡፡ ነገሥታት ተጋዳልያኑን ይህች በትር ከእናንተ ጋር ትሁን፤ ጠላት ወደ እናንተ እንዳይቀርብ አትለያችሁ፤ ይላቸዋል፡፡ ያለዚያ ኃይል ያለዚህ ሥልጣን የተከለከለ ቅጽር መዝለቅ ለተጋዳሊው አይሆንም፡፡ "ወደ እናንተ እንዳይቀርብ" የተባለው ጠላት

---

[16] ይህ ሐሳብ በሌሎች ተመሳሳይ ተረኮች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ሚካኤል፤ እስራኤል ከፈርዖን አገዛዝ ነጻ እንዲወጡ ተጋዳሊውን ሙሴን ሲረዳ እንደነበር በድርሳነ ሚካኤል ተመልክቷል፡፡ ‹‹ዕብራውያንን ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ብርሃን የመራቸው፣ ውኃውን እንደ ግድግዳ አቁሞ ባሕርን ከፍሎ ያሻገራቸው፣ ኩኒላቸው የተከለ ጠላታቸው ፈርዖንን ከእነሠራዊቱ ያሰጠመ ይህ ሚካኤል ነው›› /ኢኦተቤ፤1990፤ ገጽ 354/

የተከለከለው ቅጽር ብርታት ነው፡፡ በበትረ ሙሴ ላይ ግን የሚሠለጥን ኃይል የለውምና ለአብርሃ አጽብሐ ሁሉም ሲቻላቸው እናያለን፡፡ ያንን ትእምርተ ኃይል በገድሉ ካሳየን በኋላ ተጋዳልያኑ እንደ ሙሴ ጠላትን በተከታታይ በደረሱበት ድል ሲነሡ ማሳየት ለገድሉ ጸሐፊ ቀላል ሆኖለታል፡፡ "በትረ ሙሴ ያዙ፤ ወደ አጋንንት ማደሪያ /አጋንንት ወዳደሩበት/ ብቻቸውን ሄዱ፤ እንደ ጢስ ብናኝ ሆኑ፤ በዚያ ሀገር ያሉ ሰዎች ይህን ድንቅ ነገር ባዩ ጊዜ እጅግ አደነቁ፤ ሰገዱላቸውም፤...." /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 35/

የሙሴ በትር በፊቱ የሚደቀኑ የትኞቹንም ቅጽሮች ጥሶ በከንዓን ያለውን ርስት ለእስራኤል የሚያወርስ የመጀመሪያውን የመቅደስ ድንኳን የሚተክል፤ መቅደሱን በኢየሩሳሌም የሚሠራ ሰሎሞንን የሚያስገኘው የይሁዳ በትር ነው፡፡ ያለዚህ በትር ይሁዳ አሸናፊ አንበሳ መሆን አይችልም፡፡ የበትሩ ባለቤት መሆን የዚህ የሥልጣን፣ የክብር፣ የግዛት የኃይል ወራሽ መሆን ነው፡፡ ስለዚህ አብርሃ አጽብሐን በትረ ሙሴን እንዲታጠቁ ማድረግን ጸሐፊው በጥብቅ ይሻዋል፡፡ ከዚያም ቅጽርን ሁሉ ሲያልፉበት ያሳያል፡፡ ወደ መቅደሱም ሥራ ያደርሳቸዋል፡፡ "ሰይጣናትም የመቅደሱን ሥራ ያፈርሱ ዘንድ ተሰበሰቡ፡ አብርሃና አጽብሐም የሰይጣናቱን ሐሳብ አወቁባቸው እነዚያም ሰይጣናት ወደ መቅደሷ እንዳይቀርቡ ያቺን በትር በውስጣ አስቀመጡ›› /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 48/[X]

በበትሩ ሲያልፉት የምናየው ቅጽር የመቅደሱና የሠሪዎቹ ተቀናቃኞች ናቸው፡፡ መቅደሱ የሚሠራው እነዚህን ተቀናቃኞች በመርታት ነው፡፡ ሙሴ በበትሩ የኤርትራን ባህር ቅጽር ከተሻገረ በኋላ ነው የመቅደሱን ሥርዓት በሰና በረሃ በተራራው ላይ እንዳገኘ የሚተርከው፡፡ ስለዚህ አብርሃና አጽብሐ ይህንን የተቀናቃኞች ቅጽር በበትር እንዲጥሱ ሳይደረግ የመቅደሱን ሥርዓት ለመቀበል ለመከተል ሲያስችላቸው አናይም፡፡ የመቅደሱ ማኅደር ተከቧል፤ ያ ቅጽር ሳይሰበር የሚፈለገው በረከት አይገኝም፡፡ ስለዚህ ጠላትን ይረታሉ፤ የመቅደሱ ማደሪያ የሆነውን ሌላ የእስራኤልን ማኅበረሰብ ያንጻሉ፡፡[17] ይህ አዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብ በጉዞው ሁሉ ተጋዳልያኑ አይለዩትም፤ ይመሩታል፡፡ ውሃ ሲጠማው ከዐለት ላይ በበትሩ ያፈልቁለታል፡፡ እንደ ሙሴ ግን ውሃ ብቻ አይደለም፤ ከሙሴ የላቁ ተደርገው ተሥለዋልና፤ በእነርሱ በትረ ሙሴ የሚፈልቀው ማርና ወተት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመዓርግ ላቅ ብለው መገኘታቸውን

[17] በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትርጓሜ መጻሕፍት መሠረት በቀደመውና በአዲሱ እስራኤል መካከል ያለው ልዩነት በሥጋና በነፍስ ተለይቶ ቀርቧል፡፡ እስራኤል ዘሥጋ የሚባሉት አሰቀድመው በግዝረት የአብርሃም ልጆች መሆናቸውን በሥጋ የዘር ሐረግ የሚቆጥሩት እስራኤላውያን ናቸው፡፡ እስራኤል ዘነፍስ የሚባሉት ደግሞ ከአብርሃም ጋር የሚዛመዱት በእምነት አምኖም በመጠመቅ በሚገኝ መንፈሳዊ ልደት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ትርጓሜ በቤተክርስቲያኒቱ የአንድምታ መጻሕፈት ውስጥ ተዘውትረው ይነበባሉ፡፡ /ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ 1982፤ 1982፡፡/

ተጠቅሞ ላቅ ያለ ገቢረ ተአምር ሠሩ ለማለት ለጸሐፊው የተመቸ ሆኗል፡፡ ‹‹ጸሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ያቺን ዐለት በያዙት በትረ ሙሴ መቷት፤ በዚያን ጊዜ ማርና ውተትን አፈለቀች...›› /ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ ገጽ 48/[XI]

ጸሐፊው ለተጋዳልያኑ ባስታጠቀው በትር የእርሱን የጸሐፊውን ሥነ ልቦና የቃኘው ማኅበረሰብን መሻት ሲፈጸም፣ ፍላጎቱ ሲረካ በማሳየት የተረኩን ፋይዳ ያጎላል፡፡ የበትሩ ጽናትና ኃይል በዚህ ይታያል፡፡ ጠላትን ይረታል ትእምርተ ኃይልና ሥልጣን ነውና፡፡ ከዚህ በትር ጋር መኖር አያስርብም፤ አያስጠማም፡፡[18] ከደረቅ ጭንጫ ውሃ ይፈልቃል፡፡ በገድሉ እንደተመለከተው አብርሃ አጽብሐ ድሆችን ሰብስበው ያበላሉ፤ ለሕዝቡ ግብር ያበላሉ፡፡ ስለዚህ ተጋዳልያኑም ከደረቅ ጭንጫ ይጠጣሉ፤ ከሰማይ ኅብስት ይበላሉ፡፡ የሚመረጠውንም ማኅበረሰብ ያበላሉ፤ ያጠጣሉ፡፡ ያ ማኅበረሰብ የመቅደሱ ማኅደር አዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብ ነው፡፡ እዚህ ላይ በትር ትእምርተ በረከት ሆኖ በጸሐፊው ቀርቧል፡፡

ነገር ግን በዚህ በትር ማኅበረሰቡ የሚያገኘው መጽናናትና በረከት ብቻ አይደለም፡፡ በትር ትእምርተ በረከት ብቻ ሳይሆን ትእምርተ ተግሳጽም ይሆናል፡፡ ጸሐፊውን ያበቀለው የሃይማኖት ማኅበረሰብ የሚገዛበት መጽሐፍ ቅዱስ በትርን በብዙ አግባብ ይገልጸዋልና በዚያ እሳቤም ሊታይ ይችላል፡፡ ማኅበረሰብ በበትር ይጠበቃል፤ በቁጥጥር ሥርም ይወድቃል፡፡ በረከትንም ቅጣትንም ያወርዳል፡፡ ስለዚህ ማኅበረሰቡ "በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል" /መዝ 23.4/ የሚል አለና በዚህ አግባብ ይሆንለታል፡፡ ካልሆነም "በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ" /መዝ 2.9/ የሚል አለና በዚህ አግባብም ይሆንበታል፡፡

በትር መንግሥት ሥልጣንም ነው፡፡[19] የገድለ አብርሃ ጸሐፊ ተጋዳልያኑን ‹‹ደቂቀ ጽዮን›› በሚል ስምም ይጠራቸዋል፡፡ የተሰጠው ስም ያለዋጋ የገባ አይሆንም፡፡ አሰቀድመን ካነሣነው ልዕለ ተፈጥሮ ለተጋዳልያኑ ከሰጣቸው በትር ጋር ማዛመድ የተፈለገ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በትሩ የሚገባው ለጽዮን ልጆች ነው፡፡ የሚመነጨውም ከልዕለ ተፈጥሮ ማኅደር ከጽዮን ነው፡፡

---

[18] ሙሴ በልዕለ ተፈጥሮ ተባርኮ በተሰጠው በበትሩ በፈርዖን ፊት እንደቆመ፣ መቅሰፍትንም እንዳወረደበት፣ ታላላቅ ተአምራትንም እንዳደረገ፣ በስደትም የገጠመውን የኤርትራን ባሕር እንደከፈለበት፣ ከደረቅ ጭንጫ ውሃ እንዳፈለቀበት በመጽሐፍ ቅዱስ ተመልክቷል፡፡ ይህ በትር ያለውን ኃይልና ሥልጣን ማመላከቻ ሆኗል /ዘጸ 4÷1/፡፡

[19] በመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤ በትር የመንግሥት ሥልጣን ትእምርት ሆኖ ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡ በገድሉ ውስጥም ይህ ትእምርት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት ‹‹የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው›› የሚል ተጽፏል፡፡ ይህ በትር ግን ለጽዮን ልጆች ብቻ የተሰጠ ከጽዮንም የሚፈልቅ መሆኑን በተመሳሳይ ‹‹እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል›› ብሎ ይጽፋል፡፡ /መዝ. 45÷6፤ መዝ. 118÷2/

ስለዚህ መንግሥትና ግዛቱ የተቀደሰ ሆኖ ዘላለማዊ ነው፡፡ ለበትሩ ባለቤት አሸናፊ የለውምና ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም፡፡ በመንግሥቱ ተጠቅሞ ተገዳዳሪዎቹን፣ ተሻሚዎቹን፣ ዐማፅያኑን፣ ሽፍቶችን ሁሉ ይረታል፡፡ በመንግሥቱ ጽናት ግዛቱን ያሰፋል፡፡ በመንግሥቱ ጽናት መቅደሱን ይሠራል፡፡ መቅደሱንም ይጠብቃል፡፡

ይህ አሸናፊነት በበትሩ ባለቤት ሁሌ አለ፡፡ ኃያላኑን ሁሉ እንደ አንበሳ የሚሰብር ነው፡፡ ይህም ጸሐፌ ገድሉ አዘወትሮ ማስተጋባት የሚፈልገው የይሁዳ ነገድን ኃይል ነው፡፡ በትሩ በእጁ ነው፡፡ ስለዚህ ለዚህ ነገድ የተሰጠውን ምርቃት ከግምት አስገብቶ ዘር አቋጥሮ ከይሁዳ ነገድ ለፈረጃቸው ለእርሱ ተጋዳልያን በትር ቢያሲዛቸው የሚያስገርም አይሆንም፡፡ እንዲህ ተብሎ ተመርቋልና፡፡ "ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው፤ እንደ አንበሳ አሸመቀ፤ በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፡፡ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፡፡"/ዘፍ 49.10/፡፡

በዚህ ጊዜ የገድሉ ጸሐፊ አብርሃ አጽብሃን የሚፈለገውን በረከት ማምጣት ወደሚችሉበት የአሸናፊነት መዓርግ የበለጠ ያስጠጋቸዋል፡፡ በትሩን በታጠቁ ጊዜ ‹‹ሞዐ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ›› ይሆናሉና፡፡ በዚህ ውስጥ መቅደስ የሚያሠራ ሰሎሞናዊነት በምልዓት ይኖራል፡፡ የይሁዳ አንበሳም የሰሎሞናዊነት ምልክት ነው፡፡

ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ነው፡፡ ዳዊት ደግሞ የእሴይ ልጅ ነው፡፡ ከእሴይ ግንድ ደግሞ በትር ይወጣል፡፡[20] ስለዚህ ለተጋዳልያኑ ከዚህ በትርና ከመቅደሱ ጋር የሚያዋስናቸውን ሰሎሞናዊነት መስጠት ለጸሐፌ ገድሉ ተችሎታል፡፡

3.1.4 የጽድቅ ትሩፋት

በአብርሃ አጽብሐ ገድል የጽድቅ ትሩፋት አንዱ የመባያ ጉዳይ ነው፡፡ የአብርሃ አጽብሐ የጽድቅ ሥራ መገለጥ የሚጀምረው ገና በእናታቸው እቅፍ ሳሉ ነው፡፡ ሁለቱ መንትያ ተጋዳልያን የእናታቸውን ጡት በመቀባበል የሚጠቡ ቸሮች ሆነው ተሥለዋል፡፡ ከዚህ የገድል ሐሳብ ጋር በቀጥታ አንድ ባይሆንም የገለጻ መንገዱ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ አካሔድ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤ የእናት ማኅጸን የእናት ጡት የዚህ ዓለም ኑሮ በረከት አምሳያ የነገውን የሕይወት መንገድ አመላካች ሆኖ ይቀርባል፡፡ የይስሐቅ ልጆች ያዕቆብና ኤሳው በእናታቸው ማኅጸን የሚገፋፉ እንደነበሩ በንግር ካመለከተን በኋላ ጊዜውን ጠብቆ ኤሳው ያዕቆብን የሚያሳድድ፣ ያዕቆብም የኤሳውን በረከት የሚቀማ ሆኖ ታይቷልና፡፡

---

[20] ኢሳ. 11÷1

የዚህ ገድል ጸሐፊም በዚህ ታሪክ አንጻር ተቀራራቢ ንግር ሆኖ ነገር ግን ተቃራኒ አንድምታ እንዲኖረው አድርጎ ጽፏል፡፡ አብርሃ አጽብሐ በቀጣይ እጣ ፈንታቸው አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው በአንድ ርእዮት ሳይሻሙ ሳይቀናኑ የሚንቀሳቀሱ ሆነው ተሥለዋል፡፡

ይህ ጸሐፊውን ያበቀለው ማኅበረሰብ ያለበት ጥማት ይመስላል፡፡ የሥልጣን ሽሚያ ሽኩቻና ውዝግብ የርእዮት ዓለም ግጭት፣ የገዢ ተገዥነት ትግል በዘውዱ ቤተሰብ ውስጥ[21] መክረሩን ማኅበረሰቡ የሚሻው አይመስልም፡፡ በአብርሃ አጽብሐ ግን ይህ በእናት እቅፍ የነበራቸው ቸርነት በመንበረ ሥልጣንም እንዳይለያቸው ይደረጋል፡፡ በአንድ መንበር ሁለት ሆነው እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ይፈርዳሉ፡፡

አብርሃ አጽብሐ ለሕዝቡም ቸርነትን ያደርጋሉ፡፡ በበዓላት ያበላሉ ያጠጣሉ፡፡ ማብላት ማጠጣት ማኅበረሰቡ ከዘውዱ ቤተሰብ ስለሚጠበቀው ለተገዥዎች /subjects/ ስለሚገባ ክብር የሚነግር ይሆናል፡፡

ንግሥናን የማይፈልጉ ሆነው ይታያሉ፡፡ ነገር ግን ልዕለ ተፈጥሮ በዙፋን እንዲቀመጡ ያሳምናቸዋል፡፡ ማግባትን አይሹም ለዙፋን ውርስ ሲባል ግን ልዕለ ተፈጥሮ ከመንተዮቹ አንዱን እንዲያገባ ያሳምናል፡፡ ከምድር እህልና ውሃ አይቀምሱም፡፡ ልዕለ ተፈጥሮ የሚበሉትንንና የሚጠጡትን የሚያቀርብላቸው ይሆናል፡፡ ትኅትናቸው ልዕልናን እንዳጎናጸፋቸው እንሰበካለን፡፡

ይህ ሁሉ ግን እንደ ተጋዳሊነታቸው ሊያመጡ ለተገባቸው በረከት የበቁ እንደሆኑ ማመላከቻ ነው፡፡ ብቃትም ብቻ ሳይሆን መመረጥ እንዳላቸው በልዕለ ተፈጥሮ ጣልቃ ገብነት ውስጥ እናያለን፡፡ ስለዚህ ዳዊት፣ ሰሎሞን ለአሮጌው የእስራኤል ማኅበረሰብ ካመጡት ታላቅነት በላይ በተጋዳልያኑ አንጻር የሚታዩት በዙፋን ያሉ ገዢዎች ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብም የሚያመጡት ብልጫ ያለው ታላቅነት እንዳለ መስበኪያ ሆኖ የቀረበ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ከሰሎሞንና ከዳዊት በላይ ንጹሐን ቅዱሳን ሆነው መታየታቸው የሚያመጡት በረከትም በዚያው ደረጃ ታላቅ ነው ሊለን ይወዳል፡፡

[21] በኢትዮጵያ የመካከለኛው ታሪክ ውስጥ እንዲህ ያሉ የመንበረ ሥልጣን ትግል በዘውዱ ቤተሰብ ወስጥ የጎላ ሆኖ ይታይ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የተቀባው ዐፄ ዘመዶቹን ሁሉ ሰብስቦ አምባ ግሽን በተባለው ሥፍራ ያስር ነበር፡፡

3.1.5 ቤተ መቅደሱ

ቤተ መቅደሱ የተለየ የተባረከ የተመረጠ ሥፍራ /ቤት/ ነው፡፡ የተመረጠ የሚሆነው ከዚህ ዓለም ልዩ የተባረከ ኃያልና ተአምረኛ ለሆነው ልዕለ ተፈጥሮ ማደሪያ ከእርሱም የሚገኘው ረድኤትና በረከት ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡ አንድም በልዕለ ተፈጥሮ በተመረጡ /በተለዩ/ ተጋዳልያን በመሠራቱ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ የልዕለ ተፈጥሮን ረድኤት በረከት አልያም የተጋዳልያኑን ቅድስና ለተቀበለው ማኅበረሰብ ያ ልዩ ሥፍራ ቤተመቅደስ ነው፡፡ ማኅደርነቱ ለልዕለ ተፈጥሮ ስለሆነ የሚሠራው አካል ግን የተመረጠ ሊሆን ግድ ነው፡፡

> እጅግ ደም አፍስሰሃል፤ ታላቅም ሰልፍ አድርገሃል፤ በፊቴ በምድር ላይ ብዙ ደም አፍሰሃልና ለስሜ ቤት አትሠራም፤ እነሆ የዕረፍት ሰው የሚሆን ልጅ ይወለድልሃል፤ በዙሪያው ካሉ ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ፤ ስሙ ሰሎሞን ይባላልና፤ በዘመኑም ሰላምንና ጸጥታን ለእስራኤል እሰጣለሁ፡፡ እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፡፡ ..... የመንግሥቱም ዙፋን በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም አጸናለሁ፡፡ /ዜና 22፡8/

ተጋዳልያኑን አብርሃ አጽብሃንም ገና በሕፃንነት ወራታቸው ልዕለ ተፈጥሮ ለዚሁ ዓላማ እንዲለያቸው ይደረጋሉ፡፡ የተጋዳልያኑም መለየት ብቻ ሳይሆን የሚዘልቁት ቅጽር ሁሉ ይህንኑ ቤተመቅደስ ፍለጋ ይሆናል፡፡ ያለዚህ ቤተመቅደስ የተጋዳሊው ገድል ስምረት የለውም፡፡ በትረ መንግሥትም የጨበጡት ለዚሁ ይሆናል፡፡ የያዙት በትር ኃያልነት ማረጋገጫው፣ የሠሪት ከተማ ልዕልናና ድምቀት፣ የያዙት የይሁዳ አንበሳነት ዘውግ ማኅተም /ምልክት/ ይኸው ቤተመቅደስ ሆኖ ይቀርባል፡፡ ቤተመቅደሱ በካምቤል ሐሳብ መሠረት ተጋዳሊው የሚደርስበት አንድ ምዕራፍ ማሳያ ሲሆን የጸሐፌ ገድሉንም ሰሎሞናዊነትን የሚተክልበት ርእዮተ ዓለማዊ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ካምቤል ባስቀመጠው ሚቶሎጂያዊ ሥርዓት የታላቁ በረከት መገኛ የመጨረሻውን /ወሳኙን/ ቅጽር መዝለቅ የተጋዳሊውን ብቃት ማሳያ ስለሆነ የሚጠበቅ ምዕራፍ ነው፡፡

ጸሐፌ ገድሉም ያለዚህ ቤተመቅደስ ሰሎሞናዊነት አይኖርምና እርሱና የእርሱ ማኅበረሰብ ይህንን ምልክት /ትእምርት/ ይዞ ሰሎሞናዊነትን ያምናል ይታመናል፡፡ ስለዚህ ይህንን ለማጽናትም በተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ ተጋድሎ ውስጥ ቤተመቅደሱ ታላቅ ቤተመቅደስ እንደሆነ የሚያሳምን ከመቅደስም የላቀ መቅደስ መሆኑን ሊያሳምን የሚኖርበትን ሚታዊ ታሪክ ያቀርባል፡፡

3.1.5.1 ከሰሎሞን መቅደስ የሚበልጥ መቅደስ

የአብርሃ አጽብሃን መቅደስ ልዕልና ከሰሎሞን መቅደስ ልዕልና ማግዘፍ የሚቻለው የአንዱን ተጋዳሊ ቅድስናና መመረጥ ከሌላው በማላቅ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አብርሃ አጽብሐ ከሰሎሞን እና ከወገኑ ከእስራኤል ነገሥታትና ነቢያት ቅድስና የማይነጻጸር የላቀ ቅድስና ይላበሳሉ፡፡ ገድላቸው እነዚያን ያኰስሳል እነርሱን ያልቃል፡፡ ‹‹....እንግዲህ በማን እንመስላቸዋለን፤ በዳዊት ነው ወይስ በሰሎሞን፤ ዳዊት በመንግሥቱ መንበር ተቀምጦ ሳለ ስለሚስቱ ብሎ ኦርዮን በገደለ ጊዜ፣ሰሎሞንም በኢየሩሳሌም በነገሠ ጊዜ የአባቱን ጠላት የጌራን ልጅ ኢዮአብን በተበቀለ ጊዜ ያለርኅራኄ ያጠፋ ነበርና›› //ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 74/[XII]

አብርሃ አጽብሐ እጃቸውን ደም ካስነኩ በበቀል መንፈስ ከተሰለፉ ዳዊትና ሰሎሞን[22] ስብእና የተሻለ ስብእና ያላቸው በመሆኑ መቅደሳቸውም የተሻለ ይሆናል፤ አምሳያ የላቸውም፤ ለመቅደሱም አምሳያ የለውም፡፡ ከሰሎሞን ይልቅ አብርሃ አጽብሐ ሰማያዊቷን ኢየሩሳሌም ያያሉ፤ ሰሎሞን ብቻውን ይነግሣል፡፡ አብርሃ አጽብሐ በአንድ መንበር በፍቅር ይገዛሉ፤ ሰሎሞን ብዙ ሚስትና ዕቁባት ያከማቻል፡፡ አብርሃ አጽብሐ በድንግልና በምናኔ የመኖር ሐሳብ በውስጣቸው የሞላ ነበሩ፡፡ ሰሎሞን ተርቦ ዐሣ ሲለምን ይተረክለታል፤ አብርሃና አጽብሐ ለተጠሙ ከደረቅ ዓለት ውሃ ያፈልቃሉ፡፡ ሰሎሞን በምድር ካለ እህል ውሃ ይበላል፤ ይጠጣል፤ አብርሃ አጽብሐ ሰማያዊ ምግብና መጠጥ በመላእክት ይቀርብላቸዋል፡፡....እንዲህ እንዲህ እያለ ጸሐፊ ገድሉ ከመቅደሱ መቅደሳቸውን ሊያልቅ ይነሣል፡፡

ይህ ሲሆን ግን ለሰሎሞን መቅደስ የሆነው ሁሉ ለአብርሃ አጽብሐም መቅደስ አይጐድልበትም ሰሎሞን መቅደሱን ከጢሮስ ንጉሥ ኪራም ድጋፍ ጠይቆ ይሠራል፡፡ ኪራምም የጢሮስን ጠበብት ብልሃተኞች ይልክለታል፤ አብርሃ አጽብሐም የኪራም የልጅ ልጆችን ድጋፍ ሲጠይቁ ያሳየናል፡፡ የጢሮስም ጠበብት መጥተው ይሠራሉ፡፡

ሰሎሞን ለቤተመቅደሱ ሥራ የሚሆን እንጨት ከሊባኖስ በጥበቡ በመናፍስት /ሰይጣናት/ አስጭኖ [23]/አሸክሞ/ ያመጣል፤ አብርሃ አጽብሐም ከዓይባ፣ ከገማድ፤ ከጣና ሰይጣናትን እንጨትና ድንጋይ አሸክመው ወደ አክሱም እንዳስጫኑ ያትታል፡፡ /ገድለ አብርሃ አጽብሐ፣ ገጽ

---

[22] 2 ነገ 2÷30

[23] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለሰሎሞን በሚነገረው ትውፊት መሠረት ሰሎሞን መናፍስትን ያዝ እንደነበር የሚከተለው ምንጭ ይጠቁማል፡፡ ‹‹ሰሎሞን ቤተመቅደስ ሲሠራ እንደ ባሪያ የሚገዛቸው ፷፪ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት ነበሩትና እንጨት ቆርጣችሁ አምጡ ቢላቸው....›› /ሕማማተ መስቀል፣ ገጽ 33/፡፡

42/ ከዚህ በላቀም ሚካኤል የሚሠራበትን ድንጋይ ያቀብላል፡፡ በወርቅ በብር በዕንቁ መቅደሱ ይጌጣል፡፡ ከውስጡም ውሃ ይፈልቃል፡፡

ከዚህ በላይ መቅደሱን የላቀ የሚያደርገው የሚሠራበት የከበረ ድንጋይ ወርቅ ብርና ነሀሱ ሁሉ ከሰማይ መዝነቡ ነው፡፡ የአብርሃ አጽብሐ መቅደስ ከሰሎሞን መቅደስ ምንም ሳይጐድልበት የሰሎሞን መቅደስ የሌለው እሴት ሁሉ ታክሎበት የሚተከል ነው፡፡ የመቅደሱ መልክ ሰማያዊ ነው፤ የሚሠራበት ቁስ ሰማያዊ ነው፣ የሚሠሩት ሰማያውያንም ናቸው፣ ተጋዳልያኑ ሰማያዊ ምስጢርን ያዩ ናቸውና፡፡ ስለዚህ የሰሎሞንን ቤተመቅደስ ያስንቃል፡፡

ጸሐፌ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ በመቅደሱ ብልጫ ራሱን ያስበልጣል፡፡ ራሱን ያስመርጣል፡፡ መቅደስ ትእምርተ ቅድስና ነው፡፡ ነገር ግን ከነበረው ሳያጐድል መምጣቱ የቅድስናው መሠረት ሰሎሞናዊነት መሆኑን ለማስረገጥ ነው፡፡ የክብሩ ወራሽ ሆኖ መታየት የሚፈልግ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ዘረቢስ፣ መድረሻ ቢስ፣ አባቱን ጠርቶ አያቱን አይደግሜ አይደለም፤ ዘሩ ሥር መሠረቱ ያው የይሁዳ ነገድ ያው፤ የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት ነው፡፡ ከዚህ መነቀል አይሻም፤ ርስቱን ማጣት አይፈልግምና[24] ሰሎሞን ለመቅደሱ ያደረገውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

ነገር ግን በእርሱ ልክ ብቻ መሆን አይሻም፤ ዳግም ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ተወልዶ አዲስ ፍጥረት ሆኜአለሁ ብሏልና፤ መቅደሱን በእርሱ ያልቃል፡፡ ስለዚህ ልዕለ ተፈጥሮ ለሰሎሞን ካሳየው ጥበብና ምስጢር በላይ ለተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ በሰማያት እንዲያሳይ ይደረጋልና የአዲስ ገናና መቅደስ ባለቤት ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ከተማዩቱ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፤ ሕዝቡም እስራኤል ዘነፍስ /ሌላው እስራኤል/ ይሆናል፡፡ በዚህ መንገድ ራሱን የተመረጠ ዘውግ አድርጐ ያቀርባል፡፡ መቅደሱን በሰማያዊቱ አንጻር በመሥራቱ ዘላለማዊነትን እንደሚያሳይ ሁሉ ተጋዳልያኑን የሚከተል ሁሉ ለዘላለም በማይጠፋ ቅድስና /መመረጥ/ ውስጥ አንደሚኖር ያስባል፡፡

3.1.5.2 ኢየሱስ ያከበረው ቤተመቅደስ

> "ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፤ ደቀመዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ፡፡ እርሱ ግን መልሶ ይህንን ሁሉ ታያላችሁን፡፡ እውነት እላችኋለሁ፡፡ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው፡፡" /ማቴ 24.1/

[24] በክብረ ነገሥት እንደተመለከተው ኢትዮጵያዊ ተደርጋ የተገለጸችው የሳባ ንግሥት /ማክዳ/ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን በሄደች ጊዜ ንጉሡ ጋዛ ከተባለው ግዛቱ ርስት የሚሆናት ቦታ እንደሰጣት ተገልጿል፡፡ ይህ የርስት ስጦታ ታሪክ የኢትዮጵያን ነገሥታት ልቦና ከእስራኤል ጋር ያቆራኘ ሆኖ ኖሯል፡፡ /ሥርግው ገላው፤ 1994፤ ገጽ 26/፡፡

የኢየሩሳሌም መቅደስ አርባ ስድስት ዓመታት የፈጀበት ዕፁብ ድንቅ የተባለ መቅደስ የነበረ ቢሆንም ፈርሶ እንደሚጠፋ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ተናግሯል፡፡ በአብርሃ አጽብሐ መቅደስ ላይ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ እንዲናገርበት አይደረግም፡፡ ለመቅደሱ ሥራ ራሱ ኢየሱስ እንዳነሣሣ ይተረክልናል፡፡ "በዚህች ሥፍራ ቤትን ሥሩ" //ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ገጽ 36/[XIII] ይላል፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ከተጋዳልያኑ ጋር በሥራው መሳተፉን የሚያሳዩ ሁነቶች ይቀርባሉ፡፡ በሥራውም ያግዛል፡፡ ውሃ የተሞላውን፣ የተመረጠውን የመቅደሱን ማረፊያ /አክሱምን/ ከገነት አፈር አምጥቶ ያደርቃል፤ ይደለድላል፡፡ የሚሠራበትንም ብርና ወርቅ ሕዝቡ እስኪደነቅ ድረስ ያዘነበው እርሱ ነው፡፡ ሲፈጸምም መጥቶ የባረከው እርሱ ነው፡፡

ስለዚህ የአብርሃ አጽብሐ ቤተመቅደስ እንደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ሆኖ አይገለጽም፡፡ በዚያ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም እንደተባለ ፈርሷል፡፡ ስለዚህ ተጋዳልያኑ የኢየሱስን ፈቃድ፣ ቡራኬ በጥብቅ ይፈልጉታል፡፡ እርሱም መቅደሱን የተለየ ያደርገዋል፡፡ ተጋዳልያኑ በፍጻሜያቸው ቅጽርን ሁሉ ዘልቀው ለተከታያቸው ያቀረቡት በረከት ይህንን በኢየሱስ የከበረ ቤተመቅደስ ነውና፤ ይህንን ቤተመቅደስ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ተክለዋል፡፡[25]

ጸሐፌ ገድሉን ያበቀለው ተደራሲው ማኅበረሰብ የሚሻው መቅደስ ይሄንን ነው፡፡ መቅደስ አስቀድሜ እንደገለጽኩት የተመረጠ ሰብእና የተመረጠ ዘውግ የመሆን ነገር ነው፡፡ በኢየሱስ ያልከበረውን ቤተመቅደስ የማይፈልገው ፈርሶ ስለሚጠፋ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ተበትኖ የሚቀር፣ በስደት የሚጠፋውን አሮጌውን ምርጥ ዘር /እስራኤላዊነት/ አይሻውም፡፡ የሚሻው በእርሱ መሠረት ላይ ቆሞ እርሱን የሚተካ የማይፈርስ የማይበተን ጽኑ ገናና አዲሱን የእስራኤል ዘር መሆንን ነው፡፡[26] መበተን መፍረስ ሽንፈት ነውና እርሱን አይሻም፤ መሰደድ መጨቆን ውርደት ነውና አይስማማውም፡፡ ስለዚህ በተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ በኩል በአሸናፊ አንበሳ /በኢየሱስ/ የተባረከውን መቅደስ /መመረጥ/ ይፈልጋል፡፡

---

[25] በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብዙ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት የላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ ዳግማዊ ኢየሩሳሌም እየተባሉ መጠራታቸው የሚታወቅ ነው፡፡ የዚህ ልማድ መሠረትም የኢየሩሳሌም ሰዎች ካህናቱም ካህናቱም ሁሉ ታቦተ ጽዮንን ከነ ሥርዓተ አምልኮዋ ወደ ኢትዮጵያ /ወደ አክሱም/ ካመጡበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ በዚያው ልማድ አክሱም ጽዮን ብሎ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ በጥቅል የኢትዮጵያን ሰዎች የኢየሩሳሌም ሰዎች ንግሥናውን ከኢየሩሳሌም የመጣ፣ ታቦቱን ከኢየሩሳሌም የመጣ ወዘተ ስለሚደረግ ነው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚለውን መግለጫ የተጠቀምኩት፡፡

[26] የቀደመው የእስራኤል ዘር በ1ኛው ምዕተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ማለትም ክሮማውያን ወረራ በኋላ በየሀገራቱ መሰደዳቸው ይታወቃል፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ማኅበረሰብ አዘውትሮ የሚተርከው ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በሰሩት በደል ምክንያት የደረሰባቸው መቅሰፍት የደም ዕዳ እንደሆነ ይተረካል፡፡ ስለዚህ እስራኤላዊ ሆኖ የማይጠፋ የማይበተን የማይቀሰፍ መሆን የሚቻለው የኢየሱስን ቡራኬ ገንዘብ በማድረግ በመሆኑ እስራኤላዊነትን ሳይለቅ ነገር ግን የተባረከው ወገን ለመሆን የምርጦች ምርጥ ለመሆን በዚህ መንገድ ይጥራል፡፡

በዚህ መቅደስ ታቦት ዘዶር ትኖራለች፡፡ እርሷም የኢየሱስ እናት ማርያም ናት፡፡[27] ስለዚህ ኢየሱስ መቅደሱን አያፈርስም፡፡ ማኅበረሰቡ የተመረጠ ዘውግነቱን የማርያም የዐሥራት አገር አድርጐ የሚሰጠው ለዚህ ነው፡፡[28] ስለዚህ በሰሎሞናዊነት መሠረት ላይ የቆመው ይህ ማኅበረሰብ የምርጦች ምርጥ መሆኑን ገዝቡን "ስዩመ እግዚአብሔር"፣ ምልክቱን "ሞዐ አንበሳ"፣ በትረ መንግሥቱንም የኢየሱስን መስቀል አድርጐ ዘላለማዊ ህላዌውን ሲመኝ ይገኛል፡፡

3.1.6 ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "ከተማ" ምንነት ሲገልጹ "የንጉሥ መዲና መናገሻ፣ የአህጉር ራስ" ብለው ነው" ስለዚህ ከተማ የመንግሥት የግዛት ምልክት ሆኖ የኖረ ነው፡፡ በዚያ ብዙ ቋንቋ፣ ብዙ ሕዝብ ይኖራል፡፡ ከከተማነት በላይም ቅድስና የተሰጣቸው ከተሞች አሉ፡፡ ኢየሩሳሌም ከእነዚህ አንዷ ናት፡፡ ኢየሩሳሌም ከይሁዳ ነገድ የሆነው ገዝ የሚቀመጥባት መዲና /መናገሻ/ ናት፡፡[29] የታላቁም የሰሎሞን መቅደስ መገኛ ናት፡፡ በዚህ ክብሯ ምክንያት "ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም" ተብላለች /ነህምያ 11÷1/፡፡ በዚህች ከተማ ስም ግን ስሟን የወሰደች ሌላ ምናባዊ ከተማ በሰማይ እንዳለች በክርስትና ሚቶሎጂ ውስጥ እናያለን፡፡ ይህችም ከተማ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ናት፡፡

ቅድስቲቱ ከተማ ተጋዳልያኑ አብርሃ ወአጽብሐ ውስጣዊ ጉዞ[30] ከሚያደርጉባት ምናባዊ ከተማ አንጻር በሰማይ ልዕለ ተፈጥሮ የሠራት ሰማያዊት ከተማ ናት፡፡[31]

---

[27] ይህ በቅዳሴ ማርያም ቃል በቃል ስለሰማዩ ታቦት ሲናገር ቆይቶ ‹‹ይህቺውም እመቤታችን ማርያም ናት›› ብሎ ተርጉሞ ያሰቀመጣል፡፡ /ኢ.ኦ.ተ.ቤ፣ 1993፣ ገጽ 54፡፡/ ከኢየሱስ ጋር ለመሣመድ ያለው ፍላጎት ማሳያ ነው፡፡ ኢየሱስን ከነ ዘር ማንዘሩ የፈለገው ይመስላል፡፡ በአብርሃ አጽብሐ እንደተተከለች የተነገርላት የአክሱም ጽዮን ቤተክርቲያንም አክሱም ጽዮን ማርያም ትባላለች፡፡ የማርያም በዓል በሚከበርበት ዕለትም ትከበራለች፡፡ ስለዚህ ኢየሱስን ከነእናቱ ወስዶ ከእርሱ ጋር የተጋመደ አዲስ ጽዮናዊነትን መሥርቶ ያልፋል፡፡

[28] ኢትዮጵያ የማርያም የዐሥራት ሀገር ነች የሚለው እስከ ዛሬ በክርስቲያን ማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው ሐሳብ በሌሎችም ጥንታውያን ጽሑፎች ወስጥ የሚስተጋባ ነው፡፡ ለምሳሌ በድርሳነ ዑራኤል ያለውን ኢየሱስ ኢትዮጵያን ለእናቱ የሰጠበትን የቃልኪዳን ቃል ያቀረበበትን ገለጻ እንይ፡፡ ‹‹እናቴ ሆይ በዚች በምባርካት በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሰዎችን እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ዐሥራት ይሆኑልሽ ዘንድ ሰጥቼሻለሁ›› /ድርሳነ ዑራኤል፣ ገጽ 17/

[29] ኢየሩሳሌም ማለት የሰላም ከተማ ማለት ነው፡፡ በተራራማ ሀገር የምትገኝ ናት፡፡ ጥንታዊ ስሟ ሳሌም የሚባል ሲሆን በኋላ ኢያቡስ ያፌል እና ጽዮንም ተብላለች፡፡ ኢየሩሳሌም በተለይ በንጉሥ ሰሎሞን አምራ ሰፍታ የታላቁ መቅደስ መኖሪያ ሆና በመሠራቷ ኢየሩሳሌም ስትታሰብ በጉልህ ንጉሥ ሰሎሞን ይነሣል፡፡ ከተማይቱ በየጊዜው ቅጽሮች እየተበጁላት የይሁዳ ግዛት ወይም ነገድ ከተማ ሆና የኖረች ናት፡፡ በኋላም ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ በባቢሎናውያንና ሮማውያን ተመዝብራለች፡፡ ፈርሳለች፡፡ /የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1972፣ ገጽ 45፡፡/

[30] ውስጣዊ ጉዞ /Interior pilgrimage/ ስለሚባለው ጽንሰ ሐሳብ ሲያብራራ ‹‹በውስጣዊ ጉዞ ግለሰቡ በተወሰነና በጠበቀ ዲሲፒሊኖች ለምሳሌ በተመስጦ /meditation/ በመታገዝ ውጪውን መተው ወይም መርሳት መንፈሱን ከዓለማዊ ፍላጎት በማላቀቅ መምጠቅ ይቻላል፡፡ ተመስጧዊ ተጋዳሊ ከፈጣሪው ጋር ለመገናኘት ቅዱስ ሥፍራዎችን የመጎብኘት ግዴታ የለበትም፡፡ ተጋዳሊው እንደነባሩ ተጋዳሊ ወይም እንደ ውጫዊው ተጓዥ ሁሉ ከእካባቢው በመለየት /ግን በመንፈስ/ አካሉን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ከሥጋዊ ፍላጎቶቹ በላይ በመሆን ወደ

ወደ ዚህች ምናባዊ ከተማ ውስጣዊ ወይም ተመስጧዊ ተጋዳሊ ሆኖ መግብኘት የአብርሃ አጽብሐ ገድል አንዱ ገጽታ ነው፡፡ በኢየሩሳሌም መሥራቿ ሰሎሞን አለ፡፡ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ አለ፤ ኢየሩሳሌም የገገር በትር የማይለየው የይሁዳ ነገድ ግዛት ከተማ ናት፡፡ በዚያች ከተማ የሚከብረውም የይሁዳ አንበሳ ነው፡፡ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌምም የዚሁ አንጻር ነች፡፡

ተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐም ቅጽሩን ዐልፈው ከዚህ ዐሣ አንበሪ ከርስ /ከኢየሩሳሌም ከተማ/ እነዚህን ታላላቅ በረከቶች እንዲሹ ይደረጋል፡፡ ‹‹.....አብርሃ አጽብሐም ‹ጌታችን ሆይ እኛስ የመቅደሱን መጠን አናውቅም› አሉት ከዚያም ጌታችን በደመና ጭኖ ወደ ሰማይ አሳረጋቸው፤ የኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ምሳሌ፣ የሕንጻውን ውበት፣ ስፋቷን መሠረቷን አሳያቸው፡፡" //ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ፤ ገጽ 44/[XIV]

ወደዚህች ቅጽር ለማለፍ ለተጋዳልያኑ ሥልጣን የሚሰጠው የይሁዳ አንበሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሆናል፡፡ እርሱ በሰማይ ያሉ ሥፍራዎችን ሁሉ እርሱን ለሚወዱ ተጋዳልያን ያዘጋጃል፡፡[32] አስቀድሞም ጸሐፌ ገድሉ ከክርስቶስ ጋር ተጋዳልያኑን አመሳስሎ፤ አዛምዶ አቀራርቦ ሲገልጽልን መቆየቱ በዚህች ከተማ ባለሥልጣን በሆነው በእርሱ በአሸናፊው አንበሳ አነርሱንም አሸናፊዎች አድርጎ ለማቅረብ የተቻለው ይሆናል፡፡ ያሸነፉ ደግሞ ወደዚህች በልዕለ ተፈጥሮ ወደ ተዘጋጀች ከተማ ይገባሉ፡፡ ስለዚህ ተጋዳልያኑ ይህ የማይሳናቸው እንደሆኑ በገድሉ እንመለከታለን፡፡

ይህች ከተማ ያላትን መልክና ግርማ ኃይልና ክብር ጸሐፌ ገድሉ የበቀለበት ማኅበረሰብ በሚከተለው ሃይማኖት መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸ ነውና የማያውቀው አይደለም፡፡ ከተማዪቱ እጅግ የተዋበች ከተማ ናት፡፡ አዲሲቷ ኢየሩሳሌምም ተብላለች፡፡ በዚህች ከተማ መከራና ጉስቁልና የለም፡፡ የምስኪኖች ዕንባ ይታበሳል፡፡ የሞት ፍርሃት የለም፤ ሐዘንና ጨኸት የለም፡፡ አዲስ ናትና አሮጌው ነገር ሁሉ አልፎአል፡፡ በዚህ ከተማ ሁሉም ነገር አዲስ ይሆናል፡፡ የጠራ

ውስጡ ርቆ መጓዝ የተቀደሱ ‹ሥፍራዎችን› መጎብኘት ከፈጣሪው ጋር መገናኘት ይቻለዋል›› ይላል፡፡ /ቴዎድሮስ ገብሬ፤ 2001፤ ገጽ 64፡፡/

[31] በዮሐንስ ራእይ የተገለጠችውን ሰማያዊት ከተማ ሰብአዊ ምኞትም እንደሆነ በሚጠቁም መንገድ ፈላስፎችም ያልሟት እንደነበር የሚጽፉ አሉ፡፡ ‹‹ቅዱስ ዮሐንስ ታየሎጎስ በራእዩ የገለጻት ከተማ የአንዲት ቤተክርስቲያን ማኅበር ናት፡፡ አስቀድመው በምድር ላይ ከነበሩ ፈላስፎች፣ ገጣሚዎች፣ ባለቅኔዎች እንደ አፍላጦን ዓይነት ፈላስፎች የመረመሯት በምናባቸው የሣሏት አድልዎ መበዝበዝ የሌለባት ፍትሕ የነገሠባት እኩልነት የሰፈነባት አእምሯቸው የገመታትን ምናባዊ ከተማን ለመሥራት ሞክረው ነበር፡፡ ለዚህች ከተማ ሕግን ሥርዓትን መርኃና ደንብን እንደፍልስፍናቸውና አረዳዳቸው መጠን ሊያወጡላት ሞክረዋል፡፡›› /ታደለ ፈንታው፤ 2004/፡፡

[32] ዮሐ 14÷1፡-7

አንጸባራቂ ብርሃን ያለባት ናት፡፡ ማንም ወገን በዋዛ ጥሶት የማያልፍ ታላቅና ረጅም ቅጽር አላት፡፡ የወርቅ ዘንግ ያለው ከልካይ ቆሞባታል፡፡ እርሱ ቅጽሯን ይለካል፤ ይጠብቃል፡፡ ርዝመትና ስፋቷ እኩል ነው፡፡ ሁሉ ነገሯ በከበረ ድንጋይ ተጌጣል፡፡ በከተማዪቱ ዘንድ ሌሊት የለም፡፡ ለበጉም[33] በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ውጪ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትንም የሚያደርግ ወደ እርሷ አይገባም፡፡ /ራእ 21.1 27/

አብርሃ አጽብሐ ተጋዳሊ የሚያስብላቸውን ጉዞ ወደዚህች ፍጽምት ከተማ እንዲያደርጉ ይሆናል፡፡ እንዲሠሩ የሚደረጉት በሰማያዊቷ ከተማ አንጻር ነውና ወደዚያች ከተማ የሚጓዙት በምድር የሚሠሯትን መቅደስ መቼት /Setting/ ለማወቅ ነው፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው በዚህች ከተማ አንጻር መቅደስን ሠሩ ለማለት ተመችቶታል፡፡

የዚህች ከተማ ነገር በአብርሃ አጽብሐ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ገድላት ውስጥ ተዘውትሮ የሚገኝ መባያ ነው፡፡ ከተማይቱ አዲስ መባሏ ገድሉ የበቀለበት ጊዜና ማኅበረሰብ በተጋደሊው ውስጥ ሆኖ የሚፈልገው የሚያስሰው አዲስ ኦኗኗር፣ አዲስ ሥርዓት እንዳለ ጠቋሚ ነው፡፡ ነባሩን አስለቅቆ አንጽቶ አጽድቶ አዲስ ከተማ /መንፈስ/ እንዲመጣ መፈለጉን ይነግራል፡፡ የሚሻው አዲሱ ኦኗኗር ደግሞ በከተማይቱ እንዳየው ሥቃይና መከራ፣ ችግር፣ ሐዘንና ጩኸት የሌለበት ሁሉ እኩል የሚሆንበት የሚታዩበት ሥርዓትን ማኅበራዊ ግንኙነትን ነው፡፡ ግፍን አድልዎን ማስወገድ ይሻል፡፡

ከተማይቱ ታላቅ ቅጽር ያለባትና በወርቅ ዘንግ የምትጠበቅ ያልተመረጠ ማንም ሊገባበት የማይችል መሆኗም የሚፈለገውን አዲስ ሥርዓት ለመትከል መያዝ መታወቅ የሚገባው አንዳች ርእዮተ ዓለም መኖሩን ያመለክታል፡፡ ያለዚህ ርእዮተ ዓለም ማንም ወደዚህ ቅጽር ገብቶ የከተማዪቱ በረከቶች ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ የከተማዪቱ ቃፊር ቅጥርን ይለካል፤ ስለዚህ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ተሰፍሮ ተቆጥሮ የሚሰጥ የሥነ ኅሊና /Moral/ ሕግጋት፣ የማኅበራዊ ግንኙነት ደንብ፣ ባህል ወግ ልማድ አለ፡፡ ያንን የሚለካ ዳኛ አለ፡፡ መዝነሃል፣ ቀለሃል የሚል የፍርድ ሥርዓት አለ፡፡ የከተማዋ ርዝመት ስፋቷ ሁሉ እኩል መሆኑም እኩልነትን ማኅበራዊ ፍትህን የሚናፍቅ ማኅበረሰብን ያሳያል፡፡[34] ነውር የሚለውን ገፍቶ ማራቅ መልካም እሴት የሚለውን ስቦ ማቅረብ ይፈልጋል፡፡

---

[33] በጉ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር በግ ተብሎ ተደጋግሞ ተጠርቷል፡፡ /ዮሐ 1.29/

[34] የቁመት ወርድና ስፋት ትክክለኛነት ከሰው ኦኗኗርና ከእያንዳንዱም ሰብአዊ ፍጥረት የተቃና ሕይወት ጋር አያይዞ መተርጎም በሃይማኖት ሰባክያን የተለመደ ነው፡፡ ለዚህም የሚከተለውን እንይ ‹‹በምድራዊ ከተማ ቁመት

አብርሃ አጽብሐ ለዚህች ከተማ የተገቡ የተመረጡ ሆነው የከተማይቱን ውበትና ክብር አዩ። ማኅበረሰቡ በተጋዳልያኑ ውስጥ ራሱን ለዚህ ለሚፈለግ መልካምና አዲስ ሥርዓት የተገባ ያደርጋል። ለዚህ የሚያበቃው ግን የከተማዪቱ ብርሃን፣ ገገር፣ መቅደስ የተባለው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ በገገርነት ለዚህ ሥርዓት የሚፈለግበት ምክንያት አስቀድሜ እንደጠቀምኩት ከይሁዳ ነገድ የሚገኝ አሸናፊ አንበሳ በመሆኑ ነው። የገድሉ ጸሐፊ "በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን።›› /ሮሜ 13. 13/ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃይለ ቃል ከሚያውቀው ክርስቲያን ማኅበረሰብ የተገኘ በመሆኑ አብርሃ አጽብሐ በእርሱ የተወደዱ የተመረጡ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በዚህ መንገድ ማኅበረሰቡ ለሚሻው ማራኪ አዲስ ሥርዓት ቁልፍ ያለው በይሁዳ ነገድ ይሆንና ያለው ብቸኛ አማራጭ ሰሎሞናዊው መንግሥት ነው።

በዚህ መንግሥት የወርቅ ዘንግ ነው፤ ፍትሕ ርትዕ የሚጸናው። ነጻነት የሚገኘው ተድላ ደስታ የሚነግሠው ከተማይቱ /ሥርዓቱ/ በብርሃን /በዕውቀት/ የሚሞላው። ከኃያላን ሁሉ በላይ ሆኖ አሸናፊ የሚኾነው። የአብርሃ አጽብሐ ገድል የዚህ ነጋሪ ነው። ለዚህ ነው በገድሉ ውስጥ አብርሃ አጽብሐ የሚሠሩት ሁሉ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት በአዲሲቱ ከተማ አምሳያ እንደሆነ ደጋግሞ የሚነግረን። ተጋዳልያኑም ቅጽርን አልፈው ከተጓዙበት ጉዞ ይዘው የሚመለሱት በረከት ይሄንኑ ነው።

የሚሠሩት ከተማ በምድር ካሉ ከተሞች የተለየ ሊሆን ይገባል። በምድር ያሉ ከተሞች ከግንባታ ጀምሮ በግፍ የተገነቡ ናቸው። ታላላቆቹ የግሪክና የሮማውያን ከተሞች በባሪያ ጉልበት በግፍ የተገነቡ ናቸው። ደሀ ሀብታም፣ ገገር ተጨቋኝ፣ ወዘተ የሚሉ የልዩነት መንደሮች ናቸው። ዋይታና ጩኸት፣ ቅሚያ ስስት፣ ውሸትና ርኵሰት የሞላባቸው ናቸው። ስለዚህ የትኛውም ማኅበረሰብ ከዚህ የጸዳ አኗኗርን ይሻልና ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን የመሰለች የምናብ ከተማ ይመኛል። እንዲህ ያሉ ፍላጎቶቹን የሚገልጥበት ሚት ይኖረዋል። አብርሃ አጽብሐም እንደተጋዳሊ ይሄንን ታላቅ በረከት ለማምጣት ሲጋደሉ ጸሐፊ ገድሉ ያሳየናል።

ወርድና ስፋት ትክክል ሆኖ መታየቱ የሕይወትን የተሟላ ገጽታ ያመለክታል። የምድራውያን ከተማዎች መታወቂያቸው መከራ ሥቃይ ምሉዕነትን ማጣት ነው። ሁሉም ምድራውያን ያልተስተካከሉ በመሆናቸው እንደ ከተማዎች ሁሉ ሥልጣኔአቸውና አመራራቸው ሁሉ ያልተስተካከለ ነው። ይህ የተስተካከለ ሕይወት የሚጀምረው ከግለሰብ ነው። የመጀመሪያው የሚስተካከል ሰው በዕውቀት የበለጸገ በሃይማኖቱ የታወቀ ሆኖ ጥበብ ሥጋዊና መንፈሳዊውን አስተካክሎ ማየት መያዝ ሲቻለው ነው። ይህ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚደረግ ጉዞ ወርድን ያመለክታል። ሁለተኛው የሰው ልጅ ጥቁር ነጭ ሀብታም ደሀ አይሁዳዊ የግሪክ ሰው ባሪያ ጨዋ መሪ ተመሪ ሳይሉ በእኩልነት መውደድ ነው...››/ታደለ ፈንታው፤ 2004/

3.2 ገድለ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን

በቤተመንግሥቱ መዓርግ ንጉሥ የሥልጣን እርካቡ ጫፍ እንደሆነ ሁሉ በቤተክህነቱ ደግሞ ጵጵስና የመዓርጋቱ ሁሉ የበላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሚታወቅ ገድል የተጻፈላቸው፣ በኢትዮጵያ በጵጵስና እንዳገለገለ በታሪክም የሚጠቀሰው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው፡፡ ለዚህ ታሪካዊ ሰው ገድል ተጽፎለት እናገኛለን፡፡ ይህንን ገድል አስቀድሜ ባቀረብኩት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ለመመርመር ስሞክር ከነገሥታቱ ገድል ጋር በማነጻጸር ለማየት የሚያስችሉ ተቀራራቢ የመባያ ጉዳዮችን ያስቀመጥኩ ሲሆን እነዚህ መባያዎችም በተደጋጋሚ በገድሉ የታዩ ሁነቶች ሆነው በመገኘታቸው የመረጥኳቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ክርስቶስን መምሰል፣ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ አንድ ጎልም፣ የተባረኩ ምንጮች፣ መስበክና ማጥመቅ የተባሉ ናቸው፡፡

3.2.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል

3.2.1.1 ዐውደ ልደት

በገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንም በጥሪና መለየት ምዕራፍ ውስጥ ተጋዳሊው ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ ሲቀርብ እናያለን፡፡ አስቀድሜ በነገሥታቱ አብርሃ አጽብሐ ገድል ጸሐፊ የታየውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስመስሎ ተጋዳሊውን የመግለጽ ነገር አሁንም የካህኑ ተጋዳሊ ገድል ጸሐፊ አንድ ስልት አደርጎ ሲጠቀምበት ይታያል፡፡ በገድለ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተጋዳሊው በምድረ እስራኤል በመወለድ፣ በተወለደበት ዕለት ታላቅ ብርሃን መታየቱ፣ የአዕላፍ መላእክት ወደ ምድር መውረድ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁ፣ በሊቀ ጳጳሱ ጢሞቴዎስ መታቀፉ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አመሳስ ሎ የማቅረብ አካሔ ዱን ያመለክታል፡፡ ክርስቶስ በምድረ እስራኤል ከተወለደበት፣ በተወለደበት ዕለተ ጀምሮ ሰብአ ሰገል በመሪ ኮከብ ብርሃን መታጀቡ፣ መላእክት በቤተልሔም ከመዘመራቸው፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ከመጠመቁና በአረጋዊው ስምዖን ከመታቀፉ ጋር ይገጥማል፡፡

ይህ መመሳሰል በገድሉ ውስጥ በዘፈቀደ የሆነ የተደረገ አይደለም፡፡ ይሁንኝ ተብሎ መደረጉን የራሱን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጠቅሶ በማስታወስና ኢየሱስ ከመላእክቱም ጋር አብሮ በመገለጽ ምስክርነትና ቡራኬ አንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በኢየሱስ ልደት ከታየው ተአምራት በላይ ይታያል፡፡ "ስለ ልደቱ ክብር ምድር ሰባት ቀን ፈጽማ አበራች" ይላል፡፡ /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 2/ መላእክት በቁጥር ከመብዛታቸው የተነሣ እርሱን ለማየት ይገፋፉ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ የተጋዳሊውን ዕጣ ፈንታ ከመንገር በላይ የክርስቶስን መልክ ለመስጠትም የገቡ ናቸው፡፡

አረጋዊው ስምዖን ክርስቶስን አቅፎ የተናገረው ቃል እንደ ንግር መጪውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ እንዳመለከተው ሁሉ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንን ያቀፈው ሊቀ ጳጳሱ ጢሞቴዎስ ለክርስቶስ በተነገረው ንግር መልክ ስለ ሰላማም "ይህ ሕፃን ለሰው መድኀኒት ይሆናል።"ይላል። /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 4/

3.2.፣.2 የክህነት ዘር ቆጠራ

ንጉሡ ተጋዳሊ የምርጥ ዘር ንግሥናውን በኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስና በሥጋ እንዲዋለድ /እንዲዛመድ/ የዘር ሐረግ ተስቦ ተቆጥሮ ለማጽናት ለማላቅ ጥረት እንደሚደረግ ሁሉ ካህኑ ተጋዳሊም የምርጥ ዘር ክህነትን ይዞ እንዲገኝ የመንፈስ ዘር ሲቆጠርለት ይታያል። ስለዚህ የገድሉ ጸሐፊ ከተወለደበት ምድር እንዲወለድ፣ ከተጠመቀበት ወንዝ እንዲጠመቅ፣ በተመሰገነባቸው መላእክት እንዲመሰገን አድርጎ ከምንጩ የተገኘ ወገኑ ነው ብለን እንድናምን ጥረት ያደርጋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ወገን ከሰሎሞን ከዳዊት የነገሥታት ዘር ይውጣ እንጂ የማይጠፋ ክህነት እንዳለውም በመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን።[35] ተጋዳሊው እንዲላበስ የሚፈለገው ይህንን የማይጠፋ ክህነት ነው። ስለዚህ ነው ከሊቀ ካህኑ ጋር ተዛምዶ ቋጠሮውን ማጥበቅ የፈለገው። ከሊቀ ካህኑ ኢየሱስ ሐዋርያት ክህነትን ወስደዋል። እነርሱም ምድረ እስራኤል ያበቀላቸው ናቸው። ምድረ እስራኤል ከክርስቶስም በፊት የነበሩ የብዙ ሊቃነ ካህናት ሀገር ነው። የተመረጠው የክህነት ባለቤት የሌዊ ሀገር ነው። በዚህ ነባሩ በበቀለበት የክህነት መሠረት ላይ የማይጠፋ ክህነት ይዞ የተገኘው ደግሞ ኢየሱስ በመሆኑ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንም በነባሩ መሠረት ላይ የመጣውን ይህን የማይጠፋ ክህነት እንዲሻ ይደረጋል። የክህነቱን ዘላለማዊነት ለማጽናት እንደመልከ ጼዴቅ[36] ለዘላለም ካህን ነህ የተባለለትን ክርስቶስን መያዝ አስፈላጊ ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ መታየቱም ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ከ245 ዓ.ም. ላይ የተወለደው አባ ሰላማ የዚህ ክህነት ባለቤት የመሆኑ ጠቋሚ ነው።

---

[35] ስለኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው ቃል ያንን ያሳያል ‹‹ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደወጣ የተገለጠ ነውና፤ ስለዚህ ነገድ ሙሴ ምንም እንኳ ስለክህነት አልተናገረም .... አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሃላ ጋር ካህን ሆኗልና ::›› /ዕብ 7÷14-22/ ይህ ከዘር ቆጠራ ውጪ የሆነው

[36] መልከ ጼዴቅ የዘር ግንዱ ከማን ወገን እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ስላልተጠቀሰ ይህ ከዘር ቆጠራ ውጪ የሆነው መልከ ጼዴቅ ክህነት ዘላለማዊ ተደርጎ በመሃላ ብቻ የጸና ክህነት እንደሆነ ይታመናል። በኢትዮጵያውያን ደግሞ መልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ይታመንና በመሃላ የነበረውም የእርሱ ክህነት ለኢትዮጵያውያንም ውርስ ተደርጎ ይታሰባል። ለዚህም የንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ከበደን ገለጻ እንውሰድ፤ ‹‹ምሳሌው ሆኖ ቀድሞት እንደተገለጸው እንደ መልከ ጼዴቅ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ከሦስቱ የኖህ ልጆች ካም ሴም እና ያፌት ዘሮች ውሕደት ስለተወለደ የቅዱሳን ኪዳን ሕዝባዊነቱን ካህንነቱንና ንጉሥነቱን በማሳየት እራሱ ዘላለማዊውና ፍፁም ኢትዮጵያዊ መሆኑን አረጋግጧል።››/ኤርሚያስ ከበደ፣1993፤ ገጽ 66።/

ይህ ሁሉ ግን ተጋዳሊው የበቀለበት የታሪኩ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ ራእይ ነው። ተጋዳሊውም ብዙ ቅጽርን አልፎ ዘልቆ ሄዶ በተጋድሎው ይዞ የሚመለሰው በረከት ይሄ ነው። ለዚህ ዓለማ የተጠራው የተለየው ሰላማ ተለይቶ ከተጠራበት ኢየሩሳሌም /ምድረ እስራኤል/ ተነሥቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገው ጉዞ የፈተናው መጀመሪያ ይሆናል። በዚህ ሁኔት ውስጥ ከታሪካዊዎቹ ሰዎች አጋጣሚ በተለየ ሚታዊ ሆኖ ይተረካል። ሜርጵዮስ[37] ከተባለው መርከበኛ ነጋዴ ጋር የተጓዘው አባ ሰላማ ሜርጵዮስን ከገደሉት ሽፍቶች ሰይፍ ያመለጠው በእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ በገድሉ ይነገረናል። ለሜርጵዮስ ያልተቻለው ለተጋዳሊው ለሰላማ የተቻለው በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ምክንያት ሆኖ ኃይሉን ባሳየው በእግዚአብሔር ይሆናል። በእርሱም ረድኤት ይህንን የሽፍቶች ቅጽር ተሻግሮ ለሌላ ተጋድሎ ይዘጋጃል። ለጊዜው ተከታዮቹ የሚጠብቁትና የሚያመጣው በረከት ማሳረፊያ በሆነችው በአክሱም ያርፋል። ሄዶ ሄዶ ግን ማረፊያው የኢየሱስን የክህነት ውርስ የሚጨብጥበትን ቋጠሮ ማግኘት ነው። ለዚህ የሚያስፈልገውን ገድል ሁሉ በዚያ ሆኖ ይፈጽማል።

> ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያለማጣመም ትልሙን አቃንቶ ተለመ እንጂ። ከዚህ በኋላ ታላትና መልካም ገድልን ተጋዳለ፤ በጾምና በጸሎት በልመና በምልጃ ለእግዚአብሔር ቅኑት እንደገበሬ፣ ጽሙድ እንደበሬ ሆኖ አገለገለ። እንደ መላእክትም ትጉህ ሆነ በመሰቃየትና በመትጋት ያለ ሰንበታት ምንም እህል ሳይቀምስ የአድባራት ሁሉ እናት በምትሆን በአክሱም ተቀመጠ። /ገድለ ሰላማ ከግቱ ብርሃን፣ ገጽ 6 /

ከዚህ ተጋድሎው በኋላ ነው የኢየሱስ ክርስቶስን የክህነት ውርስ የሚያገኝበትን መስመሩን ፍለጋ እስክንድርያ የሚሔደው። እስክንድርያ የክርስቶስ የክህነት ዘር ያላቸው ሐዋርያት ውርስ /Appstolic Sucssion/ ያላት[38] ናትና ዘር ሊቋጠር ሄደ። ንጉሡ ተጋዳሊ በይሁዳ ነገድ ካሉት ጋር ዘር ተቋጥሮ ንግሥናውን እንዲያጸና እንደተደረገ ካህኑም ተጋዳሊ ክርስቶስ ሐዋርያትን ወለደ፣ ሐዋርያትም የማርቆስን መንበር፣ የማርቆስም መንበር አትናቴዎስን፣ አትናቴዎስም ሰላማን ወለደ ተብሎ መንፈሳዊ የክህነት የዘር ሐረግ እንዲቆጠርለት መደረጉ ነው።

ንጉሡ ተጋዳሊ ኢየሱስ ከይሁዳ ነገድ መወለዱን መነሻ አድርጎ በእርሱ መሠረት ላይ ሰሎሞናዊ ቤተመንግሥቱን ሲተክል፤ ካህኑ ተጋዳሊም ከይሁዳ ነገድ የተወለደው ክርስቶስ ላይ የማይጠፋ ክህነቱን መሠረት አድርጎ ቤተክህነቱን እንዲተክል ይደረጋል። ክህነቱ እንደቀደመው

---

[37] ሜሮጵዮስ በታሪክም ይሁን በገድሉ ገለጻ አባ ሰላማ ከግቱ ብርሃን ወደ አክሱም ሲመጣ ይዞት የተጓዘ ነጋዴና መርከበኛ ነበር።

[38] ሐዋርያዊ ውርስ የሚባለው ወይም ሐዋርያዊ ውርስ አላቸው የሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት ከሐዋርያት ጀምሮ የተያያዘ የክህነት ውርስ ያላቸው አብያተክርስቲያናት ናቸው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከቅዱስ ማርቆስ የእስክንድርያ መንበር ጋር ያዛመዳት ይህንን ውርስ ለማግኘት መፈለጓ ነው /ኅርኅርዮስ፤1974፤ ገጽ 136/።

ከሌዊ ወገን እንዲሆን አይፈለግም፤ የማይጠፋ ክህነት ባለቤት መሆን ይሻልና ካህኑ ተጋዳሊ ሊቀካህኑን ክርስቶስን መስሎ ከይሁዳ አንበሳ የሆነውን ክህነት እንዲፈልግ ይደረጋል። ስለዚህ ጸሐፊው ቤተክህነት ከቤተመንግሥቱ ጋር በዘር ቆጠራም አንድ መሠረት እንዲኖራት የጸና ፍላጎት እንዳለው ያመለክተናል።

ይህ ሁሉ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ ራእይ ነው። ቤተክህነቱ የሚሦ መንግሥት ባለድርሻ[39] የሚሆነው በዚህ ቆጠራ ነው።

አስቀድሜ እንዳቀረብኩት የነገሥታቱ ገድል ጸሐፊ የተጋዳሊውን ሰሎሞናዊነት አዲስ መሠረት ለማስያዝ ክርስቶስን በመምሰል እንዲባረክ ያደርገዋል። በዚህም መንግሥቱን ከዳዊት ከሰሎሞን መንግሥት ያስበልጥና ዘላለማዊ የማይጠፋ አሸናፊ መንግሥትን እንዲመሠርት ያስችለዋል። ካህኑ ተጋዳሊ ሌዋዊውን ክህነት ለውጦ አዲስ መሠረት ለማስያዝ ክርስቶስን በመምሰል ያስባርካል። በዚህም ክህነቱን ከሌዋዊው ከአሮን ክህነት ያስበልጥና የተለየ የማይጠፋ አሸናፊ ክህነት እንዲመሠርት ይደረጋል።

በካህኑ ተጋዳሊ በኩል ጸሐፌ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ የከበረውን ክህነት ለራሱ ያደርጋል። ክህነት ማገልገያ ነውና። ያ ማኅበረሰብ የሚበልጥ ክብር ባለው ክህነት ማገልገልና መገልገል ይፈልጋል። ክህነት ከልዕለ ተፈጥሮ ጋር መገናኛ ነውና በተሻለ ክህነት ከገገርው ከአምላኩ ጋር የሰመረ ግንኙነት ይፈልጋል። ክህነት መሥዋዕት ማቅረቢያ ነውና ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ማቅረብ ይፈልጋል። ስለዚህ በተጋዳሊው በኩል የላቀ የበቃ የነቃ ክህነትን በእጁ ለመጨበጥ መሻቱን ያሳያል።

ይህንን ማድረግ የሚችለው ደግሞ ተጋዳሊውን ከሌሎች ተጋዳልያን የበለጠ የተመረጠ አድርጎ በመቆረክ ነው። የመመረጡ ማሳያ ደግሞ ክርስቶስን በነገር ሁሉ መምሰሉና በእርሱ የተመሰከረለት መሆኑ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ይለዋል።

> እኔም ፊቴን ለአንተ አሳየሁህ አለው። እኔንም አይተህ መረዳት ቻልክ ከነቢያትና ከሐዋርያት ስለ እኔ መረዳት የቻለ አልነበረም፤ ሙሴም አየኝ ስለ እኔ መረዳት ተሣነው፤ አንተ ታማኝ አገልጋዬ ወዳጅ

---

[39] ቤተክርስቲያን በአቡነ ተክለሃይማኖት በኩል ከሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ጋር በተዋዋለችው መሠረት ከመንግሥትነቱ ድርሻ በመንግሥት ከሚገኘው ሀብትና ቁጥጥር ሲሦውን እንድትወስድ ያገኘችው ስምምነት ነበር። ይህ አከፋፈል ለአንጋሽ፣ ለነጋሽ፣ ለቀዳሽ ተብሎ የሚወሰድ ነበር። ንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ስለዚህ ሲያብራሩ "በኢትዮጵያ ሰፍና የምትኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት የአገልግሎት አካላዊ ዘርፎች አሏት። እነዚህም ቤተ ሕዝብ፣ ቤተክህነትና ቤተምልክና ይባላሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የታነጸበት ይህ የሦስትነት ባህርይ ምስጢር ሲሦ ለአነጋሽ፣ ሲሦ ለነጋሽ፣ ሲሦ ለቀዳሽ በሚለው ኪዳናዊ ይትበሃል የበለጠ ተተርጉሞ ጎልቶና ተብራርቶ ይታወቃል። ይህም ማለት በማናቸውም ረገድ የመንግሥቱ አንድ ሦስተኛ የሆነው ድርሻ የቤተሕዝቡ ሌላው አንድ ሦስተኛ የሆነው ድርሻ የቤተክህነቱ ሲሆን የቀረው አንድ ሦስተኛ የሆነው ድርሻም የቤተምልክናው ይሆናል ማለት ነው። /ኤርሚያስ ከበደ፤1993፤ ገጽ 68።/

የልቡናዬን ፈቃድ የምትፈጽም ታማኝ ሆይ ፊቴን አይተህ መረዳት ቻልክ። /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 54/

ክህነቱ ብልጫ ያለው እንዲሆን የሚደረገው ከሌሎቹ ብቻ አይደለም። ክህነቱ ከንግሥናውም ብልጫ አለኝ ማለቱን አይተውም። ሁለቱም ከይሁዳ ነገድ የተቀዱ ሆነው ይቅረቡ እንጂ ክህነት ብልጫ እንዳለው ማሳየቱን ይቀጥላል። ስለዚህ በገድሉ ጸሐፊ ባቀረባቸው የተለያዩ ሁነቶች ያንን የሚያሳዩ ድርጊቶች አሉ። ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የነገሥታቱን የአብርሃ አጽብሐን ሥራ ሁሉ እንዲባርክ ይደረጋል። ሌላው ቀርቶ የደከሙለት በክርስቶስ እንዲሠሩ የታዘዙትን ቤተመቅደስ ባርኮ፣ ታቦት አስገብቶ ቀድሶ አወድሶ ቤተመቅደስ የሚያደርገው ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው። ያለ እርሱ መባረክ መቀደስ የለም። እርሱ አውጋዥ ናዛዥ ነው። የነገሥታቱ አባት ነው። ነገሥታት አብርሃ አጽብሐ ለብፁዕና ለቅዱስ ለተመረጠ ከሣቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ "አንተ ከእኛ በረከት ትቀበል ዘንድ አይገባህም፤ እኛ ከአንተ በረከት እንቀበል ዘንድ ይገባል እንጂ አንተ የሁላችን የሥጋችንና የነፍሳችን አባት ነህና....."ይሉታል። /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 30/

ቤተክህነት በዚህ መሠረት ላይ ቆማ ነው- ቤተ ሕዝቡን ይዛ አንጋሽና ቀዳሽ የሆነችበትን ዕድል የምታሰፋው። በዚህም መሠረት ላይ ቆማ ነው። "እምነ መንግሥት የዐቢ ክህነት፣ ከመንግሥት ክህነት ትበልጣለች" የምትለው።[40] ይሔ ብልጫ ከሌለ ቤተመንግሥቱ ቤተክህነቱን እንደሆነ ይቆጠራልና። ይህንን ሲያደርግ ደግሞ ዎዝያናዊ ጥሰት[41] ፈጽሟልና ቤተክህነት ‹‹በዎዝያን መቅሰፍት ትመታለህ›› ትለዋለች።

3.2.2. አንድ ሕልም

> አብርሃና አጽብሐም ከእንቅልፋቸው ነቅተው የተደነቀ ድንቅ ሥራን ላደረገልን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። ብለው አመሰገኑ። ከዚህ በኋላ ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጋር ተገናኝተው ያዩትን ሁሉ ነገሩት፤ እሱም ያየውን ነገራቸው ሕልማቸውና ተመስጦአቸው ፍቅራቸው አንድ ሆነ። /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ገጽ 34/

---

[40] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት መሠረት ክህነት ሰማያዊ በመሆኑ፣ ንግሥናንም የሚባርከው ክህነት በመሆኑ ክህነት ከመንግሥት ይበልጣል የሚል እምነት አለ /ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፣1988።/

[41] ዎዝያን የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እንደ ካህን ቤተመቅደስ ገብቶ ለማጠን የደፈረና ካህናቱንም የናቀ ነበር። በዚህ ድፍረቱ በለምጽ የተቀጣና የተቀሰፈ ነበር። ‹‹ንጉሡንም ዎዝያንን እየተቃወሙ ዎዝያን ሆይ ዕጣን ማጠን የተቀደሱት የአሮን ልጆች የካህናቱ ሹመት ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባህም በድለሃልና ከመቅደሱ ውጣ፤ ከአምላክም ከእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አይሆንልህም አሉት፤ ዎዝያንም ተቆጣ የሚያጥንበትንም ጥና በእጁ ነበረ፤ ካህናቱንም በተቆጣ ጊዜ በካህናቱ ፊት በእግዚአብሔር ቤት ወስጥ በዕጣኑ መሠዊያ አጠገብ ሳለ በግምባሩ ላይ ለምጽ ታየ።›› /2ዜና መዋ. 26÷18-19/

በገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ውስጥ ካህኑ ተጋዳሊ ከነገሥታቱ ተጋዳልያን አብርሃና አጽብሐ ጋር በአንድ ቀን አንድ ሕልም እንዲያልሙ ይደረጋሉ፡፡ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን በድንግል ማርያም ወደ ሰማያት ተወስዶ በክብር ቦታ በንግሥና ስታስቀምጠው ያያል፡፡ አብርሃና አጽብሐም በድንግል ማርያም ወደ ሰማይ ተነጥቀው ይወጣሉ፤ የብርሃን ዘውድ የብርሃን ዙፋን /ወንበር/ ላይ ታስቀምጣቸዋለች፡፡

ለተጋዳሊ ካህኑ የሚሆነው ሁሉ ለተጋዳልያን ነገሥታቱ አይቀርባቸውም፡፡ ለነገሥታቱ የሆነውም ለካህኑ አይቀርበትም፡፡ የአብርሃ አጽብሐ ገድልም በነጻነት ይነገራል፡፡ አንድ አንዴ ተራኪው የሰላማ ከሣቱ ብርሃንን ገድል አቋርጦ ለተወሰኑ ቅጽበቶች አብርሃና አጽብሐን ገድል ሊነግረን ይጥራል፡፡ ገብቶ የነገሥታቱን ገድል ይነግረናል፡፡ የሚነገረው የማንኛው ገድል እንደሆነ መለየት በማያስችል ሁኔታ ተቀይጦ ይፈሳል፡፡ አንዳንዴም ሁለቱንም ወገኖች ባለቤት አድርጉ ይተርካል፡፡

> አምላክን የወለደች በሁለት ወገን ድንግል የምትሆን ቅድስት እመቤታችንን ልጇ እንዳነገሣት እንደ እርሷ ብፁዕና ቅዱስ አቡነ ሰላማ ከሣቱ ብርሃንንም አነገሠችው ነገሥታት አብርሃና አጽብሐን ከእርሷ ጋር ወደ ሰማይ ነጠቀቻቸውና በደስታ የመድኃኒት ዘወድን አቀዳጀታ የጽድቅን ቀሚስ አለበሰቻቸው የጽድቅንም መጎናጸፊያ ተጎናጽፋ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ፊት አከበረቻቸው ... ከዚህ በኋላ ብፁዕና ቅዱስ አቡነ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ከእንቅልፉ ተነሥቶ በነፍሱ ተደሰተ ...አብርሃና አጽብሐም ከእንቅልፋቸው ነቅተው የተደነቀ ደንቅ ሥራን ላደረገልን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ብለው አመሰገኑ ከዚህ በኋላ ከአቡነ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ጋር ተገናኝተው ያዩትን ሁሉ ነገሩት አርሱም ያየውን ነገራቸው... /ገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን፣ ገጽ 34/

እንዲህ ያለው መዋቅራዊ ሁኔታ ያለ አንዳች ፋይዳ የሚገባ አይሆንም፡፡ በካህኑና በንጉሡ ተጋዳሊ ዝምድና ውስጥ እውን እንዲሆን የሚፈለግ የማኅበረሰብ ራእይ አለ፡፡ ሁለቱም ከአንድ ምንጭ ይቀዳሉ፤ ወደ አንድ ሕዝብ ይፈሳሉ፡፡ ካህኑና ነገሥታቱ ሁለት ወገን ሲሆኑ አንድ ሆነው ሲራመዱ የሚታዩ ናቸው፤ አንድ ሆነው ሲታሰቡ ደግሞ ሁለት ሆነው ሲያስቡ፤ ሲሠሩ የሚገኙ ናቸው፡፡ ምንጫቸው ያው የይሁዳ አንበሳ ነው፡፡ የማፈሱትም "አግዓዚት ሀገር" በሚሏት በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ላይ ነው፡፡ አንድ ሕልማቸው አንድ ርእዮታቸው ነው፡፡ የሚሰበከው የሴም ገናናነት ነው፡፡ የሚያበራው የዳዊት ኮከብ ነው፡፡[42] ሁለቱም ከተባረከ ከተመረጠ ዘር ወጥተው አንድ ሥልጣን ተጋርተው በአንድ ሕዝብ ላይ የሠለጠኑ መሆናቸውን

[42] በኢትዮጵያ ቤተመንግሥቶች ጭምር/ ለምሳሌ በፋሲል ግንብ ላይ፣ ብሔራዊ ቤተመንግሥት/ በየአጥሮቻቸው ላይ የዳዊት ኮከብ የሚባለው የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ምልክት እስከ አሁን ድረስ እንደሚታይባቸው ልብ ይሏል፡፡ ይህ ምልክት በኢትዮጵያ ሥር ከሰደደው የሰሎሞናዊነት ባህል የመነጨ ነው፡፡

ይነግራል። አንዱ የአንዱን ክብር ይጋራል። ካህኑ ንጉሥ፣ ንጉሡ ካህን ሊሆን ይዳዳል። የቁስ ንጉሥ ዮሐንስ አፈታሪክ የዚህ ነጸብራቅ ነው።[43]

የቤተመንግሥቱ ሥራ የሚቀናው በቤተክህነቱ ትከሻ ነው። የቤተክህነቱም ሥራ የሚቀናው በቤተመንግሥቱ ትከሻ ነው። የመንግሥቱ ግዛት መስፋፋት የቤተክህነቱ ሀገረ ስብከት መስፋት ማሳያ ነው። ንጉሡ የረገጠውን ሁሉ ካህኑ ይረግጣል፤ ካህኑ የረገጠውን ሁሉ ንጉሡ ይረግጣል።[44] በተጋዳልያኑ የታየው አንድ ሕልም አንድ ተመስጥኦ የዚህ ርእዮት አንድነት ጠቋሚ ነው። ነገር ግን እንደ ተጋዳሊ አሸናፊ ሆነው እንዲወጡ የተዘጋጀላቸው የተጋድሎ ቅጽር የአጋንንት ተገዳዳሪነት ነው። ሁለቱም በአጋንንት የተመሰሉትን የዚህን አንድ ርእዮት ተቃዋሚዎች በያዙት በትረ ሥልጣን እየረቱ መቅደሱ ወዳለበት ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ይመለሳሉ። ቅድስቲቱ ከተማ የያዙት አንድ ርእዮት ተተክሎ ጸድቆ ያደገበት ማኅበረሰብ ማሳያ ነው።

3.2.3 መስበክና ማጥመቅ ለታላቁ ቤተመቅደስ

መስበክና ማጥመቅ በገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ተደጋግሞ የሚመጣ ወሳኝ መባያ ነው። ሰላማ ካህን እንደመሆኑ ዋነኛ ተግባሩ ሆኖ በገድሉ የሚነበበው መስበክና ማጥመቅ ነው። በኢትዮጵያ ከሐማሌን እስከ ሸዋ፣ ከጐጃም እስከ በጌምድር ተመላልሶ ሕዝቡን ያስተምራል። ያጠምቃል። ሕግና ሥርዓትም ይሠራል። ይህንን ሲያደርግ ደግሞ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እንዳይለየው ይደረጋል። የዚህ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ማሳያ ሆነው ሚካኤልና ማርያም ይገለጣሉ። በዚያ ረድኤት ተአምራትንም ይሠራል። እነዚህ ተአምራት ሕዝቡ እንዲጠመቅ የሚያነሣሡ ቀስቃሽ ክስተቶች ናቸው። አጥምቆ ሲያቆርብ የፀሐይ መጥለቂያ ይደርሳል፤ እርሱ ባለበት ግን ፀሐይ መጥለቅ አይሆንላትም፤ ትገዘታለች፤ ለሰላማ የማስተማር፣ የማጥመቅ ሥራ ተራዳኢ ትሆናለች። ለማስተማር ከአገር አገር ይዞራል፤ ወንዝ ይሻገራል። የወንዝ ሙላት ግን አያግደውም፤ ዓባይን የመሰለ ታላቅ ወንዝ በመጠምጠሚያው እየከፈለ እንዲሻገር ይደረጋል።

---

[43] በመካከለኛው የኢትዮጵያ የታሪክ ዘመን ውስጥ ያሉትን የኢትዮጵያ ነገሥታት ወይም ዐፄዎች የአውሮፓ ክርስቲያን ነገሥታት ግንኙነት ለማድረግ ሲፈልጉ የሚጽፉላቸው ደብዳቤ ከለአቢሲኒያ ንጉሥ ለቁስ ዮሐንስ /Prester Jhon የሚል እንደነበር ይገለጻል /Taddesse,1972, 257/

[44] የታደሰ ታምራት ማብራሪያ ለዚህ ሐሳብ አስረጂ ሊሆን ይችላል። "The evangelization of the Ethiopian region followed very closely the expansion of Christian state. The fourteenth century which was marked by the maximum expansion of the kingdom was also the period when the Ethiopian church exerted its pressures most on the non Christian peoples in the area The Shewan plateau which had increasingly come to be the most important theatre for the military activities of the Christian army also assumed a key position as the center for propagating Christian teaching among the conqured people." /Taddesse,1972,156/

ነገር ግን አንድን ተጋዳሊ የማይለዩት ተግዳሮቶች የሚሻገረው ቅጽር ሆነው እንዲጋረጡበት ይደረጋል። ለስብከት በሚመላለስበት ቦታ ሁሉ ሊያስተምረው የቀረበው ሕዝብ ይቃወመዋል። ይህንንም ሰይጣናት ያዘጋጁት ወጥመድ ይሆናል። በሐሰት ይከሰሳል። ለፍርድ ወደ ዳኛ ይቀርባል፤ ይሰደዳል። ጸሐፌ ገድሉ ይህ እንደሆነበት ብቻ ጽፎልን አይተውም፤ ይህንን ቅጽር ግን አልፎ የሚሻውን የሚፈጽምበት ኃይል ባለቤት ይሆናል።

ይህንን ተቃውሞ የሚረታ ሆኖ የሚሣለውም ከመጣበት ፈተና በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት በመጋረድ፣ ሊጐዱት የተነሡት ሰዎች ተቀስፈው ካልሆነም በሌላ ተአምራት በመሥራት ይሆናል። ሕፃን እንደ ገደለ አድርገው የከሰሱትን ለማሳፈር ለመርታት የሞተውን ሕፃን በማስነሣት ገዳዩ /ሰላማ ከሣቴ ብርሃን/ አለመሆኑን ያስመሰከራል። ከሙት የሚያስነሣቸውም ሁሉ የእርሱን ስብከት ሰብከው ዳግም በዚህ ዓለም መኖርን ጠልተው ወደ መቃብር ይመለሳሉ። ፈውስና የሙታን ትንሣኤ በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ተአምራት ሆነው ግባቸው ግን የሰላማ ከሣቴ ብርሃንን የመሰበክና የማጥመቅ ሥራ ማቅናት ይሆናል።

ሰብኮ አጥምቆ ግን ማረፊያ ወደቡ ሆኖ በገድሉ የሚጠቀስልን አክሱም ይሆናል። አክሱም ነገሥታቱ የሠሩት በእርሱ የተባረከው ቤተመቅደስ ያለባትና በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አምሳል የተሠራች ከተማ ሆና በገድሉ ገለጻዎች ወስጥ ትታያለች። የገድሉ ጸሐፊ ግን ሰላማ ነገሥታቱ በሠሩት ቤተመቅደስ በሠሩት ከተማ ብቻ እንዲወሰን አይሻም። ከዚያ አሻግሮ የበቃና ተወዳደሪ አሸናፊ እንዲሆን ያደርገዋል። ንግሥናው ከክህነቱ እንዳይበልጥ እርሱም ከተማና መቅደስን መሥራትን ይሻል። እርሱ የሚሠራው ከተማና መቅደስ የሚገነባው ግን በስብከቱና በጥምቀቱ ይሆናል። ይህንን ሲያደርግ ግን ለነገሥታት ተጋዳልያኑ የሆነው ሁሉ አይቀርበትም። እርሱም የሚሠራውን ከተማ መቅደስ አምሳል ለማየት ወደ ሰማያት መጓዝን ይሻል። "እኔ ነፍሴ ከሥጋየ ሳትለይ የምኖርበት ማደሪያየንና የነቢያት የሐዋርያት፣ የደናግል የመነኮሳት ማደሪያቸውን አይ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ...." /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 53/ ይህንን የቅዱሳን ማደሪያ ያለውን የሰማይን ከተማ ማየት የሚፈለገው በዚያ አንጻር የሚሠራው ከተማና መቅደስ ስላለ ነው።[45] ስለዚህ ተጋዳሊው በሰማይ ያለውን ከተማና መቅደስ አየ።

[45] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን የሚባለው ሕንጻው ብቻ አይደለም፤ ገብኤው ሕዝቡ የምእመናን ኅብረት ቤተመቅደስ ይባላል። /ኅርኅርዮስ፣ 1974/ በመጽሐፍ ቅዱስም ተመሳሳይ እሳቤ አለ። "በሐዋርያት በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል። የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በእርሱም ሕንጻው ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ" /ኤፌ 2፡20/

የሰማይ ከተማ የሰማይ መቅደስና ታቦት የተሠራው በቅዱሳን ሰዎች ነው፡፡[46] ስለዚህ ይህንን ከተማና መቅደስ ይሠራል፡፡ ስለዚህ በዚህ ከነገሥታት ተጋዳልያኑ አያንስም ኢትዮጵያን ከተማ አድርጐ ክርስቲያኖችን መቅደስ ያደርጋል፡፡[47] በዚያም ውስጥ ካህን ሆኖ ያገለግላል፡፡

ይህ ጸሐፊ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ ራእይ ነው፡፡ በዚህ ተጋዳሊ በኩል ሊይዝ ሊጨብጥ የሚፈልገውን ታላቅነት በዚህ ተረክ አንጸባርቋል፡፡ በገድሉ የተመለከተውን የሚከተለውን የጸሐፊ ገድሉን መንደርደሪያ ሐሳብ ስናነብ ማኅበረሰቡ ተጋዳሊውን ያበቀለበት ዓላማ ይገባናል፡፡

> በብፁዕና በቅዱስ አቡነ ሰላማ እጅ በአክሱም ሀገር ቅብዐ መንግሥትን የተቀቡ የኢትዮጵያ ነገሥታት የሚሆኑ በደጋጐች አብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት በእስክንድርያ ሐዋርያ ከሚሆን ከማርቆስ ወንበር ተገኝቶ የወጣ <u>የአግዓዚት ሀገር</u> ሊቀጳጳስ የብፁዕና የቅዱስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሐምሌ ሃያ ስድስት ቀን የሚነበበውን የዜና ገድሉን መጽሐፍ እንጀምራለን፡፡ ሰላማም ማለት የስሙ ትርጓሜ የሰላማ የፍቅር የዕረፍት የተድላ የደስታ የጸጋ የሞገስ ዘመን ማለት ነው፡፡ አግዓዚትም ማለት <u>ትርጓሜው ታዛዥ ነጻ የወጣች</u>፣ በእግዚአብሔር የተመነች ታማኝ ተገዢ የወንጌል ታዛዥና ፈጻሚ የወልድ ሙሽራ ማለት ነው፡፡ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን የዚህች ቤተመቅደስ ልጆች ከምንሆን ከትንሹና ከትልቁም ጋር ይሁን፡፡ /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ገጽ 52/

በተጋዳሊው ተጋድሎ ውስጥ ማኅበረሰቡ ሊያገኘው የፈለገው በረከት ይሔንን መቅደስና ከተማ መሆን ነው፡፡ ጸሐፊው የዚያ ማኅበረሰብ አባል ነውና ያንን ሥነልቡና በጻፈው ገድል ውስጥ ያስተጋባል፡፡ በዚህ ውስጥ ነጻነትን ሃይማኖታዊ /የአምልኮ/ መንፈስን የተላበሰች ሀገር ባለቤት መሆን ይመኛል፡፡ "የወልድ ሙሽራ" መባሏም ዮሐንስ በራእዩ "ቅድስቲቱ ከተማ ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ /ራእ 21.2/፡፡

---

[46] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቅዳሴ ቃላት ውስጥ ይህንን የሚገልጹ በዜማና በንባብ የሚባሉ ቃላት አሉ፡፡ በቅዳሴ ማርያም ውስጥ ያለው የዚህ መልክ ያለው ቃላት የሚከተለውን ይመላል፡፡«የእሳት ነበልባል ደንኊኖች ወደተተከሉባት፣ የካህናት አለቃ ወዳለባት ያግባችሁ፤ የተሳለ የፊቱ መልክ በዚያ አለ፡፡ ንጹህ አክሊልና ብሩህ ልብስ ከዚያ አለ፡፡ እርሱም ከላይ የተገኘ ነው እንጂ የሰው ልጅ ያልተጠበበበት ነው፡፡ የቅዱሳን ነቢያት ማኅበር ወዳለበት ያገባችሁ፤ ያሰተማሩ የሐዋርያትም ማኅበር፣ ድል የነሡ የሰማዕታትም ማኅበር፣ ብሩካን የሚሆኑ የጻድቃንም ማኅበር የተሾሙ፤ የካህናትም ማኅበር፣ ትጉኃን የሚሆኑ የመላእክትም ማኅበር፣ የፍጡማን ደናግላን የመነኮሳት ማኅበር ወዳሉበት ያገባችሁ፡፡ ከሁሉ በላይ ከሆነች ከአንዲት ቤተክርስቲያን ፍጡም እንድነቷ ሁሉ ጋር ከእነርሱም ጋር ታቦት ዘዶር ወዳለችበት፤ ይህቺውም እመቤታችን ማርያም ናት፡፡.... ››/ ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፣ 1993/

[47] ይህ ክረስቲያኖችን መቅደስ አድርጎ የመውሰድ እሳቤ በኦርቶዶክስ ክርስትና ዓለም ያለ ጉልህ እሳቤ ነው፡፡ ስለዚህም የኦርቶዶክ ክርስትና ታዋቂ ቴዎሎጂያን የሆኑትን የቁስ ታወድሮስ ማላቴን ጽሑፍ ማስረጃ ማድረግ ይቻላል፡፡ ‹‹This is the new temple to which the Lord /Christ/ drew our attention when he said 'Destroy this temple and in three days I will raise it up again …but the temple He was speaking of was his own body ' (Jn.2:19,20). As aresult His incarnation has replaced God's dwelling among his people in the past . His body and blood are offered to them so that they may abide in Him and unite with Him as branches in the One Vine. They become 'members of his body,' a temple of God as the apostle says '…do you not know that your body is a temple of the holy spirit within you which you have from God '(1 cor.6:17).'' /Malaty, 2004, 16-17/

ካለው ጋር ይገጥማል፡፡ "ቤተመቅደስም" አላት ማኅበረሰቡ ራሱን የዚህች መቅደስ ልጅ አድርጐ ያስባል፡፡ ስለዚህ በተጋዳሊው ተፈልጐ የሚገኘው በረከት ይህ መመረጥ ነው፡፡ ይህ መቀደስ ነው፡፡

3.2.4 የተባረኩ ምንጮች

በገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ውስጥ ምንጮችን መባረክ አንድ ወሳኝ የመባያ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ አንዳች ትእምርታዊ ፋይዳም ያለው ነው፡፡ "በዚያች ደብረ ምስጢርና ደብረ ምስራቅ በምትባል ደብር በምሥራቁ በኩል ሁለት የውሃ ምንጮችን ሠራ፡፡ በክረምትና በበጋ በወደይና በመዉውም ቢሆን ከውስጧ ውሃ እንዳይታጣ በመስቀል ምልክት አማትቦ ባረካት" /ገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን፣ ገጽ 18/

ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ውሃ በታጣበት ሁሉ ምንጭን እንዲያስፋፋ ይደረጋል፡፡ ጸሐፊው ከተጋዳሊው መንጭቶ ለተከታዮቹ የሚፈስ የበረከት ጎርፍ መኖሩን በምድረ በዳ በሚከስታቸው ምንጮች ሊጠቁመን ይጥራል፡፡ ከዚያም ምንጭ የሚወጣው ውሃ ወቅትና መልክአ ምድር ሳይገድበው ለተጠሙት ሁሉ የሚፈስ ነው፡፡ የሚፈልቀውን ውሃ ከግዮን፣ ከኤፍራጥስ ወንዞች ውሃ ጋር ያነጻጽረዋል፡፡ ተጋዳሊው ያንን እንዲያደርግ የሚፈቅደው ግን ለወዳጆቹ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ቃሉን ለሚሰሙ የእርሱን ሕግና ሥርዓት ለሚቀበሉ ይሆናል፡፡ ለዚህም ማሳያ ሆኖ የቀረበው ሁነት እርሱ ሕፃን እንደገደለ አድርገው የከሰሱትን ሰዎች ሕፃኑን ከሞት አስነሥቶ እርሱ አለመግደሉን ካስመሰከረ በኋላ እነዚያን የተቃዋሚዎች ሀገር ይረግማል፡፡ ከዚያ ፈቅ ብሎ የወዳጆቹን ሥፍራ ያገኛል፡፡ በዚያ ሥፍራ ከተራራው ሥር ውሃን አመንጭቶ ምድሩን ያረሰርሳል፡፡ /ገድለ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን፣ ገጽ 22/

በመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውሃ የንጽሕና፣ የሕይወት፣ የመልካም ሥራ የዕውቀት ምሳሌ ነው፡፡ ለምሳሌ ሶልከው የገቡ ሴሰኞች የተባሉ የሃይማኖት ተቃዋሚዎችን "በነፋስ የተወሰዱ ውሃ የሌለባቸው ደመናዎች፤ ፍሬ የማያፈሩ....." እያለ ይገልጻቸዋል፡፡ /ይሁ 1.12/ ተጋዳሊው እንዲሠራ የሚደረገውም የውሃ ምንጭ በተጋድሎው ፍጻሜ የሚያመጣውን በረከት ለሚጠባበቁ ተከታዮቹ ያመጣላቸውን የሃይማኖት ሕይወት፣ የሃይማኖት ዕውቀት፣ የሃይማኖት ሥራ ሁሉ የሚያሳይ ይሆናል፡፡ ከዚያ በፊት ከዚህ ከተጠማ ማኅበረሰብ ውስጥ መመላለሱን እናያለን፡፡

ይህ ለተጋዳሊው አስቀድሞም በተጻፈለት ንግር ውስጥም እናገኘዋለን፡፡ ሕፃኑ ሰላማ በሊቀጳጳሱ ጢሞቴዎስ እቅፍ ሆኖ "ለኢትዮጵያ ሀገር ብርሃን ይሆናቸዋል፣ በረሃብ ዘመን ጥጋብ በጥማት ዘመን መጠጥ በእርቃን ዘመን ልብስ፣ በሐዘን ዘመን ደስታ በችግር ዘመን መጠጊያ

ይሆናቸዋል፡፡" /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 4/ ተብሎ ትንቢት እንዲነገርለት ተደርጎ ፍፃሜውም እንዲታይ የማድረግ አካሔድ ነው፡፡ የሚያንጻቸው ምንጮች፣ የሚያፈሰው ምድርን የሚያረሰርስ ውሃ በተከታዮቹ የሚፈለጉ፣ ቀድመው በትንቢት የተነገሩ በረከቶች ናቸው፡፡ እነዚህን በረከቶች ለማምጣት ካምቤል ባስቀመጠው የተጋዳሊው የገዛ ምዕራፎች ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ ስለዚህ ጠላቶቹን ማሸነፍ መርገም ቅጽሮችን ሁሉ መሻገር ይጠበቅበታልና እንዲሁ ሲሆን ገድሉ ያሳየናል፡፡

ያንን የጠላቶቹን መሰናክል አልፎ ወደ ተራራ ይጓዛል፡፡ ከተራራውም ሥር ያንን በረከት ያፈልቃል፡፡ ከሰላማ ከሣቴ ብርሃን መምጣት በፊት ኢትዮጵያ የዚህ በረከት ባለቤት አልነበረችም፡፡ ያልበራላት ነበርና ያበራላታል፡፡ ተርባ ተጠምታ ነበርና ያጠጣታል፡፡ ሐዘንተኛ ነበረችና ያጽናናታል፡፡ ይህ ጸሐፌ ገድሉ ያለበት የማኅበረሰቡ ጥማት ነው፡፡ በተጋዳሊው በኩል ጥማቱ እንዲረካ መፈለጉን ይነገረናል፡፡ ለዚህም ነው ከሰላማ ከሣቴ ብርሃን በፊት ስለነበረችው ኢትዮጵያ ጸሐፌ ገድሉ ሲያብራራ /ሲገልጽ/ "ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ያዘኑትና የተከዘች ነበረች" /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 24/ ይለናል፡፡ ይህን ትካዜ ያራቀው በተጋዳሊው በኩል ማኅበረሰቡ የሚፈልገው ሥርዓት ነው፡፡ የሚፈልገው ርእዮት ነው፡፡ ይህ ሥርዓት መምጣቱ ነው ኢትዮጵያን እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ለመዘርጋት የሚያበቃት፡፡ ከዚያ ‹‹ቅድስት ሀገር›› ትሆናለች፡፡ ማኅበረሰቡ በዚሁ ሥርዓት ራሱን የተመረጠ ማድረጉን ይቀጥላል፡፡ ምንጮች የተባሉ ካህናቱ፣ መሳፍንቱ፣ ሁሉ ለመቅደሷ ምክንያት የሚሆን ዕውቀት፣ ሕይወት፣ ንጽሕና ይላበሳሉ ሊለን ይፈልጋል፡፡ እነዚህ ምንጮች የማይነጥፉት ግን ከይሁዳ አንበሳነት የሚመነጨው ሰሎሞናዊው ቤተመንግሥትና ቤተክህነት ቡራኬው /ቁጥጥሩ/ እስካለ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ ጸሐፌ ገድሉ እንዲህ ይለናል

> ያን ጊዜ ጽዮን በብርሃን ድንኳን ነበረች፡፡ ከሴም ዕጣ የሆነ የዕሴይ ልጅ የነቢዩ ዳዊት ልጅ የሰሎሞን ልጅ የሚሆን ምኒልክ ከአመጣት በኋላ በአክሱም አገር ቤተክርስቲያን አልተሠራላትም ነበር፡፡ ይህችም ሀገር ከዓለም ሀገሮች ሁሉ የሃይማኖትና የጽድቅ ሀገር ናት፡፡ ጽዮን በውስጧ ትኖር ዘንድ ያቺን ሀገር መረጠቻት፡፡ /ገድለ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣ ገጽ 25 /

ይህ መጠሪያዋ የመጣው ስለተጋዳሊው ሰላማ በሚጽፍልን በደራሲው በኩል የሚስተጋባው፣ ማኅበረሰቡ የሚሻው ሥርዓት በኢትዮጵያ ከተተከለ በኋላ ይሆናል፡፡ ሥርዓቱ፣ ጽዮናዊ ሆኖ መመረጡ ይኖራል ማለቱ ነው፡፡

3.3. ገድለ ላሊበላ

ገድለ ላሊበላም ከነገሥታት ቅዱሳን ገድል አንዱ ነው፡፡ በዚሁ ገድል በተደጋጋሚነት ጎልተው የታዩ ወሳኝ የመባያ ጉዳዮችን ለይቼ አስቀድሜ ባቀረብኩት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ለመተንተን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ እነዚህ የመባያ ጉዳዮች ከአብርሃ አጽብሐ ገድል ጋር እጅግ ተመሳሳይ ሲሆኑ ገድላቱን ለማነጻጸር የተመቹ ናቸው፡፡ ክርስቶስን መምሰል ፣ገዛ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትና ምድራዊት፣ የጽድቅ ትሩፋትና መቅደሱ የተባሉ ናቸው፡፡

3.3.1 ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል

በካምቤል ሐሳብ መሠረት በተጋዳሊ እርምጃ ወስጥ ቀዳሚ ምዕራፍ በሆነው "መጠራት /መለየት/" ውስጥ ተጋዳሊውን ገና ከዕንስና ከልደት የሕይወት ክፍል አንሥቶ ለተባሩ ለተጋዳሊው ዕጣ ፈንታ አመላካች /ንግር/ የሆኑ ተአምራዊ ክስተቶች ይታያሉ፡፡ ይህ በገድለ ላሊበላም የሚስተዋል ነው፡፡ በዚህ ጥሪና ለተጋድሎ የመለየት ደረጃ ውስጥ በንጉሡ ተጋዳሊ ላሊበላ የሚታየው ኢየሱስን መስሎ የመጠራት ፋይዳ ግን ተደርቦ መስተዋል ያለበት ሁነት ነው፡፡

3.3.1.1 ዐውደ ልደት

ተጋዳሊውን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ማመሳሰል በገድለ ላሊበላ የሚንጸባረቅ አንዱ ገጽታው ነው፡፡ ይህም በተጋዳሊው የመለየት/ኅርየት/ ምዕራፍና የተጋድሎ ምዕራፍ ላይ ነው፡፡ በነገሥታት ተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ የታየው በጽንስና በልደት ቀን ኢየሱስን አስመስሎ የማቅረብ ስልት በንጉሡ ተጋዳሊ ላሊበላም ገድል ውስጥ ይታያል፡፡ ላሊበላ የሚወለደው በታኅሣሥ 29 ቀን ይሆናል፡፡ መወለዱ ብቻ ሳይሆን በተወለደበት ሂደትና ዕለት ታዩ የምንባለው ትዕይንቶች የመመሳሰሉን ነገር በጉልህ ያሳያሉ፡፡

የላሊበላ እናት ሳትወልድ በመኖሯ የምታዝን መካን ነበረች፤ የኢየሱስ እናት ድንግል ነበረች፡፡ እውነታዎቹ የተላያዩ ሆነው አለመውለድን ለመውለድ ካለመዘጋጀት ጋር አቀራርቦ ለመጻፍ የበቃ ይመስላል፡፡ የላሊበላን እናት ራእይ ታያት መልአኩ ሚካኤል ልጅን እንደምትወልድ አበሠራት፣ የኢየሱስ እናት በድንግልና ልጅን እንደምትወልድ ገብርኤል አበሠራት፤ ላሊበላ በተወለደ ጊዜ ንቦች ከበቡት ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ መላእክት፣ እረኞች፣ ሰብአሰገል ከበቡት የላሊበላን መወለድ ንብ አበሠረ፣ የኢየሱስን መወለድ ኮከብ አበሠረ፡፡ እነዚህንና እነዚህን

የመሰሉ ሁነቶች በላሊበላ ልደት የተከሰቱ ናቸው፡፡ በነገሥታት ተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ ልደትም የዚህኑ ትዕይንት ግልባጭ አይተናል፡፡

ሌላው ነጥብ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ተወለደ የተባለው የአይሁድ ንጉሥ ነው፡፡ ሰብአ ሰገልም ሊሰግዱለት በመጡ ጊዜ ሥፍራውን ይጠይቁ የነበሩት "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?" እያሉ ነበር /ማቴ 2.1/፡፡ ይህንን በሰማ ጊዜ የደነገጠውም በጊዜው ንጉሥ የነበረው ሄሮድስ ነው፤ አሳዳጁም ሆነ፡፡ ኢየሱስ ንጉሥን መሲህ /ክርስቶስ/ ሆኖ ሕዝቡን ነጻ የሚያወጣ ሆኖ ተወልዷል፡፡ ንጉሥና መሲሕ የመባሉ ነገር በገድለ ላሊበላ ውስጥ ፋይዳ አለው፡፡ ወንድሙም በቅንዓት ሲያሳድደው እናነባለን፡፡

3.3.1.2 ንግሥና

አስቀድሞ በታሪኩ በልደት ኢየሱስን አስመስሎ ተጋዳሊውን መሣሉ የንግሥናው ዕጣ ነጋሪ መሆኑ ነው፡፡ "የተወለደው ንጉሥ ነው" ለማለት የቀረቡ ትእምርቶችም አሉ፡፡ እነዚያንም ትእምርቶች ገድሉ መልሶ ይተረጉማቸዋል፡፡ ለዚህ የሚጠቀሰው በተወለደ ጊዜ የከበበው የንብ መንጋ በንግሥናው ለሚሰበሰበው ሠራዊት አምሳያ አድርጐ ማቅረቡ ነው፡፡ "ንብም በንጉሥ ሠራዊት ይመሰላል፤ መርዛቸውም ሰውን በሚጐዱበት በንጉሥ ሠራዊት ጦር መሣሪያ ይመሰላል፡፡ ንጉሥን የከዱ ዐላውያንን ድል በሚነሡበት ንጉሥ ላሊበላ ንጉሥ ይሆን ዘንድ አለውና ስለዚህ ንቦች በንጉሥ ሠራዊት አምሳል ከበቡት...›› /ገድለ ላሊበላ ገጽ፣ 116/

ጸሐፌ ገድሉ ይህንን አምሳያ በተጋዳሊው የመለየት ምዕራፍ አምጥቶ ቀጣዩን የታሪኩን ትልም የቀና፡ያደርጋል፡፡ ንጉሥ መሆኑን ማመላከት ብቻ ሳይሆን ነባሩ ንጉሥ በካህናት አለቃ አንጻር ዘመዶቹ በሰጡት ምክር ተነሣስቶ ላሊበላን ሊያሳድደው ይነሣል፡፡ ከክርስቶስ ያለው ልዩነት ስደቱ በግብፅ መሆኑና በኢየሩሳሌም መሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ ክርስቶስን የመምሰሉ ዋነኛ ፋይዳ ንጉሥ ተጋዳሊ ነውና ንግሥናውን ነጋሪ ሆኖ ነው፡፡ ንግሥናው ግን ከሌሎች የተለየ የሚሆነው አንዳች ሃይማኖታዊ ተልእኮ ለመፈጸም የተለየ /የተጠራ/ መሲሕ ሆኖ እንዲሣል በመደረጉ ነው፡፡ ክርስቶስ ንጉሠ አይሁድ ሆኖ ነባሩን መቅደስ አፍርሶ ራሱን ነጻ የሚያወጣ አድርጐ ያቆማል፡፡ ንጉሥ ላሊበላም የፈረሰውን /ሕዝቡ ያጣውን/ የሰሎሞን መቅደስ[48] ተክቶ በዳግማዊት ኢየሩሳሌም /ሮሃ/ ነጻ የሚያወጣ መቅደስ ይሠራል፡፡

---

[48] ሰሎሞን በዘመኑ የሠራውን ታላቁን የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 ዓ.ዓ በሴዴቅያስ ዘመን፡የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነጾር አፍርሶ አቃጥሎታል፡፡ በኋላ ዘሩባቤል የሠራውና ንጉሥ ሄሮድስ ያሳደሰው ቤተመቅደስ በምትኩ ተሠርቶ የቆየ ቢሆንም በኋላ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ70 ዓ.ም የፈረሰና ኢየሱስም እንደሚፈርስ ትንቢት የተናገረበት እንደሆነ ይታመናል፡፡ /ዘካርያስ ተኮላ፣ 1993 ዓ.ም/

3.3.1.3 ሞትና ትንሣኤ

ንጉሡ ተጋዳሊ ላሊበላ ግን ኢየሱስን እንዲመስል የሚደረገው በመወለድ ብቻ አይደለም በሞትና ትንሣኤውም ነው፡፡ "ቅዱስ ላሊበላም ለሞት እስኪደርስ ድረስ ጸናባቸው፡፡ ለውሻውና ለሰው ሞትን የወለደች ይህቺን የሞት ጽዋ ጠጥቷልና፡፡ እርሱን መጠጣቱ የገደለችው አይደለም፡፡ የሰማይና የምድር ምስጢርን ገለጠችለት እንጂ እሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተመሳሳይ ነውና፡፡" /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 57/

ላሊበላ ጠላቶቹ ያዘጋጁለትን መርዝ ጠጥቶ ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ለሦስት ቀናት ከቆየ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነሣል፡፡ ይህ ተጋዳሊው የሚፈለገውን በረከት ይዞ ለመመለስ ዕድል ያገኘበት የተጋድሎ ቅጽርና የድል ዓውድ መሆኑ ነው፡፡ ይህንን ሞትና ትንሣኤውን ገድሉ ሲያብራራ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ተመሳሳይ ነው፡፡" ማለቱ የማመሳሰሉ ነገር ይሁነኝ ተብሎ የተደረገ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ተጋዳሊው ክርስቶስን እንዲመስል የሚደረግበት ሌላው ሁነት ሞትና ትንሣኤው ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐ በጥምቀት ኢየሱስን እንዲመስሉት ይደረጋል፡፡ ላሊበላ ደግሞ በሞትና ትንሣኤ፡፡ እነዚህ ሁለት ጽንሰ ሐሳቦች ተዛምዶ አላቸው፡፡ ታሪኩም በዚህ የተዛምዶ እሳቤ ላይ ቆሞ የታሪኩን ትልም ያቀናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤ ጥምቀትና ሞት /መቃብር/ አሮጌውን ነገር የመተው ወደ አዲሱም የመድረስ፣ አዳፋውን የማጠብ ንጹሑን የመልበስ፣ ጨለማውን የመጣል ወደ ብርሃን የመቅረብ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ጸሐፊው ብዙ ርእዮቱን በቀዳበት በመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤ በጥምቀት የሚገኝ አዲስ ተፈጥሮ በትንሣኤ ከሚገኝ አዲስ ሕይወት ጋር ይዛመዳል፡፡[49]

በላሊበላ ተጋዳሊነት የሚገኘው በረከት እንደመጣ ለተጋዳሊው የሚገባውን መለየትና ዳግም ልደት በዚህ ኢየሱስን በመሰለበት ሞትና ትንሣኤው በኩል ይሰጠዋል፡፡ የአይሁድ ንጉሥ የኢየሱስ ሞት በፈቃዱ የተቀበለው ሆኖ ለሌሎች ሕይወት /በረከት/ እንደሰጠ ይተረክልናል፤ እንዲሁ ንጉሡ ተጋዳሊ ላሊበላም በፈቃዱ የመርዙን ጽዋ አንሥቶ በመጠጣት ሞትን ተቀብሎ ለብዙዎች ሕይወት የሚሆን ቤተመቅደስ ለመሥራት የበቃ መሆኑን ማመላከት የጸሐፊ ገድሉ ሐሳብ ነው፡፡

---

[49] "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡" /ሮሜ 6.4/

በአጠቃላይ ሲታይ በንጉሥ ላሊበላና በኢየሱስ መካከል ያለው ተመሳስሎ ላሊበላን ንግሥና የሚገባው ለማኅበረሰቡ የተመረጠ፣ የተለየ፣ ነጻ ንጉሥ ሆኖ የመሰጠቱ ንግር ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃን ሆኖ ግዛት እንዳለው ሳያውቅ ግዛቱ ይታወቃል፤ ሳይሾሙት መሾሙ፣ ገዢ ሳይሆን ግዛቱ፣ መስፍን ሳይሆን ምስፍናው ቀድሞ የሚታወቅ ይሆናል፡፡

የጸሐፌ ገድሉን ሥነልቡና የሠራው ማኅበረሰብ የሚጥለው አሮጌ ነገር፣ የተጫነው አንዳች ቀንበር፤ የታከተው አንዳች ሥርዓት እንዳለና አዲስ ሕይወት፣ ነጻነት፣ አዲስ ሥርዓት መናፈቁን ያሳያል፡፡

ላሊበላ "ንጉሥ ሊሆን ነው" እየተባለ ተፈዘዝበታል፤ ከሰው ተገልሎ ኖሯል፤ በዱር በገደል እየተራበ እየተጠማ ኖሯል፤ ዳዊት ከሳኦል እንደሸሸ ከወንድሙ ከንጉሥ ሀርበይ ሸሽቶ ኖሯል፡፡ በሀሰት ተከሷል፤ ተገርፏል፤ ወደ ኢየሩሳሌም ተሰዷል፤ በመርዝ ሞቷል፤ ከሞት ተነሥቷል፡፡ ይህንን የሚመስሉ ነገሮች ሁሉ ስለ ኢየሱስ በሚናገሩ ተረኮች ውስጥ አሉ፡፡

3.3.2 ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም

ለክርስትና ሃይማኖት አገልግሎት በሚሰጡ ሚቶች ሁሉ ተጋዳሊው መቅደስ የሚባለውን በረከት ለተከታዮቹ ለማምጣት በተጋዳሊነት ፈለጎች ሁሉ የሚያልፍ ከሆነ ቅድስተቱን ከተማ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ሣይረግጥ እንዲያልፍ አይደረግም፡፡ ያቺ ቅጽር መቅደሱ ያለበት ተጋዳሊው በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት የሚሻገራት ቅጽር ናት፡፡ ላሊበላም ንጉሥ ተጋዳሊ ሆኖ በተጋድሎው ሊያመጣ የሚፈለገው ይህንን መቅደስ በመሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ሚታዊ ጉዞ የገድሉ ወሳኝ ክፍል ነው፡፡

የገድሉ ጸሐፊ ላሊበላ እንዲያልፍበት በሚሻው የጉዞ ምዕራፍ ሁሉ በየመዓርጋቱ ከሚያጋጥሙት ልብ ሰቃይ ትዕይንቶች ጋር ይተርክልናል፡፡ ላሊበላ በመልአኩ በገብርኤል ረድኤት በመጀመሪያው ሰማይ ያጋጠመውን የርኩሳን መናፍስት ጩኸትና ተቃውሞ ሰብሮ ቅጽሩን ያልፋል፡፡ በሰማይም በየማዕረጋቱ ሰባቱን ሰማያት ይጐበኛል፡፡ በዚህ ጉዞው በቀጣይም በተጋዳሊነት ጉዞው ከሚኖረው ሚና ጋር የተያያዙ መንገድ ጠራጊ ሁነቶች ይገለጻሉ፡፡ ለቤተመቅደስ ሥራ የመመረጡ ነገር፣ የመቅደሱ አሠራር ሥርዓትና የቅብዐ መንግሥቱ ጉዳይ ነው፡፡

ላሊበላ በደረሰባቸው በሰባቱም ሰማያት በመላእክትና በሰዎች ነፍሳት ወደፊት ስለሚሠራው መቅደስ እንዲደነቅ፤ እንዲመሰገንም ይደረጋል፡፡ ገብርኤልም ወደ እነዚህ አድናቂ መላእክትና ነፍሳት እንዳደረሰው ይተረክልናል፡፡ ሲያዩት የሚሰግዱለት የሚያመሰግኑት ይኖራሉ፡፡ እርሱም

የሚያየውን የሰማይ ምስጢር ሁሉ ያደንቃል፡፡ የሚሰግዱለት እነርሱ ደግሞ በእርሱ እጅ ገና ወደፊት የሚሠራውን መቅደስ ያደንቃሉ፡፡ በሰባተኛው ሰማይ ግን ከአምላኩ ጋር ይገናኛል፡፡

ይህ ሁሉ ጸሐፊ ገድሉ የተጋዳሊውን መመረጥ ለማጉላት ያስገባው ግነት ነው፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው የሚሠራውን መቅደስ ልዕልናና ክብር ሊነግረን የሚፈልገው በሠሪው ልዕልናና ክብር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ተደራሲው የመቅደሱን ልዕልናና ክብር አስቀድሞ በሠሪው ልዕልናና ክብር ምክንያት አምኖ ሥራውን በቀጣዮቹ ምዕራፎች ይጠብቃል፡፡ እንዲህ ያለ ጠቢብ፣ ጻድቅ ክቡር ንጉሥ ይገባናል ይላል፡፡ መቅደሱ የሚታነጸው ልዕለ ተፈጥሮ ለዚህ በለየው፣ ለዚህ መዓርግ በተገባ ቅዱስ ንጉሥ መሆኑን፣ የላሊበላን መመረጥ በሰባቱ ሰማያት ጉዞው ውስጥ ያሳያል፡፡ እንዲህ ያለ ንጉሥ ይገባናል ይላል፡፡

ሌላው ነጥብ የመቅደሱ ሥራና አሠራር ሥርዓት መታወጅ አለበት፡፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያ የሚሆነው መቅደስ ሥርዓት አስቀድሞ ለሙሴ የተነገረ ነው፡፡ አዲሱ መስፍን ንጉሥ ላሊበላም ከሙሴ የተሻለ መቅደስ ይሠራ ዘንድ እንደ ሙሴ ሊታዘዝ ይገባዋልና እንዲህ ባለ ሁነት ውስጥ እርሱን ማሳለፍ ለጸሐፊ ገድሉ አስፈላጊ ይሆንበታል፡፡ ስለዚህም ሙሴ ወደ ሲና ተራራ እንደወጣ እርሱ ግን ከፍ ከፍ ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት /ሰባቱ ሰማያት/ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በዚያ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ይቀበላል፡፡ የላቀና የተገባ መቅደስ ለመሥራት ከሙሴ የማይተናነስ እንደውም የላቀ የመታዘዝ ሥርዓት ውስጥ ሲያልፍ ያሳየናል፡፡ በሲና ተራራ ሳይሆን ከፍ ከፍ ብሎ በሰማያት የታዘዘ ከሆነ መቅደሱም ከሙሴ ድንኳን ከፍ ከፍ ያለ እንደሚሆን አመላካች ነው፡፡ "የማሳይህ ለሙሴ እንዳሳየሁት አይደለም፤ መቅደሴን የምትሠራልኝም ሙሴ እንደሠራው አይደለም፡፡" /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 84/

ስለዚህ በዚያው ስለ መቅደሱ ሥራና ሥርዓትም ተነግሮት እንዲመለስ ማድረግ ሌላው አስፈላጊ ነገር ይሆናል፡፡ የሚሠራውም በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም አምሳል እንደሆነ ይነገረዋል፡፡ በሥራው የመላእክት ተራዳኢነት አንደማይለየው ይነገረዋል፡፡ የባስልኤል ልጆች ጥበብ በሙሴ ድንኳን እንደታየ እነዚህን መሰል ጠቢባንም እንደሚታዘዙለት ይነገረዋል፡፡

በታሪኩ ውስጥ በምናገኘው በዚህ ሁነት ውስጥ የተጠቀሱት ሚታዊ ነገሮች ሁሉ በተመረጠ ንጉሥ ተጋዳሊ የተሠራው መቅደስ ከመቅደሶች ሁሉ የላቀ መቅደስ መሆኑን ማስረገጫ አድርጐ ጸሐፊ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ የሚነግርበት ነው፡፡ እግረ መንገዱንም ማኅበረሰቡ ራሱን የተመረጠ አዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብ አድርጐ የሚያቀርብበት ነው፡፡ ስለዚህ ንጉሡ ሰሎሞናዊ ሕዝቡ እስራኤላዊ ሆኖ ለመቅረብ የሚያበቁ ሚቶች ናቸው፡፡

ሚታዊው ሳይሆን ታሪካዊው ላሊበላ ግን ሰሎሞናዊ ንጉሥ ለመሆን ይሁዳን፣ ዳዊትን፣ ሰሎሞንን፣ ቀዳማዊ ምኒልክን... ቆጥሮ የሚያመጣው የዘር ሐረግ[50] የለምና፡፡ መቅደሱን ለመሥራት የተመረጠ ንጉሥ ሆኖ የሚታይበት ሁኔት በሚታዊው ላሊበላ ውስጥ መታየት ይኖርበታል፡፡ ከእነዚህ ሚቶች አንዱ በሰማይ የተፈጸመው ቅብዐ መንግሥት ነው፡፡ ንግሥናው የአይሁድ ንጉሥ ከሆነው ከኢየሱስ ጽንሰት ልደት፣ ሞትና ትንሣኤ ጋር በተመሳሰለበት ንግር ብቻ አይቀርም፡፡ በሰማይም ይነግሣል፡፡ "የኃያላን ጌታ ይህንን ብሎ ቅብዐ መንግሥቱን በላዩ ላይ አፈሰሰ፤ መሠዊያንና ቤተመቅደሶችን እስከምትፈጽም በሕዝቤ ላይ ትነግሥ ዘንድ እነሆ ቅብዐ መንግሥትን ቀባሁህ፡፡" /ገድለ ላሊበላ፣ገጽ 92/

የላሊበላ ንግሥና እንደዚህ የተለየ ሆኖ እንዲታይ ጸሐፊው ይተጋል፡፡[51] በዚህ ሚት ታሪካዊውን ላሊበላ ከዘር ቆጠራ የሚጠብቀው ከተቻለም ዘር ከተቆጠረላቸው ነገሥታት ሁሉ በላይ የሚያደርገው ሚት በተጋዳሊው የተጋድሎ እርምጃ ውስጥ ተካቷል፡፡ ስለዚህ የሚሠራው መቅደስ ሰሎሞናዊና ከማንም በላይ የላቀ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ በኋላ ላሊበላ የማይከሰስ የማይወቀስ ሆኖ መሣል ይጀምራል፡፡ ከሳሽ ድፍረት ያጣል፡፡ የሰሎሞን አምላክ ሾመው "በሚወነጅሉህ ሰዎች ሁሉ ልብ ፍርሃትን አሳድራለሁ፡፡" /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 92/ ብሎታል፡፡ በሕዝቤ ላይ ትነግሣለህ ብሎ ሕዝቡን አዲሱ እስራኤል ያደረገው እግዚአብሔር ሰሎሞናዊ መሆንን በመፈለግ የሚደረገውን የዘር ቆጠራ አይቃወምምና የላሊበላን ሥልጣን "ቤተመቅደሱን እስከምትፈጽም" ብሎ ንግሥናውን የገደበው ይመስላል፡፡

በዚህ ሁኔት ውስጥ የሚታየው አይ አዎ /paradox/ ጸሐፌ ገድሉን /ታሪኩን/ ባበቀለው ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ሥነ ልቦናዊ ግጭት ጠቋሚ ነው፡፡ ታላቁን የላሊበላን መቅደስ የክብሩ መገለጫ የሚያደርገው ማኅበረሰብ ሠሪውን ያልተመረጠ የሚያደርግበት አንጀት የለውም፡፡ አርቆ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አድርጐ ያነግሠዋል፡፡ የኢየሩሳሌም ሰማያዊቱ ጉዞ አንዱ ፋይዳ

---

[50] የዘአማዌ ሥርወ መንግሥት ተቀባይነት እንዳይኖረው ሴማዊ የሚባሉት የትግሬና የአምሃራ ወገኖች ክብረ ነገሥትን እየጠቀሱ ለንግሥና ከሚገባው የእስራኤላዊ የዘር ሐረግ ውጪ የነገሡ በመሆናቸው ለንግሥናው ያልተመረጡ የሥልጣን ነጣቂዎች /usurpers/ ናቸው የሚል የተቃውሞ ዘመቻ ያደርጉ ነበር፡፡ በኋላም የሰሎሞናዊው መንግሥት የመመሥረቱ መሠረት ይኸው ሆኗል፡፡ ታደሰ ታምራት ስለዚህ ሲያበራሩ እንዲህ ብለዋል"...Nevertheless, an Ethiopic version could not be made right away because as the scribe has it. It went out the days of Zagua and they did not translate it because this book says "those who reign not being Israelites are transgressors of the Law" Anti Zagwe feelings were probably widespread in Tigre Where last power was firmly established."/Taddesse,1972, 64/

[51] እንደዚህ ዓይነት ንግሥና በዘአማዌ ሥርወ መንግሥት ውስጥ ለነበሩ ለሌሎችም ገድል በስማቸው በተጻፈላቸው ነገሥታት ገድል ውስጥ ተመሳሳይ ነገር መኖሩ ያልኩትን ነገር የሚያጠናክርልኝ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ በገድለ ይምርሃነ ክርስቶስ ገድል ውስጥም ‹‹መድኃኒታችን በተቀደሱ እጆቹ የንግሥና ቅብዓትን ቀባው›› የሚል ተጽፏል፡፡ /ተስፋሚካኤል፤ 2005፣ ገጽ 24/

ይሔ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ለላሊበላ ሰሎሞናዊነትን የሚያስጨብጥበት ሌላም ሁነት በታሪኩ ውስጥ አያጣም፡፡

ላሊበላ በመልአኩ በገብርኤል ታዝሎ ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም እንደተጓዘ ሁሉ በዚሁ መልአክ ታዝሎ ወደ ምድራዊት ኢየሩሳሌምም እንዲጓዝ ይደረጋል፡፡ ኢየሩሳሌም ሰሎሞን ታላቁን የእስራኤል ቤተመቅደስ የሠራበት ከተማ በመሆኑ ኢየሩሳሌምን መርገጥ ከዚያ ቡራኬ መውሰድ መቅደሱን ለመሥራት የተገባ ንጉሥ የመሆን ማሳያ ይሆናል፡፡ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም አምሳያ ቤተመቅደሶቹን እንደሚሠራ ሁሉ ምድራዊቱም ኢየሩሳሌም አምሳያ ትሆናለች፡፡ ይህ በሚታዊ ላሊበላ ያለ ሁነት ብቻ ሳይሆን በታሪካዊው ላሊበላም የታሪክ ሁነት ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡[52]

3.3.3. የጽድቅ ትሩፋት

ከመሬታውያን ሁሉ የከበረ የዚህን የከበረ ሰው ትሩፋቱን እጽፍላችሁ ዘንድ ተሳነኝ /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 157/

የጽድቅ ትሩፋት በገድለ ላሊበላ አንዱ የመባያ ጉዳይ ነው፡፡ ለተጋዳሊው ላሊበላ የጽድቅ ትሩፋት አላብሶ መሣል ያስፈለገበት ምክንያት ይኖራል፡፡ ላሊበላ ከጅምር እስከ ፍጻሜ መልካም ጸድቅ የሚያስብሉት በርካታ መገለጫዎች ተሰጥተውታል፡፡ ኃጢአትን የሠራ መቅደሱን ለመሥራት የተገባ አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤ የእስራኤሉን የኢየሩሳሌም መቅደስ እንዳይሠራ ዳዊት የተከለከለው ኃጢአትን በመሥራቱ ነው፡፡ በእጁ የሰው ደም ስለፈሰሰና ሌሎችም የጽድቅ ሥራውን የጐዱ ተግባራትን ፈጽሟል፡፡ ስለዚህ "አንተ አትሠራም ልጅህ ግን ይሠራልኛል" የተባለው ለዚህ ነው፡፡ በገድለ ላሊበላም ተጋዳሊው መቅደስን ለመሥራት የተገባ ይሆን ዘንድ የጽድቅ ትሩፋት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

የገድሉ የመጀመሪያ ምዕራፎች ይህንን የጽድቅ ትሩፋት ደጋግመው ሊነግሩን የተጻፉ ናቸው፡፡ ላሊበላ ገዢ ሲሆን ተገዢ መስሎ መኖሩ፣ ትሕትናው፣ ጾም ጸሎቱ፣ ቅንነቱ፣ ደሀ አደጎችና ባልቴቶችን መደገፉ፣ ትዕግስቱ፣ ፍቅሩ ሁሉ ተደጋግሞ ተገልጿል፡፡ ጽድቁም የላቀ መሆኑ

---

[52] ሥርገው ሐብለሥላሴ ይህ በሮሃ የተሠራው የላሊበላ ቤተመቅደስ የኢየሩሳሌም አምሳያና ምትክ መሆኑን በተመለከተ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል ‹‹Many Christians left Ethiopia but few reached there objective. The dangers they encountered in the desert of the sudan and Egypt or in passing through muslim countries on their way to the holy land were not unknow to Lalibela. Roha then was to be a substitute for Jerusalem, a place of safety for pilgrims. It would appear that his plan met with some succes. Alvares a sixteeenth century visitor to Roha observed that there was much pilgrimage and even today it is important place for Ethiopian christians.... ›› / Sergew. 1972. /

ተጠቁሟል፡፡ "የፀሐይ ብርሃን ከጨረቃና ከዋክብት ብርሃን እንዲበልጥ እንዲሁም ስሙ ቅዱስ ላሊበላ የተባለ ሰው ክብር ከሌሎቹ ጻድቃን ክብር ይበልጣል፡፡" /ገድለ ላሊበላ ገጽ 41/

ከጻድቃንም በላይ በሥራው መላእክትን እንደመሰለ ይነገረናል፡፡ ይህንን አግዝፎ የሚያሳየው ላሊበላ እንደ ንጉሥ በንግሥና ክብሩ የዚህን ዓለም ደስታ አለማጣጣሙን የሚገልጸው የገድሉ ክፍል ሲነበብ ነው፡፡ ላሊበላ የሚበላውን ክርስቶስ ጎረዮ የተባለው ረድኡ እያዘጋጀ እንደሚሰጠው ይተረክልናል፤ የሚበላው ደረቅ እንጀራ በጮመን ወጥ ነው፡፡ በነገሥታት ቤት ካለ ፍሪዳ ተለይቶ የጮመን ወጥ በደረቅ እንጀራ መብላቱ በጽድቅ ትሩፋት የበለጸገ መሆኑን ለመግለጽ የገባ ነው፡፡ የሚበላውም ከሦስት ጉርሻ በላይ አልነበረም፡፡ በዓይነቱ ብቻ ሳይሆን በመጠኑም ማነሱ የዚሁ ማሳያ ነው፡፡ የሚጠጣውም ወይን አይደለም ውሃ ብቻ ነበር፤ የውሃውም መጠን አንድ ጽዋ ብቻ በመሆኑ በመጠኑ ያነሰ ነው፡፡ በሚበላው ምግብና መጠጥ ዓይነት መጠን ብቻ ሳይሆን ይህንን ለማግኘት የሚጠቀምበትም የገቢ ምንጭ የጽድቅ ትሩፋቱ ማሳያ ነው፡፡ ላሊበላ ጥበበ ዕድ የሚሠራና የሥራውን ውጤት በረድኡ በኩል ሸጦ በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሆኖ ተሥሏል፡፡

ላሊበላ እንደ ነገሥታት ከሰበሰበው ግብር የሚጠቀም ወይም በግፍ ጨብጦ ረግጦ በመግዛት በንጥቂያ እና በቅሚያ የሚተዳደር አለመሆኑ እንደ ጽድቅ ሥራ ጐልቶ ታይቷል፡፡ የመቅደሱንም ሥራ ሲያከናውን በሥራው ለተሳተፉ ሠራተኞች ሁሉ በደሞዝ ተዋውሎ ማሠራቱን እንጂ በግዳጅ የምስኪኖችን ጉልበት አለመበዝበዙ የዚሁ አካል ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ የጽድቅ ትሩፋት ከነገሥታት ሁሉ የሚበልጥ ንጉሥ በመሆኑ ለተጋዳሊው መቅደሱን ለመሥራት የተገባ ሆኖ ተደራሲው እንዲቀበለው የሚያነሣሣ ነው፡፡ ስለዚህ ለሰሎሞናዊው ሥራና ሓላፊነት የተመረጠ እንደሆነ አድርጐ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ ማመንና ማሳመን ይፈልጋል፡፡

3.3.4 ቤተ መቅደሱ

በሚታዊውም ይሁን በታሪካዊው ላሊበላ ጐልቶ የሚታየውና የሚነገረው ታላቅ በረከት የቤተ መቅደሱ ሥራ ነው፡፡ ሚታዊው ላሊበላ የሚያጋጥሙትን ቅጽሮች ሁሉ እያለፈ የሚያገኛቸው ድሎች ወደዚህ በረከት የሚያደርሱት መወጣጫዎች ይሆናሉ፡፡ ተከታዮቹም የሚናፍቁት ከተጋዳሊው እጆች ሊያገኙት የሚሹት ተፈላጊው በረከት መቅደሱ ነው፡፡ ኢየሱስን የመምሰሉ፤ ወደ ሰማያዊትና ምድራዊት ኢየሩሳሌም የመሔዱ፤ በጽድቅ ትሩፋት የመበልጸገ መደምደሚያ መቅደሱ ነው፡፡ መቅደሱ ደግሞ ከመቅደሶች ሁሉ የላቀ ነው፡፡ በተለይም እስራኤላውያን

ከበቀሏቸው መቅደሶች ሁሉ የላቀ መሆኑን ማሳየት በገድሉ ተዘውትሮ የሚገለጽ ይሆናል። ይህም በሠሪው፣ በአሠራሩ፣ በሚሠራበት ቁስ፣ በሚሠራለት ሕዝብ ልዕልና ይገለፃል።

ላሊበላ ከሌሎች መቅደስ ከሠሩ የእስራኤል መሳፍንት፣ ነገሥታትና ቅዱሳን ሁሉ የበለጠ ክብር ያለው ሆኖ ተገልጿል። ለሌሎች ያልሆኑ ለእርሱ ብቻ የታደሉ ጸጋዎች ለተጋዳሊው ንጉሥ ላሊበላ ተሰጥተዋል። አስቀድመን እንዳየናቸው በልደት በሞትና በትንሣኤ ኢየሱስን የመሰሉ ወይም መስለው የኖሩ የእስራኤል ምርጦች አልነበሩም። ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን የተሳለሙ፣ በዚያም ሰማያዊ መካነ ሲመት ተገኝተው ቅብዐ መንግሥት ያገኙ የእስራኤል ምርጦች አልነበሩም። እንደ ላሊበላም በጽድቅ ትሩፋት ዕድሜያቸውን ሙሉ ያሳለፉ የእስራኤል ምርጦች አልነበሩም፤ ሙሴ እግዚአብሔርን ደስ ባለማሰኘቱ ወደ ምድረ ርስት ሳይገባ ቀርቷል፣ ሰሎሞንም በሠራው ኃጢአት የእስራኤል መንግሥት ተበትኗል። ፍጻሜያቸው እንደ ጅምራቸው አልሆነምና። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተረኮች የገድለ ላሊበላ ጸሐፊ አያውቃቸውም ብሎ መናገር አይቻልም። አምላኩ ገብረመስቀል ብሎ እንዲጠራው የሚደረገው ላሊበላ ግን ሁልጊዜ ሐሳቡና ሥራው ለነፍሱ የሚገባውን የጽድቅ ሥራ መሥራት ነውና ከፍ ያለ ክብር ያለው ሆኖ ተሥሏል። "ምድራዊ ሐሳብን፣ ለሥጋውም ፈቃድ ቢሆን ሚስቱንም ደስ ለማሰኘት ቢሆን አላሰበም። .... ስለ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አሰበ እንጂ።" /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 153/

ስለዚህ ከእነዚያ ከእስራኤሉ መስፍንና ንጉሥ የተለየ መቅደስ ሠራ ብሎ ለማቅረብ ለጸሐፊው ተችሎታል። ሙሴ ከተፈተለ ልብስና ከዕንጨት ድንኳንን ሠራ፣ ሰሎሞንም እርዝመታቸው ስምንትና ሰባት ክንድ በሚሆኑ በታላላቅ ድንጋዮችና የጢሮስ ንጉሥ ኪራም በረዳው የዝግባና የጽድ፣ የዋንዛ ዕንጨት ቤተመቅደሱን ሠራ። ስለዚህ ጸሐፊው ላሊበላ ከአንድ ቋጥኝ በመሥራቱ የላቀ ምርጥና ጥበበኛ ነው ብሎ ሲያቀርብልን ለማሳመኑ እርግጠኛ ሆኖ ነው። "የአንደኛው ጥበበኛ ቤት ግን በድንጋይ በእንጨት በገመድ በጭቃ ሠራ፤ ሁለተኛው ጥበበኛ ግን ቤተመቅደሱን ከአንድ ቋጥኝ ድንጋይ ሠራ" /ገድለ ላሊበላ፣ ገጽ 157/

ስለዚህ በእርጅና እንደሚጠፋው እንደ ሙሴ ድንኳን፣ ዐረ እስራኤል ነገሥታት በቀላሉ እንዳፈረሱት እንደ ሰሎሞን ቤተመቅደስ ሳይሆን የመቅደሱን ክብር ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም እስክትተካው ድረስ ለዘለዓለም እንደሚኖር ይነግረናል።

በተሠራበት ቁስ ብቻ ሳይሆን በአሠራሩም ቢሆን የላሊበላ መቅደስ የላቀ እንደሆነ ማመልከት ሌላው የገድሉ ሐሳብ ነው፡፡ ሙሴ ባስልኤልን[53] የመሰሉ ጠቢባንን፣ ሰሎሞን የጢሮስን ጠቢባን ሰብስቦ አሠራ፡፡ ላሊበላ ግን ባስልኤልን፣ ኢልያብን፣ የጢሮስን ጠቢባን የመሰሉ ጠቢባን ሳይጐድሉበት የመላእክትም ረድኤት ተጨምሮ እንደሠራው ይነገረናል፡፡ የመቅደሱን ልክ /መጠን/ ሰፋሪዎች ንድፍ አውጪዎች ሁሉ መላእክት ነበሩ፤ ቀን ሰዎች ቢሠሩ በመላእክት ረድኤት ሌሊትም ይሠራልና በነጋ ቁጥር የሥራው መጠንም ጥራት ይጨምር ነበር፡፡

በአሠራሩም ብቻ ሳይሆን የላሊበላ ቤተመቅደስ ለተመረጠ ሕዝብ የተሠራ በመሆኑ የላቀ ይሆናል፡፡ የሰሎሞንና የሙሴ ቤተመቅደስ የተሠራው እንዲሠሩ ያዘዛቸው አምላክ ከመረጠው ሕዝብ ጋር የሚገናኝበት ነው፡፡ ላሊበላም የተመረጠ መቅደስ ሲሠራ ያዘዘው ልዕለ ተፈጥሮ ለመረጠው ያንን በረከት በተጋዳሊው በኩል ሊያመጣለት ላዘጋጃቸው ምርጥ ሕዝብ ነው፡፡ "እኒህን አብያተ ክርስቲያናት ትሠራልኝ ዘንድ አስተውል፤ በጐ መዓዛ ያለው እጣን መስዋዕትና ቁርባንን በውስጣቸው የሚያሳርጉ የመረጥኳቸው ሕዝቦች አሉና፡፡›› /ገድለ ላሊበላ ገጽ 85/

ይህ ምርጥ ማኅበረሰብ ተጋዳሊውን ያበቀለው፤ በገድሉም ውስጥ ክብሩን እየገለጠ ያለው ማኅበረሰብ ነው፡፡ እርሱም አዲሱ እስራኤል ነው፡፡ ተጋዳሊውም አዲሱ ምርጥ ንጉሥ ሰሎሞን አዲሱ ምርጥ መስፍን ሙሴ ነው፡፡ ከሙሴና ከሰሎሞንም የላቀ ነውና፤ ሕዝቡም ከእስራኤል የላቀ ክብር ያለው ይሆናል፡፡ ሀገሩም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቅድስቲቱ ከተማ ትሆናለች፡፡ በዚያ መቅደስ አለ፤ ተጋዳሊውን ለገድል ያበቃው ተፈላጊውን በረከት ያስገኘው ልዕለ ተፈጥሮ ይከብርበታል፡፡

[53] ባስልኤል በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መሠረት በሙሴ ዘመን የነበረ የጥበብ ጸጋ የተሰጠውና የሙሴን ድንኳን በመሥራት ስሙ የተጠራ ነበር /ዘጸ 36÷1/፡፡

3.4 ንጽጽራዊ ዕይታ

በጥናቱ ያካተትኳቸው ገድሎች ሁለቱ የነገሥታት እና አንዱ የጳጳስ በመሆኑ በተወሰነ መልኩ በንጽጽር ለማየት ያስችላል። በተለይ የአብርሃ አጽብሐ ገድል ከሰላማ ከሳቱ ብርሃን ገድል ጋር ለማስተያየት በገድሉ እንደተጋዳሊ የተወሰዱት ታሪካዊዎቹ አብርሃ አጽብሐና ሰላማ ከሳቱ ብርሃን ዘመንኛ በመሆናቸው አመቺ ነው። ታሪካዊው ላሊበላ በነበረበት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጳጳስ ቢኖራትም ገድል የተጻፈለት ጳጳስ ባለመሆኑ ለላሊበላ ዘመንኛ ሆኖ የሚታይ የጳጳስ ገድል አይገኝም። ይሁን እንጂ ገድላቱ የተጻፉት በኋለኛው ዘመን በመሆኑ በአክሱምም ይሁን በዛግዌ ዘመን ለነበሩት ለነገሥታቱና ለጳጳሳቱ ያለውን ዕይታ የሚቃኘው ሥነልቡና ልዩነት ስለማይኖረው የላሊበላም ገድል እንደ አብርሃ አጽብሐ ከሰላማ ከሳቱ ብርሃን ገድል ጋር ቢነጻጸር የማያራምድ አይሆንም።

በሁለቱ የነገሥታት ተጋዳልያን ገደል የሚዘወተሩት የመባያ ጉዳዮች ተመሳሳይ መሆን የተጋዳልያኑ መነሻና መድረሻ ዕጣ ፈንታዎች መመሳሰላቸውን ለማመልከት ያስችላል። ነገሥታቱ በሁለቱም ገድሎች ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው እንዲጠሩ እንዲለዩ የሚደረጉ ናቸው። ማኅበረሰቡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተጸነሰና እንደተወለደ በሚያስብበት የቀን ቀመር ጠብቀው በጽንሰትና በውልደት ቀን መምሰላቸው፣ በጽንሰትና በውልደት ሂደትና ሁኔታዎች ያንኑ መልክ ይዞ ለመገኘት መጣራቸው የላሊበላንና የአብርሃ አጽብሐን ገድል ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል።

አብርሃ አጽብሐ ዘር ተቋጥረው ራሳቸውን ከይሁዳ ነገድ ከሰሎሞን ትውልድ አንድ አድርገው እንዲገኙ ብመደረጉ፣ ዳግም ልደት ለማግኘት በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ መጠመቃቸው ይሁን ተብሎ ኢየሱስን እንዲመስሉ የተደረገበትን ሁኔታን ሲያጎላው፤ ላሊበላ ደግሞ የዳግም ሕይወት ብሥራቱን የምናየው በዘመዶቹ ተነኮል መርዝ ጠጥቶ ከሞተ በኋላ እንደ ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን እንደተነሣ ሆኖ መገለጹ ነው። ሁለቱም የአዲስ ሕይወት ብስራት ሆነው የተቀመጡ ዘይቤዎች /ሜታፎሮች/ ሲሆኑ አስቀድመን በትንታኔው ባነሳናቸው ፋይዳዎች በሁለቱ ገድላት ውስጥ ያሉ ተጋዳሊዎችን አነሣሥ ተመሳሳይ ያደርገዋል።

አብርሃ አጽብሐ ከዳግም ልደት በኋላ የኃይልና የሥልጣን በትር የሆነውን በትረ ሙሴ ይዘው የኢየሱስ ጠላት የነበረውን የጌርጌሴኖኑን ሰይጣን በማሸነፍ ያጠረውን ቅጽር በመዝለት የሚፈለገውን በረከት ለማምጣት ተጋድሎን ይፈጽማሉ። የሚያልፉት ቅጽር ላይ የቆሙት ተከላካይ ቃፊሮች የኢየሱስንም የተጋድሎ ቅጽር ዘግተው የነበሩት የጌርጌሴኖን መናፍስት

በመሆናቸው በሚያልፉት ቅጽርም ከኢየሱስ ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ላሊበላም ኢየሱስ ላመነት ያመጣውን የሚፈለገውን በረከት ለመስጠት የተሻገራትን የመጨረሻ ቅጽር የሆነችውን የሞት ጽዋ በመጎንጨትና እንደ እርሱ በሦስተኛው ቀን በመነሣት በዘለቃት ቅጽር ኢየሱስን እንዲመስል ተደርጓል፡፡ ሁለቱም ነገሥታት ተጋዳሊያን በሚዘልቁት ቅጽር ዓይነት ከኢየሱስ ጋር ሲመሳሰሉ እናገኛለን ማለት ነው፡፡

በሁለቱም የነገሥታት ገድላት ቅጽርን ታልፎ ተፈላጊውን በተጋዳሊው የሚመጣ በረከት ለማግኘት ነገሥታቱ በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ወደሚመረጡበት ወደሚሾሙበት ሰማያዊ ከተማ ይዘልቃሉ፤ እርሷም ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ናት፡፡ በዚያ አሸናፊዎች ከሚገኙበት፤ እነርሱ ይመስሉት ዘንድ የወደዱት አሸናፊው አንበሳ ኢየሱስ የነገሠበት ከተማ በመሆኑ ያንን መሳለም የዚያችን ከተማ ቡራኬ የማግኘት፣ ሊያገኙትም የሚሹትን በረከት ለማግኘት ያላቸው ኃይልና ተስፋ አስተማማኝ የመሆኑ ማሳያ ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐ የሚሹት ለተከታዮቻቸው ያተርፉት ዘንድ የሚመኙት በረከት ቤተመቅደስ ነው፡፡ ያንን እንዲሠሩ መታዘዛቸውን እንረዳለን፡፡ የሚሠሩበት አቅምና ጥበብ መሥሪያ ቁስም ሁሉ የሚያገኙት ከዚሁ ሰማያዊ ዓለም እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ላሊበላም ለተከታዮቹ ያመጣው ዘንድ የተፈለገው በረከት ቤተመቅደስ በመሆኑ በዚህ በሚፈልገው በረከት ከነገሥታቱ ከአብርሃ አጽብሐ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እርሱንም እውን ለማድረግ በዚያችው ሰማያዊ ከተማ መሾሙ ይነገረናል፡፡ ኃይልና ዕውቀት ይላበሳል፡፡ የሚሠራውን መቅደስ አርአያ ወይም ምሳሌ ያገኛል፡፡ ስለዚህም በሁለቱም ነገሥታት ተጋዳልያን ተፈላጊው የሚታሰሰው በረከት ቤተመቅደስ በመሆኑ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ያንንም ለማግኘት የሚሾሙበት፣ የሚመረጡበት፣ የሚሠሩትን መቅደስ አርአያ የሚያዩበት በምን እንደሚሰሩ ዕውቀትን ገንዘብ የሚያደርጉበት ከተማም ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም በመሆኗ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

ነገሥታት ተጋዳልያኑ የሰማያዊቷን ብቻ ሳይሆን የምድራዊቷን ኢየሩሳሌም በረከት እንዳላጡ ሆኖ ተገልጿል፡፡ አብርሃ አጽብሐ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመጓዛቸው ገድላቸው ባይነግረንም ኢየሩሳሌም ግን ወደ እነርሱ ትመጣለች፡፡ ሲጠመቁ ዮርዳኖስ ወደ እነርሱ መምጣቱ ይነገረናል፡፡ ውሃው ብቻ ሳይሆን አፈሩም በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ታፍሶ የአክሱምን ባህር ማድረቂያ፣ የመቅደሱምን መሠረት ማጽኛ ሆኖ ይመጣል፡፡ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የኢየሩሳሌም በረከት አይለያቸውም፡፡

በገድሉ ላሊበላ ግን ከአብርሃ አጽብሐ በተለየ ተጋዳሊው በረከቱን የሚያገኘው በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት በመልአኩ ገብርኤል ታዝሎ ኢየሩሳሌምን የሚሳለም ሆኖ ነው፡፡ ቡራኬውን ያገኙበት መንገድ ቢለያይም በሁለቱም ገድል ያሉ ተጋዳሊያን ግን ኢየሩሳሌም ምድራዊትንም ተመኝቶ በማግኘት ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሁለቱም ገድሎች ያሉ ተጋዳልያን የሚጓዙበት ፈለግ ሙሴና ሰሎሞን የተጓዙበትን መቅደስ የመሥራት ፈለግ ተከትለው ይሁን እንጂ ከእነርሱ በክብር ብልጫ ያላቸው መሆኑን ማመላከት የገድሉ ሌላው ገጽታ ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐ በጽድቅ ትሩፋታቸው ለበቀል ተነሥተዋል፣ የሰው ደም አፍሰዋል ከተባሉት ሰሎሞንና ዳዊት እየተነጻጸሩ በቅድስና ብልጫ ያላቸው ሆነው ቀርበዋል፡፡ እንደ ሰሎሞን፣ እንደ ዳዊት፣ እንደ ሙሴ ለማግባት ሳይመኙ በድንግልና ለመወሰን ያላቸውን ፍላጎት አጉልቶ ያሳየናል፡፡ የሚበሉትም ምድራዊ ምግብና መጠጥ አይደለም፡፡ ልዕለ ተፈጥሮ የሚያቀርብላቸውን ሰማያዊ መጠጥ ይጠጣሉ፣ ሰማያዊ ምግብ ይበላሉ እንጂ፡፡ እነርሱ ሌላውን በማብላት በማጠጣት ቸርነታቸውን ደጋግመው ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ የጽድቅ ትሩፋት ሰብእናቸው ከሙሴ፣ ከዳዊት፣ ከሰሎሞን ይበልጣል፡፡ የዚህ ሰብእና ብልጫም የመቅደሱ ልዕልና ቀድሞ የሚታይበት አመላካች ሁነት ነው፡፡

ላሊበላም እንዲሁ በድንግልና ለመኖር ይመኝ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በልዕለ ተፈጥሮ ምክርና ምርጫ ግፊት ያገባ ሆኖ ይገለጻል፡፡ አለማግባት ወይም በአንድ መወሰን የመንፈስ ልዕልናን የማግኘት ማሳያ አድርጎ ጸሐፊው የተገኘበት ክርስቲያን ማኅበረሰብ ያየዋልና አንዱን ከአንዱ የሚያስበልጥበት ነገር ነው፡፡ ስለዚህ በመቶ የሚቆጠሩ ዕቁባትና ሚስቶች ካሉት ከሰሎሞን በልጦ መታየቱ አይቀርም፡፡[54] የሚበላውም በቀን አንዴ ሆኖ አገልጋዩ መጥኖ የሚያዘጋጅለትን እጅግ ያነሰ መዓድ ይሆናል፡፡ ለሌሎች ግን የሚመጸውትና የቸርነት ሥራ የሚሠራ ሆኖ ይሣላል፡፡ ይህ ሁሉ የጽድቅ ትሩፋቱ የከበረ የሰብእና ልዕልና ሰጥቶት መቅደሱ ከሰሎሞንና ከሙሴ እንዲበልጥ ይደረጋል፡፡ በእነዚህ በሁለቱም ገድላት የሚታየው ነገሥታት ተጋዳሊያኑን ከሙሴና ከሰሎሞን ጋር እያነጻጸሩ የማየት ዝንባሌ መቅደሱን ከመቅደሳቸው ለማላቅ በመሆኑ የነገሥታት ተጋዳልያኑን ገድል ተመሳሳይነት የጎላ ያደርገዋል፡፡

ነገሥታት ተጋዳልያኑ ተፈላጊውን በረከት የመቅደሱን ነገር እውን የሚያደርጉበት ሥልጣንና ኃይል የታጠቁበት በትረ ሙሴ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ አብርሃ አጽብሐ ገና በሕፃንነት

[54] በክርስትና አመለካከት የብሉይ ኪዳን ክብር ከሐዲስ ኪዳን ክብር የላቀ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳኑ ምሳሌ ሐዲስ ኪዳኑ አማናዊ፣ ብሉይ ኪዳኑ ጥላ ሐዲስ ኪዳኑ አካል እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ላሊበላ የተገኘበት ማኅበረሰብ ክርስቲያንና ‹‹ራስን መግዛት››፣ ‹‹ምናኔ›› ከፍተኛው የጽድቅ ትሩፋት ማሳያ በሆነበት ማኅበረሰብ በመሆኑ በዚህም መሥፈርት አንዱን ከአንዱ ያበላልጣል፡፡

ወራታቸው ልዕለ ተፈጥሮ ይህንን በትረ ሙሴ ሲያስታጥቃቸው እናያለን፡፡ ለላሊበላ ደግሞ ገብረ መስቀል የሚለው ስሙ ከዚሁ ከሙሴ በትር ጋር ተነጻጽሮ ሲሰጠው እናገኛለን፡፡ ይህ የኃይል የሥልጣን ማሳያ ምንጭ ነው፡፡

ሌላው በነገሥታቱ ገድል የሚታየው ዋነኛው ነጥብ የመቅደሱ ነገር ነው አብርሃ አጽብሐ መቅደሱን በአክሱም ሲያቆሙ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት አይለያቸውም፡፡ መቅደሱም በመላእክት ተራዳኢነት ይሠራል፡፡ መሥሪያውም ቁስ ሰማያዊ ነው፡፡ የሚሠሩትም ጠቢባን የሰሎሞንን መቅደስ የሠሩ የጢሮስ ጠቢባን ውሉደ ኪራም ናቸው፡፡ እነዚህ የሙሴን የመገናኛ ድንኳን የሠሩ የባስልኤል ጥበብ የማይለያቸው መሆኑን ተራኪው ደጋግሞ ይገልጻል፡፡ በተመሳሳይ በገድለ ላሊበላም ተጋዳሊው የመላእክት ተራዳኢነት ሳይለየው ከሰውም ወገን በባስልኤልና በጤሮሳውያን ጥበብ የተላበሱ ሙያተኞች እንደሠሩት ይነገራል፡፡ በዚህ ሁለቱም ገድል ተዘውትረው የሚነገሩ በመሆኑ ተማሳሳይነት አላቸው፡፡

የአብርሃ አጽብሐ ቤተመቅደስ የሚሠራው ከሰማይ በወረደ ቁስ ነው፡፡ መልአኩ መሥሪያውን ድንጋይ ያቀብላል፡፡ ኢየሱስ የሚሠራበትን ማዕድን ያዘንባል፡፡ በዚህ ከሙሴና ከሰሎሞን መቅደስ እንዲልቅ ይደረጋል፡፡ በላሊበላ ደግሞ የሚሠራው ከአንድ ቋጥኝ ድንጋይ ብቻ በመሆኑ መቅደሱን ከእስራኤል መሳፍንትና ነገሥታት መቅደስ ማስበለጫ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በአብርሃ አጽብሃ የተሠራበት ቁስ ከሰማይ በመምጣቱ በላሊበላ ደግሞ ከአንድ ቋጥኝ በመሆኑ የተለያየ ይምሰል እንጂ ያንን በገድሉ ደጋግሞ በሚነገርበት ዓላማ ግን ተመሳሳይነት አለ፡፡ እርሱም ከእስራኤላውያኑ ቤተመቅደስ አልቆ ማሳየት ነው፡፡

የአብርሃ አጽብሐ ቤተመቅደስ የሚሠራው በአክሱም ነው፡፡ የላሊበላ ደግሞ በሮሃ ነው፡፡ እነዚህ ቦታዎች ይለያዩ እንጂ በመንፈስ ያላቸውን አንድነት ለማንጸባረቅ በገድለ ላሊበላ ያለው ተጋዳሊ የአብርሃ አጽብሐ መቅደስ ባለበት በአክሱም በመልአኩ ገብርኤል ተጭኖ ሲሳለም እንደሐሊ ይነግረናል፡፡ ይህ ያለምክንያት አይደለም፡፡ መቅደሱን እንደ በረከት ከተጋዳልያኑ የሚሻው ማኅበረሰብ ያው አንዱ አዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብ ኢትዮጵያውያን ይሆናሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በሁለቱን የነገሥታት ገድላት የሚታዩ ዝምድናዎችና የነገሥታት ገድላት ሲታሰቡ ትኩረት የማይነፈጋቸው ነጥቦች ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የተንጸባረቁ የነገሥታቱን ገድላት አንድ የሚያደርጉ የመባያ ጉዳዮችን ይዘን ከጻጻሱ ገድል ጋር ማሰተያየትም አግባብ ይሆናል፡፡

ጳጳሱ ተጋዳሊ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በምድረ እስራኤል በኢየሱስ የመቃብርና የትንሣኤ ሥፍራ በኢየሩሳሌም በመወለድና እርሱ በተጠመቀበት ወንዝ በዮርዳኖስ በመጠመቅ ኢየሱስን መስሎ እንዲጠራ ወይም እንዲለይ፤ በጽንሰትና በውልደት ሂደትና ሁኔታዎችም እርሱን መስሎ ለመመረጥ መቻሉን እንድናይ መደረጉ ከነገሥታቱ ገድል ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ ንጉሡ ተጋዳሊ የኢየሱስን ሥር መሠረት እንደሚፈልገው ሁሉ ጳጳሱም ተጋዳሊ ያንኑ መሻት ተሥሎበት ይገኛል፡፡ ይህ ተመሳሳይነት ኢየሱስን መስለው ተጋዳልያኑ እንዲለዩ አንዲጠሩ በሆነበትም ፋይዳ አንድ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

ንጉሡ ተጋዳሊ በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ተፈላጊው በረከት የሚገኝበትን ቅጽር ለማለፍ የበቃ ሆኖ እንደሚተረክለት ሁሉ ለጳጳሱ ተጋዳሊም በዚሁ መንገድ ይዘልቃል፡፡ ለጳጳሱ የሚያጋጥሙት ፈተናዎች ከሽፍቶችና ጥላቻ ካላቸው ሰዎች ነው፡፡ ንጉሥ ባለመሆኑ እንደ ላሊበላ ንግሥናን ሹመት ሽልማትን ከሚሹ ዘመዶቹ አይደለም ወይም እንደ አብርሃ አጽብሐ ከመናፍስቱ አይደለም ወይም የሞት ጽዋን ሲጠጣ አናይም፡፡ ስለዚህ ለካህን እንደሚገባው በጉዞውና በአገልግሎቱ የሚያጋጥሙት ተቀዋሚ የየአካባቢው ሰዎች የሚያልፈው ፈተና ወይም የሚዘለቀው ቅጽር ማሳያ ሆነዋል፡፡

ንጉሡ ተጋዳሊ የኢየሱስ ክርስቶስን የይሁዳ የንግሥና የዘር ወርስ በሥጋ ወይም በሰማያዊ ቅብዓት ለማግኘት ሲጥር ጳጳሱ ግን የኢየሱስን የሊቀ ካህንነት በሐዋርያዊ ውርስ መንገድ ሊቀባ ወደ እስክንድርያ ይጓዛል፡፡ ከዚያም እንደ ንጉሡ በትረ ሙሴ ሳይሆን በትረ አሮን ይይዛል፡፡ ይህም እርሱ ያመጣው ዘንድ ላለው በረከት ማምጫ ኃይልና ሥልጣን ማሳያ ነው፡፡ የአሮን በትር የክህነት በትር ሲሆን የሙሴ በትር የምስፍና በትር ነው፤ በዚህ ይለያያሉ፡፡ በትሩ ግን ሥልጣንና ኃይል በመሆኑ ይመሳሰላሉ፡፡

ሌላው መነጻጸሪያ መባያ የኢየሩሳሌም ሰማያዊት ጉዞ ነው፡፡ ነገሥታት ተጋዳልያኑ ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ጉዞ አድርገው ከአሸናፊዎች ማኅበር ጋር መደባለቃቸው እንደተነገረን፤ በዚያ ከነገሠው ከይሁዳ አንበሳ ከኢየሱስ ጋር ይገናኛሉ፡፡ በዚያ መመረጣቸውን ያጸናሉ፡፡ በዚያ ይሾማሉ፡፡ የጳጳሱም ተጋዳሊ ጸሐፌ ገድልም ተጋዳሊውን ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንዲጓዝ አደርጓል፡፡ በዚያ መመረጡን ያጸናል፡፡ ከሊቀ ካህናት ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ የክህነቱን ኃይል ያትማል፡፡ በጉዞው ተጋዳልያኑ የሚሔዱበት ሰማያዊ ከተማ አንድ ይሁን እንጂ እነዚያ ንግሥናቸውን ሲያጸኑ እርሱ ግን ክህነቱን ሲያጸና ይሔዳልና ይለያያሉ፡፡

ይህንን ቡራኬ ይዞ ወደ ምደር የሚወርደው እርሱም ለተከታዮቹ ሊያመጣ የሚመኘውን በረከት መቅደሱን ለመሥራት ነው፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው መሣሪያ ማጥመቅና መስበክ ይሆናል፡፡ ከነገሥታት ተጋዳልያኑም የሚለየው እርሱ በሚሠራው መቅደስና እነርሱ በሚሠሩት መቅደስ ዓይነት ነው፡፡ እነርሱ ከቋጥኝ ዓለት፣ ከወርቅ፣ ከብር ሕንጻ ቤተመቅደስ ይሠራሉ፡፡ እርሱ ግን በስብከትና በማጥመቅ በማቁረብም የተያያዘ የማኅበረሰብ መቅደስ ይሠራል፡፡ በሰላማ ከሳቱ ብርሃን ገድል ተራኪ መሠረትም ‹‹መቅደስ›› የተባለው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ካህኑ የተቀደሰውን ማኅበረሰብ ሲሠራ ንጉሡ የተቀደሰውን የሚቀድስ፣ የትድስናውም ምልክት የሆነውን፣ የጳጳሱም መንበር የሆነውን ሕንፃ ቤተመቅደስ ይሠራል፡፡ ልዩነቱ ይህ ነው፡፡

ለካህኑ ተጋዳሊ ይህንን መቅደስ ለመሥራት የተገባ መሆኑን ማመላከቻ የጽድቅ ትሩፋቱ ጎልቶ ይነገራል፡፡ ይህ ንጉሡም ለሚሠራው መቅደስ የተገባ መሆኑን ማመላከቻ የሚሆን ጽድቅ እንዳለው መንገር ዋነኛው መባያ ነው፡፡ ጳጳሱ በዚህ ጽድቁ ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ዕውቀት ጥበብ ባህልና ታሪክ መሠረት መሆኑን የሚያመላክት ምንጮችን የመባረክ ተምሳሌታዊ ሁነት ተደጋግመው ይተረካሉ፡፡ ይህም በንጉሡ ተጋዳሊ ፈለጎች ወስጥ የሚታይ መባያ አይደለም፡፡ ይህም ጳጳሱን ከንጉሡ በተሻለ አስፈላጊና የሥልጣኑም መሠረት እንደሆነ ለማሳየት የተመለከተ ነው፡፡ ደጋግሞ ይባርካልና ቡራኬው የንጉሡንም መቅደስ ይጨምራል፡፡ ሁሉንም ይባርካል ያለእርሱ ቡራኬ መቅደስ የለም፤ መቅደስ ከሌለ መመረጥ አይኖርም፡፡ የመመረጡ ማጽኛ በጳጳሱ እጅ ያለው በትረ አሮን ነው፡፡ እርሱም ክህነት ይሆናል፡፡ በዚህ ክህነት ንጉሡና ካህኑ ይጣመራሉ፡፡

በነገሥታት ተጋዳልያኑ አብርሃ አጽብሐ ገድል የሰላማ ከሳቱ ብርሃን የገድል ተሳትፎ ይነሣል፡፡ በጳጳሱ ተጋዳሊ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ገድል ተደጋግሞ እንደሚታየው ደግሞ ነገሥታት ተጋዳልያኑ/አብርሃ አጽብሐ/ እንደ ተጋዳሊ ሊተረክላቸው የሚሞከርበት ክፍል አለ፡፡ ነገሥታቱና ጳጳሱ አንድ ዓይነት ሕልምም ያያሉ፡፡ ይህ መባያ በነገሥታቱ ገድል ባይኖርም በካህኑ ገድል የሚታይ ነው፡፡ ይህም በቤተክህነቱ ማኅበረሰብ ያለውን የመመረጡ የመቀደሱ ምክንያት እኔ ነኝና አንድም ሁለትም ነን የሚል አንድምታ ማስያዣ ነው፡፡

ማጠቃለያ

ሃይማኖታዊ ተረኮች በሚት ጥናት ውስጥ ትኩረት ከሚሰጥባቸው ተረኮች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ተረኮች ውስጥ የማኅበረሰብ እሴትና ባህል በጉልህ ሊንጸባረቅ የሚችልባቸው መድረኮችም ናቸው፡፡ በእኔ ጥናት ትኩረት የተሰጠባቸው የነገሥታትና የጳጳስ ገድላት በዚሁ አግባብ የሚታዩ ናቸው፡፡

የጥናት ዋነኛ ዓላማ በእነዚህ ገድላት በቀረቡ ተጋዳልያን የሕይወት ገጽታዎች ውስጥ የተንጸባረቁ ገድሉን ያበቀለው ማኅበረሰብ የሚያስተጋባቸውን ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች መመርመርና፣ የተጋዳሊነት ጽንሰ ሐሳብ በእነዚህ ገድላት ውስጥ በምን ደረጃና ሁኔታ እንደተንጸባረቀ ማጥናት ነው፡፡ በተለይም ለሁሉም ገድሎች መባያ ሆነው የተለዩትን ጉዳዮች ያላቸውን ትርጉምና አንድምታ መተንተን ላይ አተኩሬያለሁ፡፡ በሁለት ወገን የሚታዩት ገድላት ማለትም የነገሥታቱና የጳጳሱ ገድላት ከተነሡት የመባያ ጉዳዮች አንጻር በንጽጽር ለማየትም ጥሬያለሁ፡፡ እነዚህን ዓላማዎች መነሻ አድርጌ የሠራሁት ትንታኔም የሚከተሉትን ዋና ዋና ድምዳሜዎች ለመስጠት አብቅተውኛል፡፡

በጥናቴ ከተካተቱት ሦስት ገድሎች ሁለቱ የነገሥታት ተጋዳልያን ሲሆኑ አንዱ የጳጳስ /ካህን/ ተጋዳሊ ተጋድሎ የሚተረክበት ገድል ነው፡፡ በነገሥታት ተጋዳልያን አብርሃ አጽብሐ ገድል መንትያ ነገሥታት ተጋዳልያን ሆነው ከጅምሩ በልዕለ ተፈጥሮ ለተጋድሎ የተለዩ ነገሥታት አንድም ሁለትም ሆነው ልዕለ ተፈጥሮ በመራቸው ጐዳና ለተከታዮቻቸው፣ ለሚገዙት ማኅበረሰብ የሚያስፈልገውን በረከት ይዞ ለመመለስ ተጋድሎ ወደ ሚፈጽሙበት ቅጽር ይዘልቃሉ፡፡

ቅጽሩን በስኬት ዘልቀው ተፈላጊውን በረከት እንዲያመጡ አስፈላጊ የሆኑ ጸጋዎችን /ኃይል/ ይሰብሳሉ፡፡ ከእነዚህም ቅድሚያ የሚነሣው ከጽንሰትና ከመወለድ አንስቶ ክርስቶስን መስሎ ለተጋዳሊነት ተለይተው እንዲወጡ ሲደረግ እናያለን፡፡ ተጋዳሊው በዋናነት የኢየሱስ ክርስቶስን ገጽታ መላበስ ከሥር ከመሠረቱ ይፈልገዋል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን እስራኤላዊ ዝርያ ወስዶ እንደ ኢየሱስ ዘር ተቋጥሮ የዳዊት የሰሎሞን ልጅ ሆኖ ለክርስቶስ ወንድም ይሆናል፡፡ ዘሩን ብቻ ሳይሆን የትውልድና የጽንሰት ቀኑንም ይጋራል፡፡ በሥጋም ብቻ ሳይሆን በመንፈስ በሚገኘው አዲስ ልደትም ኢየሱስ ከተወለደበት የዮርዳኖስ ማኅጸን ይወለዳሉ፣ ለዚያም ኢየሱስን ባጠመቀው ዮሐንስ እጅ ይጠመቃሉ፡፡ ይህ የተጋዳልያኑን አሸናፊነት ቀድሞ ማመልከቻ ሁነት ነው፡፡

እንደ ማኅበረሰቡ እምነት ኢየሱስ አሸናፊ አንበሳ ተብሎ የሚጠራ ድል ነሺና አዳኝ ንጉሥ ነው፡፡ እርሱን መስሎ መጠራትም የዚህ አሸናፊነት ዕጣ ፈንታ ነጋሪ ነው፡፡ አብርሃ አጽብሐም እስራኤልን የሚገዛውን የይሁዳ አንበሳ በትረ መንግሥቱ ሳይለያቸው ይህ በትረ መንግሥት በሚሰጣቸው ኃይል ለአዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብ ነጻነት፣ መዳንን የሚያመጡ ነገሥታት ሆነው ይገለጻሉ፡፡ ስለዚህ ለዚያ ነጻነት የሚያበቃ አዲስ ልደት ማኅበረሰቡም እንዲኖረው ለማጥመቅ ለማቁረብ ሐዋርያ እንዲልኩ ይደረጋል፡፡ ሐዋርያም ይሆናሉ፡፡ ዋናው ነጥብ ግን ሰሎሞናዊ ሆኖ ነገር ግን ከሰሎሞን የሚበልጥ ሰሎሞንን መሆንን ስለሚሹ "ከሰሎሞን የሚበልጥ" ከተባለለት ኢየሱስ ጋር ወንድማማች መሆን አማራጭ የሌለው መንገድ ሆኗልና በነገር ሁሉ እርሱን አስመስሎ ተጋዳልያኑን ማቅረብ በገድሉ ተዘውትሯል፡፡

ስለዚህም እንደተጋዳሊ የሚያልፉት ቅጽር የማያሸንፉት ጠላት ልክና ዓይነት አቻ የመሆኑ አምሳያ የጌርጌሴኖን አጋንንት ሆኖ ይገኛል፡፡ ኢየሱስ እርሱን ረትቷልና ለእነርሱም እንዲገጥማቸው የሚላከው ተገዳዳሪ ተሳድዶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ይኸው መንፈስ በመሆኑ በመርታት በአሸናፊነት እኩል ሚዛን ይደፋሉ፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ወዳለበት ወዳሸናፊዎችም ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይዘልቃሉ፡፡ በዚያም ያለውን ኃይልና እውቀት ሁሉ ተላብሰው በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ዳግም የሚያመጡትን በረከት ወደ ሚጠባበቀው ተከታይ ማኅበረሰብ መጥተው መቅደሱን ለመሠራት የበቁ ይሆናሉ፡፡

እነዚህ ነገሥታት ተጋዳልያን ሁለት ሲሆኑ እንደ አንድ ሐሳብና ግብራቸው በገድሉ ይተረክላቸዋል፡፡ የነገሡትም በአንድ መንበር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከምድር የሆነውን ምግብና መጠጥ እየበሉ በሰማያዊ እውቀት የበለጸጉ፣ የጽድቅ ትሩፋት የተላበሱ ሆነው ለተደራሲው ይታያሉ፡፡ ይህ ተጋዳልያኑን የበለጠ ተመራጭ የሚያደርጋቸው በዘመናቸው ሰላምና ዕረፍት ያለበት፣ ፍትሕ የቀናበት ዘመን መሆኑን በመንገር፣ ሰሎሞን መቅደስ ለመሥራት በተመረጠበት ሁኔታ ውስጥ ማለፋቸውን በማሳየት መቅደሱን ለመሥራት የተገቡ ሆነው መገኘታቸውን ጸሐፊው ሊያሳምነን መፈለጉን ያሳያል፡፡ ተገቢነቱ ብቻ ሳይሆን ኃይልና ጥበብ ይሰጣቸዋል፡፡ የዚህ ኃይልና ጥበብ ትእምርት ደግሞ በትረ ሙሴው ነው፡፡ ይህ ለሚመሩት፣ ተስፋ ለሚያደርጓቸው ማኅበረሰብ መተማመኛ ነው፡፡

መቅደሱ በተጋዳልያኑ ውስጥ ሆኖ ራሱን የተመረጠ አድርጐ የሚያስበው ማኅበረሰብ የመመረጡ ምልክት ነው፡፡ ስለዚህ ከዚያ በፊት የሚመጡ ትረካዎች ሁሉ ለዚህ ማሳመኛ የሚሆኑ ገጽታዎችን ሁሉ ለተጋዳሊው ማላበስ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስን

በመምሰል በመጡት ተጋዳልያን ውስጥ ንጉሥ ሰሎሞን ከነገሠበት ከቀደመው እስራኤል የበለጠ ታላቅነትና መመረጥ እንዳለው ሊያሳየን የሚሻው፡፡ ከዚያም በላይ ነገሥታት ተጋዳልያኑ የጽድቅ ትሩፋትና የኃይል በትርን ተጠቅመው ከዐለት ውሃ የሚጠጡ የሚያጠጡ፣ ከሰማይ መና የሚበሉና የሚያበሉ እስከመሆን እንደደረሱ ይተረክልናል፡፡ በትሩ የኃይልና የሥልጣን ትእምርት ነው፡፡ በዚያውም የኃይልና /የሥልጣን/ በትር ከእጅ እንደማያጣ የተነገረለት የይሁዳ ነገድ ወራሽ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በትር ለጽዮን ልጆች የሚገባም ነውና በአፍሪካ ምድር ያለ ጽዮናዊነትን በዚያው ይተክላል፡፡

አብርሃ አጽብሐ ይህንን ኃይልና ጥበብ መመሪያ ይዘው ቅጽርን ሁሉ ዘልቀው ወደ ተፈላጊው በረከት እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡ እርሱም መቅደሱን በአክሱም ጽዮን መሥራት ነው፡፡ ያለዚህ ታላቅ መቅደስ እነርሱ ከሰሎሞን የሚበልጡ ሰሎሞናውያን ሕዝቡም ከእስራኤል የሚበልጥ አዲሱ እስራኤል ሊሆን አይቻለውም፡፡

ስለዚህ የሰሎሞን መቅደስ የተሠራበት ጥበብ፣ የአሠራር ሂደትና ሥርዓት ሁሉ ሳይጐድልበት ነገር ግን በተጋዳልያኑ የበለጠ /የላቀ/ ስብእናና የጽድቅ ትሩፋት ምክንያት ከሰሎሞን መቅደስ የበለጠ መቅደስ ሆኖ ይሠራል፡፡ ከተጋዳልያኑ የጽድቅ ትሩፋት ሌላ የመቅደሱ አርአያ፣ መሥሪያ ቁስ ሠራተኞችም ሰማያዊ በመሆናቸው መቅደሱ ታላቅ ይሆናል፡፡ ከዚህ በላይ የበለጠ ታላቅ የሚያደርገውም መልክ ተሰጥቶታል፡፡ የኢየሩሳሌም ታላቅ መቅደስ ይፈርሳል ብሎ የተናገረው ኢየሱስ የአብርሃ አጽብሐን መቅደስ ግን ከጅምር እስከ ፍጻሜ ባሉ ሂደቶች በሥራው ሲሳተፍ እናያለን፡፡ መቅደሱ በኢየሱስ ይፈርሳል የተባለው የቀደመው የይሁዳ ግዛት መቅደስ ሳይሆን በኢየሱስ የከበረ አዲሱ የይሁዳ ነገድ ግዛት መቅደስ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ቤተመቅደሱ ተጋዳልያኑን ያበቀለው ማኅበረሰብ ራሱን የተመረጠ አድርጐ የሚያስብበት ርእዮት ምልክት ነው፡፡ ቤተመቅደስም የተለየ ሰብእና ማንነት ምልክት ነው፡፡ የተመረጠበት ልክ ዳዊት ሰሎሞን ከነገሡበት፣ ኢየሱስ ተወልዶ ካደገበት፣ ሞቶ ከተነሣበት ማኅበረሰብ ጋር የሚያነጻጽረው ይህ ማኅበረሰብ የመመረጡን መሠረት ያንነ ሰሎሞናዊነት አድርጐ ነገር ግን ከሰሎሞን ማኅበረሰብ የሚበልጥ ማኅበረሰብ ሆኖ የሚታይበትን መልክ በሚታዊ ተረኮች የተላበሰ ነው፡፡ አዲሱን ታላቁ የእስራኤል ማኅበረሰብ ያደርጋል፡፡ የዚያ ማኅበረሰብ ንግሥና፣ ክብር፣ ልዕልና፣ መመረጥ፣ ወራሽ ሆኖ፣ የማይፈርስም መቅደስ /የማይበተን ምርጥ ዘር/ አድርጐ ራሱን የሚያስብ ነው፡፡ የማንነቱ የባህሉ፣ የርእዮተ ዓለሙ መሠረት ይኸ ነው፡፡ በዚያ ርእዮተ ዓለም ላይ ቆሞ አዳኝ ታዳጊ ሆኖ ሌሎችን ሊያጠምቅ ይነሣል፣ አሸናፊ አንበሳ ሆኖ

ሌላውን እየሰበረ ይስፋፋል፡፡ የግዛቱ ጥንካሬና ገናናነት ምስጢር በዚህ ርእዮት ላይ የተደገፈ ሥነ ልቦና መታጠቁ ነው፡፡

ይህ ግን በአብርሃ አጽብሐ ገድል ብቻ የተንጸባረቀ አይደለም፡፡ ሌላው ንጉሥ ተጋዳሊ ላሊበላም በዚሁ መንገድ ይጠራል፣ ይዘልቃል፣ የሚፈልገውን በረከት ይዞ ይመለሳል፡፡

ላሊበላ እንደ አብርሃ አጽብሐ የኢየሱስን የልደት ቀን የልደቱ ቀን፣ ኢየሱስ የተወለደበትን አምሳያ /ገጽታ/ ገጽታ አድርጐ ለተጋድሎ እንዲጠራ ተደርጎ መሳሉን እናያለን፡፡ ላሊበላ ተለይቶ ሊዘልቅበት የተለየው የተጋድሎ ቅጽር በዘመዶቹ /በቤተ መንግሥቱ ቤተሰብ/ የተዘጋጀለትን መርዝ ጠጥቶ ሞትን ማሸነፍ ይሆናል፡፡ ተጋዳሊው ይህንን ቅጽር ዘልቆ መርዝ የጠጣ ትኩስ ሥጋውን በምድር ትቶ በአካለ ነፍስ ወደሚያደርገው የሰባቱ ሰማያት ጉዞ ይዘልቃል፡፡ ከአሸናፊዎች ኅብረት ጋር ይቀላቀላል፡፡ በዚያ አሸናፊው አንበሳ ኢየሱስ አለና የእርሱ ቡራኬ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተቀብሎ እርሱን መስሎ በሦስተኛው ቀን ከሞት ሊነሣ ወደ ምድር ይወርዳል፡፡ ይህ ሚታዊ ጉዞ ንጉሡን፣ ተጋዳሊ ላሊበላን፣ ከሌሎቹ ነገሥታት ተጋዳልያን አብርሃ አጽብሐ ጋር አንድ ያደርጋቸዋል፡፡

በላሊበላም በአብርሃ አጽብሐም ያየነው ኢየሱስን መስሎ የመጠራትና ወደ አንድ ቅጽር ዘልቆ ከአሸናፊዎች ጋር ማኅበር ጋር መቀላቀል በ ሁለቱም ገድሎች የሚነበብ ነው፡፡ ስለዚህ በነገሠታት ገድል ቁልጭ ብሎ የሚታየው ይህ ኢየሱስን መስሎ የመጠራቱ ነገርና የኢየሱስን ንግሥና የማሰቡ ነገር ያለው የአገዛዝ ሥርዓት ኅልፈት ሽረት የሌለበት ሆኖ እንዲቀጥል ገድሉን ባበቀለው ማኅበረሰብ ያለውን የጸና ምኞት አመላካች ይሆናል፡፡ በኢየሱስ መሲሕ /አዳኝነት/ ቤተመንግሥቱ አንዳች መንፈሳዊ ጸጋ፣ ድኅነት ለማምጣት ተለይቶ /ተባርኮ/ የተሰጠ ሥርወ መንግሥት ሆኖ መተከሉን ይነግረናል፡፡ በኢየሱስ ድል ነሺ አንበሳነት ይህ ሥርወ መንግሥት ሞዐ አንበሳ ተብሎ በታላቅ ግርማ ተስፋፊነቱን የሚፈጽም ኃይል ይሆናል፡፡ በአብርሃ አጽብሐ "ቆጥሮ ራሱን ከይሁዳ ወገን ያደረገው ሥርዓት በላሊበላ ደግሞ የዘር ስብራቱ ሳያግደው በሰማያዊ ቅብዐ መንግሥት ከኢየሱስ ጋር ተዛምዶ ከይሁዳ /ከእሴይ/ በትር ያቆጠቆጠው ምርጥ ዘውግ አካል ሆኖ ታይቷል፡፡

ላሊበላም እንደ አብርሃ አጽብሐ ንጉሥ ነው፡፡ መቅደስ ሊሠራ ይነሣል፤ ከሥር ከመሠረቱም ተለይቶ ለተጋዳሊነት ሲጠራ ይህንን መቅደስ መትከል ተፈላጊው በረከት ሆኖ ይነገረዋል፡፡ እርሱንም እውን ሊያደርግ ይቀባል፤ ይህንን እውን ለማድረግ ኃይል ጥበብ የሆነ በትር ይሰጠዋል፤ ይህም ከሙሴ በትር ጋር ተነጻጽሮ የተሰጠው ገብረ መስቀል የተባለ ስሙ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ተመራጭ የሚያደርገውም እንደ አብርሃ አጽብሐ መቅደስን ከሠሩ ሌሎች የእስራኤል መሳፍንትና ነገሥታት የሚለየውን የጽድቅ ትሩፋት ይላበሳል፡፡ በዚህ ጽድቁ ሰብእናውን ከሰብእናቸው አልቆ ከእነርሱ በነገር ሁሉ የላቀ ቤተመቅደስ ለመሥራቱ ሁነኛ አመላካች ትልም ሆኖ በታሪኩ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ በሠሪው በላሊበላ ቅድስና ሁሉ በስም ተጠቅሰው መበለጣቸው በገድሉ ከተነገራቸው ከሙሴና ከሰሎሞን መቅደስ የላቀ ቤተመቅደስ ይሠራል፡፡ ለዚሁ ቤተመቅደስ ታላቅነት ማመላከቻ የሆኑ ሁነቶች በየምዕራፉ እናገኛለን፡፡

ተጋዳሊው ላሊበላ ከታሪካዊው ላሊበላ በተለየ የሥራውን ንድፍ /አርአያ/ ለማየት ወደ ሰባቱ ሰማያት ከመሔዱ ባሻገር በምድር ያለውን የሰሎሞንን ከተማ ኢየሩሳሌምንና ቀደምቱ ተጋዳልያን አብርሃ አጽብሐ መቅደስ የሠሩበትን ከተማ አክሱምን በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ደርሰባቸው እንዲመለስ ይደረጋል፡፡ ይህ ሁሉ አሰሳ "ከሰሎሞን የሚበልጥ በዚህ አለ" ለማስባል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለሰሎሞን ለሙሴ የሆነው ጥበብና ኃይል ሳይቀርበት ለእርሱ ግን የላቀ ጥበብና ኃይል የተሰጠው ሆኖ ይገለጻል፡፡ የዚያ ማሳመኛው ደግሞ በአብርሃ አጽብሐ እንደታየው የጽድቅ ትሩፋቱ ይሆናል፡፡

በአብርሃ አጽብሐ ገድል ያገኘነውን ይዞ የተመለሰውን በረከት ማለትም የታላቁን መቅደስ አንድምታ ከላሊበላም ገድል የምንወስደው ይሆናል፡፡ ከጅምር እስከ ፍጻሜ በገድሉ ተደጋግሞ የሚጠቀሱት ለንጽጽር የሚመጡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቀደም ጠቃሾች ሁሉ የምርጦች ምርጥ የመሆን፣ ከዚያ ከቀደመው ክብር የመብለጥ፣ በኃይልና በጥበብ ልቆ አሸናፊ ዘውግ የመሆን ሩጫ ነው፡፡ መቅደሱ የአዲሱ የእስራኤል ማኅበረሰብና የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ትእምርት ነው፡፡ ይህንን ተፈላጊ በረከት ለማምጣት ግን በሁለቱም ገድሎች ያሉ ተጋዳልያን የሚጓዙባቸው ፈለጎች ተደራሲው ሊጠይቅ /ሊያነሣ/ የሚችላቸውን ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚሰጡ ሁነቶች በተደራደሩበት ትልም የተሠሩ ተረኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ትልሙን ያጠነከሩ ሁነቶች በአብዛኛው በሁለቱ ገድሎች መመሳሰላቸው ነገሥታት ተጋዳልያን የተጻፈላቸው ገድል ሁሉ መነሻና መድረሻ ፈለጎች በደንብ እንዲጠኑ የሚያነሣሣ ይሆናል፡፡ በተለይም በኢትዮጵያውያን ተረኮች ውስጥ ያለውን የባህል መሠረት፣ ሥነ-ልቦናዊ ማንነት ጉዳይ የቋጠሮውን ውል ለማግኘት ፈር ቀዳጅ ይሆናል፡፡

በዚሁ መንገድ በተነጻጸረና በአቻነት መታየት የሚገባው የጳጳሳት ገድል ሲሆን በዚህ ጥናት የተካተተው የብቸኛው የጳጳስ ገድል የሆነው ገድለ አባ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ነው፡፡ ጳጳሱ ተጋዳሊ ከንጉሡ ተጋዳሊ ባልተለየ ሁኔታ በመመረጡና በተጠራበት መንገድ ኢየሱስን መስለ

ይታያል። አባ ሰላማም የተወለደበትን ሀገር በምድረ እስራኤል በማድረግ፣ ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ የተከሰቱ ሚታዊ ነገሮች ሁሉ በእርሱም ልደት እንደተከሰቱ ተገልጸውለት፣ በዮርዳኖስ ወንዝም እንዲጠመቅ ተደርጎ ስለኢየሱስ በተነገሩ ተረኮች ወስጥ ያሉ ሁነቶችን ወርሷል።

ንጉሡ ንግሥናውን ከኢየሱስ ንግሥና በማጋጠም መሠረት እንዲኖረው እንደተደረገ ሁሉ ጳጳሱም ክህነቱን ከኢየሱስ ሊቀካህንነት በመግጠም መሠረት እንዲያገኝ መደረጉን እናስተውላለን። ይህንን መሠረት ይዞ የተጠራው ጳጳሱ ተጋዳሊ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ወደ ሚፈለገው በረከት ለመድረስ የሚዘልቀው ቅጽር ይዘጋጅለታል። የቀይ ባህርን ሽፍቶች ሰይፍ በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ይሻገራል። አሁንም በየደረጃው የተዘጋጁለትን የፈተና ቅጽሮች ሰማለፍ የሚያበቃውን ኃይል ለመላበስ በደም በጸሎት ይጋደላል። ከዚያም ከኢየሱስ ክህነት መንፈሳዊ ዝርያ ዘር ቆጥሮ ሊዋለድ ወደ እስክንድርያ ይሔዳል። ይህን ሐዋርያዊ የክህነት ውርስ በእጁ ጨብጦ ይመለሳል። ከዚያ የበለጠ ታላቁን ቅጽር ሰብሮ ተፈላጊውን በረከት መቅደሱን ሊያመጣ ይነሣሣል። ለዚህ ዋነኛ መሣሪያው መስበክና ማጥመቅ ይሆናል። በዚህ ይጠርባል፣ ያስውባል፣ ይሠራል፣ ያንጻል፣ ያስጌጣል። የዚህ እንቅፋት የሆኑትን ቅጽሮች ሁሉ በተአምራት አሸናፊ ይሆናል። እነዚህ በሰይጣናት የተመሰሉ ተቃዋሚዎቹ ናቸው። መቅደሱም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ነው። ጳጳሱ ተጋዳሊ ከንጉሡ ተጋዳሊ በተለየ የሚሠራው መቅደስ የኢትዮጵያን ማኅበረሰብ ነው። ባህል ሥርዓት ወግ ልማድ ማኅበራዊ ሕግጋት ይሠራል። በዚያ መጠበቂያ ማኅበረሰቡን አያይዞ በአንድ ሥርዓት ውስጥ ያንጻል።

ጳጳሱ ተጋዳሊ ከንጉሡ ተጋዳሊ ቢበልጥ እንጂ አያንስም እንደ ንጉሡ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያለ መሐላ ለይሁዳ ወገን የተሰጠው ክህነት ባለቤት ሆኗል። በዚህም የንጉሡን ተጋዳሊ የዘውግ ቅድስና ተጋርቷል። ንጉሡ የሠራውን ሕንፃ መቀደስ የሚያከብር ሌላ መቅደስ ማኅበረሰብ አንጿል። በዚህም የሰሎሞናዊው ሥርዓት የሚሣ መንግሥት ወራሽ ሆኗል። የንጉሡ ተጋዳሊ ሥራዎች ሁሉ የሚባረኩት በዚሁ ጳጳሱ ተጋዳሊ ነውና። ክህነት ከምስፍና እንደሚበልጥ ሊያሳምን ይጥራል። ቤተክህነት የባህሉ፣ የዕውቀቱ፣ የሕጉ፣ የሥርዓቱ ቀማሪ፣ የቡራኬው ሁሉ ምንጭ፣ የመንግሥቱ ቅብዐት መሠረት በትረ መስቀሌ ነው ትላለች። ለዚህም ነው ጳጳሱ ተጋዳሊ በሄደበት ሁሉ ምንጭ ይባርካል፤ ተቀድቶ የማያልቅ የሚያረካ የሚያረሰርስ ውሃ ያፈልቃል። እነዚህ ምንጮች ቀድሜ ከላይ የጠቀስኳቸውን እሴቶች ሁሉ ምንጭ የመሆኗ አምሳያ ነው። ይህን ኃይል እንደዋዛ የተገኘ አለመሆኑን ደግሞ ለማሳየት ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሄዶ ከታላቁ ሊቀ ካህን ከኢየሱስ ይገናኛል። በዚህ ተራክቦ ሉዓላዊ ሥልጣን ይወሌዳል።

ስለዚህ ቤተክህነት የቤተመንግሥቱ አንጋሽና አውራሽነቷን ታጸናለች፡፡ ያለ እርሷ ቡራኬ የሚጸና የሚቆም ሰሎሞናዊነት አይኖርም፣ ያለእርሷ ቡራኬ እርሷ ላሠራችው መቅደስ ማኅበረሰብ እምብርት የሚሆን ቤተመቅደስ አይኖርም፡፡ ስለዚህ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ መሆን መብት ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ነው በጳጳሱ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን ገድል ውስጥ ጳጳሱና ንጉሡ ተጋዳሊ አንድ ኅልም አይተው ሲደናነቁ የምናየው፡፡ ይህ አንድ ኅልም አንድ ርእዮት ነው፡፡ ጳጳሱ ባለበት ንጉሡ አለ፤ ንጉሡም ባለበት ጳጳሱ አለ፡፡ ግብር ካለ ዐሥራት በኩራት አለ፡፡ ይህ አንድ ሕልም ነው ገድሉን ያበቀለው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ርእዮተ ዓለም ምንጭ፡፡

ስለዚህ በንጽጽር ሲታይም በገድላቱ በሠፈሩ በተወሰኑ የመባያ ጉዳዮችና አምሳያዎች መለያየት ቢኖርም መባያዎቹና አምሳያዎቹ ያላቸው አንድምታ ተመሳሳይ በመሆኑ በማኅበረሰብ የሥልጣን ተዋረድ መሠረት ከፍ ያለው ሥፍራ በሚሰጣቸው በካህኑና በንጉሡ መካከል አንድ ርእዮት ማየት ይቻላል፡፡

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

I Newspaper, reports, history books, novels, films, comic strips, pantomime, dance, gossip, psychoanalytic sessions are only some of the narratives which permeate our lives.

II As Religions become institutionalized or associated with secular political power these collective sacred metaphors and the religions themselves tend to be distorted for self-serving or political purposes.

III A hero ventures forth from the world of common day into a region of supernatural wonder: fabulous forces are there encountered and a decisive victory is won: the hero comes back from this mysterious adventure with the power to bestow boons on his fellow man.

IV "Because I have called, and ye refused … I also will laugh at your calamity; I will mock when you're your fear cometh; when you're your fear cometh; as desolation, and your destruction cometh as a whirlwind; when distress and anguish cometh upon you" "when the turning away of the simple shall slay them and the prosperity of fools shall destroy them." /proverb 1: 24-27,32/

V The advanture is always everywhere a passage beyond the veil of the known into the unknown the powers that watch at the boundary are dangerous ; to deal with them is risky; yet for anyone with competence and courage the danger fades.

VI ወይቤሎ እግዚአነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት አምጽእ ማየ ዮርዳኖስ ወአምጽአ ፍጡነ፡፡ ወይበሎ እግዚእነ ኢየሱስ ለዮሐንስ መጥምቀ አጥምቆሙ ለእሉ ፍቁራንየ በውእቱ ማይ፤ ወይበሎ ዮሐንስ ለእግዚአነ እንዘ ሀሎ ጻጻስ ይደልወኒኑ ከመ አጥምቅ አነ፤ ወይቤሎ ከመ ይትዓወቅ ጽንዓ ፍቅርየ በላዕሌሆሙ፤ ወተመጠወ ዮሐንስ ወእተ ማየ እመ እደዊሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት፤ ወይበ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ወሰመዮሙ አብርሃ ወአጽብሐ፤ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌሆሙ….."

VII ወይቤልዎ አብርሃ አጽብሐ ለባስያነ መንፈስ ለውእቱ ሰይጣን ሚመጠን መዋዕል ዘነበርከ በውስተ ይእቲ ሀገር እንዘ ታስሕት አልባበ ሰብእ ወይቤ ሰይጣን ቀዳሚ ነበርኩ በሀገረ ጌርጌሴኖን ወእምዝ ወጽአ ኢየሱስ ናዝራዊ ዘይብልዎ ክርስቶስ ዘአንትሙ ታመልኩዎ እንዘ ይሜህር ወንጌለ ወሰደደነ እም ዝየ ወካዕበ ፈነወነ ኀበ መራዕየ አሕርው ወጸድሉ ኩሎሙ መራዕይ ሀድግነ ዘንተ ሀገረ ወፃድነ ኩሎ አድያመ ወበጻሕነ ኀበ ዝየ ወነበርነ እስከ ዮም በዛቲ ሀገር እንዘ ንከውን አማልከተ፡፡

VIII "ወይ ሊተ፣ አሌ ሊተ እፎ አሐውር እምቅድመ ገጸሙ ለእሉ ነገሥት ቀዳሚ ተንሥኡ በላዕሌነ ፤ወፀ እደው ወሰደዱነ እም ኢየሩሳሌም ወእም ኩሉ አህጉር ወነደግነ ሎሙ ወሮምኒ አመ ነበርነ ገዳመ ከመ አራዊት ወመጽኡ ኀቤነ እሉ ነገሥት ዕኑዓን ከመ ይስድዱነ እምዝየ እንከሰ ነበ አይቱ ነሐውር ወነበርነ በኢትዮጵያ ዘንሴፈዋ አንደጉነ አብርሃ ወአጽብሐ››

IX ፡‹‹ይእቲ በትር ትንብር ምስሌክሙ ወኢትትፈለጥ፣ ከመ ኢይቅረብ ጸላዓ ላዕሌክሙ"

X ተጋቢኦሙ ሰይጣናት ከመ ያንሕልዋ ለዛቲ መቅደስ ወርእዮሙ አብርሃ አጽብሐ ተምይንቶሙ ለእሙንቱ ሰይጣናት አንበርዋ ለይእቲ በትር ማእከለ መቅደስ ከመኢይቅረቡ ኀቤሃ ሰይጣናት....."

XI ወእም ድኅረ ፈጸሙ ጸሎተ ዘበጥዋ ለይዕቲ ኮክሕ በበትረ ሙሴ ዘሀለወት ምስሌሆሙ ወሶቤሃ ፈልፈለት ሀሊበ ወመዓረ

XII በመኑ እንከ ናስተማስሎሙ በዳዊትኑ ወሚመ በሰሎሞን፤ ባሕቱ ዳዊትኒ አመ ነበረ ዲበ መንበረ መንግሥቱ አመ አቅትሎ ለኦርዮ መስፍን በእንተ ብእሲቱ፤ ወሰሎሞንኒ አመ ነግሠ በኢየሩሳሌም ተበቀሎ ለኢዮአብ ወልደ ጌራ ፀረ አቡሁ፣ ወኢመሐኮሙ ወቀተሎ በእኩይ ሞት

XIII፡ ሕንፁ ሊተ ማኅደረ በይእቲ መካን

XIV "ወይቤልዎ አብርሃ አጽብሐ ኦ እግዚእነ ንሕነሰ ኢነአምር መጠኑ ለመቅደስ ወአሜሃ መሰጦሙ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስሌሁ በደመና ወአዕረኅሙ ውስተ ሰማይ ወአርአዮሙ ሥነ-ሕንፃሃ፣ ወሰነ ስቅለተ፣ ሥነ ርባታ ወሠራሬሃ ለኢየሩሳሌም ሰማያዊት

መዘርዝር

መራራስ አማን በላይ፤ መጽሐፈ አብርሂት፤ አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ድርጅት፤ 2004ዓ.ም

ሠርፀ ገብረመድኅን፣ «የገድለ ጊዮርጊስ የአጻጻፍ ባህርይና ሥነጽሑፋዊ ዕሴት»፣ ለአባዲማ የቀረበ፣ የኢ.ቋ.ሥ.ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1983ዓ.ም

ሥርግው ገላው /ተርጓሚ እና አርታዒ/፤ ክብረ ነገሥት ግዕዝና አማርኛ፤ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፤ 1994ዓ.ም

ስባሔ ካሣው፣ «የገድለ ተክለሃይማኖት የአጻጻፍ ባህርይና ሥነጽሑፋዊ ዕሴት»፣ ለአባዲማ የቀረበ፣ የኢ.ቋ.ሥ.ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1981ዓ.ም

ቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ፣ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ ግዕዝና አማርኛ፣ አዲስ አበባ፤ 2000ዓ.ም

ብርሃኑ አድማስ /ዲያቆን/፤ በዓላት፤ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን አሳታሚ ድርጅት፤ 1999ዓ.ም

ተስፋ ሚካኤል ታከለ፤ ገድል ዘቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ፤ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን አሳታሚ ድርጅት፤ 2005ዓ.ም

ታደለ ፈንታው /ዲያቆን/፤ ‹‹መሠረት ያላት የእግዚአብሔር ከተማ"፤ ስምዐ ጽድቅ፤ አዲስ አበባ፣ ሐምሌ 1፣ 2004ዓ.ም

ታደለ ፈንታው /ዲያቆን/፤ "መሠረት ያላት የእግዚአብሔር ከተማ"፣ ስምዐ ጽድቅ፤ አዲስ አበባ፣ ሐምሌ 16፣ 2004ዓ.ም

ቴዎድሮስ ገብሬ፤ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ 2001ዓ.ም

ቸርነት አበበ /መምህር/፤ አዲስ አበባ፣ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፤ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማ.፤ 2003ዓ.ም

አምሳሉ አክሊሉ፤ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ታሪክ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ /ያልታተመ/ 1976ዓ.ም

አራጌ ይመር፤ "በአራት ገድሎች ላይ የተደረገ ዐውደ ንባባዊ ትንታኔ"፣ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ዘርፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001ዓ.ም

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ሕማማተ መስቀል፤ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፤ 1961ዓ.ም

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ መዝሙረ ዳዊት ንባብና ትርጓሜ፤ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ድርጅት፤1982፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ መጽሐፈ ቅዳሴ በግዕዝና አማርኛ ከነምልክቱ፤ አዲስ አበባ፣ አክሱም ማተሚያ ድርጅት፤ 1993፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ መጽሐፈ ግጻዌ፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤1991፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ወንጌል ቅዱስ ዘእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንባብና ትርጓሜው፤ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ድርጅት፤ 1988፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ድርሳነ ሚካኤል፤ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ደርጅት፤1990፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ድርሳነ ዑራኤል ግዕዝና አማርኛ፤ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ድርጅት፤ 1985፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ገድለ ተክለሃይማኖት ግዕዝና አማርኛ፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፤ 1989፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ግዕዝና አማርኛ፣ አዲስ አበባ፣ 1998፡፡

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ ገድለ አብርሃ ወአጽብሃ፤ አዲግራት አብርሃ ወአጽብሃ ቤተክርስቲያን፡፡ /ያልታተመ/፡፡

ኤርምያስ ከበደ /ንቡረ ዕድ/፤ ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ፤ ዋሽንግተን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፤1993፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1948፡፡

ዘካርያስ ተኮላ፤ የቅድስት አገር ታሪካዊ ቦታዎች፤ ኢየሩሳሌም፣ 1993፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤ 1972፡፡

ዮሐንስ አድማሱ፤ «የልቦለድ ሥነጽሑፍ ጉዞ»፤ መነን 13ኛ ዓመት፣ ቁ 9፤ 1961፡፡

ደበበ ሰይፉ፡ «የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ዕድገትና አቅጣጫ»፡ የካቲት 3ኛ ዓመት፣ ቁ 4፡ 1974ዓ.ም

ገርጎርዮስ /አባ/፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፤ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት፤ 1974ዓ.ም

Abrams. M.H. A Glossary Of Literary Terms. (7th edn.) Boston: Heinle & Heinle a Division of Thompson Learning Inc. 1999.

Campbell, Joseph. The Hero with a Thousand Faces. (2nd edn.) Princeton, New Jersey:Princeton university press. 1948.

Ephrem Eshete. ‹‹Narative Techniques of Three Selected Ethiopian Hagiographies." MA Thesis, DFLL. Addis Ababa: School of Graduate Studies Addis Ababa University. 1999.

Getatchew Haile. "Religious Controversies and the Growth of Ethiopic Literature in the Fourteenth and Fifteenth Centuries. "Reprinted From Oriens Christianus-Wiesbaden. 1981.

Getatchew Haile. "Remarks on the content of Geez Literature of Ethiopia" in History Journal. V II. No.2. Addis Ababa: HSU. 1988.

Kineferegeb Zelke. "Bibliography of Ethiopian Hagiographical Traditions." Journal Of Ethiopian Studies.V. 13,No.2. Addis Ababa. 1975.

Leeming, David. Myth: A Biography of Belief. Oxford: Oxford University Press. 2002.

Malaty, Tadros. /Fr/. Church, House of God. (6th ed.) Alexanderia: St.Mena Monastery Press. 2004.

Kennan. S. Rimmon. Narrative Fiction: Contemporary Poetics. London: Metheun. 1983.

Sergew Hableselassie. Ancient and Medival Ethiopian History to 1270. Addis Abeba: United Printers. 1972.

Selamawit Mecca. ‹‹Women in Ethiopic Hagiographies›› In: *Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies.* ed. by Svein Ege, Harald Aspen, Birhanu Teferra and Shiferaw Bekele. Trondheim. 2009.

Taddesse Tamrat. "Hagiographies and the Reconstruction of Medival Ethiopian History " Conference On Current Research Trends in Ethiopian History.Addis Ababa:A.A.U. I.E.S. 1988.

Taddesse Tamrat. Church and State 1270-1527. Addis Ababa: Oxford University Press. 1972.

The New Encyclopaedia Britanica. (15th ed.) V.24.Chicago:Encyclopaedia Britanica Inc. 1991.

Yonas Admassu. "Narrating Ethiopia: A Panorama of the National Imaginary"A Dissertation Submitted in Partial Satisfaction of the Requirements for the Degree Doctor of Philosophy in Comparative Literature. Los Angeles: University Of California. 1995.

ይህ ቴስስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የኔ ወጥ ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩንቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ።

ስም _____

ፊርማ _____

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ግንቦት 2005 ዓ.ም